አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በ2004 ዓ.ም በታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት ፍተሻ

በ

ዘውዴ ታሪኩ ተገኝ

ነሐሴ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# በ2004 ዓ.ም በታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት ፍተሻ

በ

ዘውዴ ታሪኩ ተገኝ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በተግባራዊ ስነ ልሳን አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

**2004 ዓ.ም በታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት ፍተሻ**

በ

ዘውዴ ታሪኩ

ነሐሴ 2007 ዓ.ም

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ጌታሁን አማረ (ዶ/ር) | |

| የፈታኝ ስም | ፊርማ |
|---|---|
| ደረጀ ገብሬ | |
| ግርማ ገብሬ | |

## ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ አሁን የያዘውን መልክ እንዲኖረው ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እያንዳንዱን ምዕራፍ በተደጋጋሚ በማረም ሙያዊ እገዛቸው ላልተለዩኝ ለውድ መምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ጌታሁን አማረ ምስጋናና አክብሮቴ የላቀ ነው፡፡

ይህንን ትምህርት እንድጀምር ከማበረታታት ጀምሮ ፈታኝ የሆነው የትምህርት ጊዜ እስኪጠናቀቅ በሀሳብና በገንዘብ እገዛው ያልተለየኝ ባለቤቴ ደመቀ መንግስት እገዛህ ለዚች ሰአት አድርሶኛልና የምስጋና ቃላትን በሙሉ ተጠቅሜ አመሰግናለሁ በሚለው መደምደሚያ ተመስገንልኝ፡፡

በትምህርት ቤት በነበረኝ ቆይታ በሀሳብና በቁሳቁስ እገዛቸው ያልተለየኝ ወንድሜ መኩሪያ ታሪኩ፣ ለባለቤቱ አስናቀች ሰኒ፣ ለልጁ ዳግማዊት መኩሪያና ሁልጊዜ በትምህርቴ የላቀ ደረጃ እንድደርስ ለሚመኙልኝ ቤተሰቦቼ በሙሉ እዚህ የመድረሴ ሚስጢር ናችሁና ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ነው፡፡

የጊዶሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ታገለ ኪታንቦ፣ የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የክፍል ጓደኞቼ ለጥናቴ እዚህ መድረስ ድርሻ አላችሁና መስጋናዬን ተቀበሉኝ፡፡

ከመጀመሪያው ረቂቅ ጀምሮ እስከ ፍፃሜ ከመልካም ስነ ምግባር ጋር የኮምፒውተር ፅሁፍን ለተየበችልኝ ለወ/ሪት ሰናይት አጥላው ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

## ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ....................................................................................................................i

ማውጫ ....................................................................................................................ii

የሠንጠረዥ ማውጫ ....................................................................................................v

አጠቃሎ ....................................................................................................................vi

**ምዕራፍ አንድ**

1. የጥናቱ ዳራ ....................................................................................................1

2. የጥናቱ አላማ ....................................................................................................3

3. የጥናቱ አስፈላጊነት ............................................................................................3

4. የጥናቱ ወሰን ....................................................................................................4

**ምዕራፍ ሁለት**

2. የዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ........................................................................................5

2.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት .......................................................................5

2.1.1 የቋንቋ መማሪያ መፃሐፍት አስፈላጊነት ..................................................................6

2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መፃሐፍት አይነቶች ......................................................................8

2.1.2.1 ልማዳዊ የመማሪያ መፅሐፍ ................................................................................8

2.1.2.2 ተግባቦታዊ የመማሪያ መፅሐፍ ............................................................................9

2.1.3 የመማሪያ መፃሐፍት ባህሪያት ............................................................................10

2.1.4 የንባብ ምንነት ................................................................................................11

2.1.5 ለምን እናነባለን? ..............................................................................................13

2.1.6 ምን እናነባለን? ................................................................................................14

2.1.7 እንዴት እናነባለን? ............................................................................................14

2.1.8 የአንብቦ መረዳት ምንነት ....................................................................................16

2.1.9 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ..................................................................................17

2.1.10 የአንብቦ መረዳት ጥያቄ አይነቶች ..........................................................................21

2.1.11 የቋንቋ ክሂል መልመጃ ምንነት ............................................................................23

2.1.12 የቋንቋ መልመጃ አደረጃጀት ..................................................................................23

2.2 የቀደምት ስራዎች ቅኝት ......................................................................................25

ምዕራፍ ሶስት

3. የምርምር ንድፍና ዘዴ ....................27
3.1 የመረጃ ምንጮች ....................27
3.2 የናሙና አመራረጥ ....................27
3.2.1 የመማሪያ መፃሐፍቶቹ ናሙና አመራረጥ ....................27
3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ....................28
3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ....................28
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች ....................29
3.3.1 የሰነድ ፍተሻ ....................29
3.3.2 በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ....................29
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ....................30

ምዕራፍ አራት

4. የመረጃ ትንተና ....................31
4.1 የተተኳሪ መፃሐፍቱ አጭር ቅኝት ....................31
4.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ....................32
4.2.1 የክሂሎች ቅንጅት ....................37
4.2.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አደረጃጀት ....................43
4.3 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር ....................47
4.3.1 ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያለው ቅንጅት ....................54
4.3.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አደረጃጀት ....................58

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያና አስተያየት ....................61
5.1 ማጠቃለያ ....................61
5.2 አስተያየት ....................63
ዋቢ መጽሐፍ ....................65

## አባሪዎች

አባሪ አንድ ፦ ለአስረኛ እና ለዘጠነኛ ክፍል የቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ ..........................69

አባሪ ሁለት ፦ የዘጠነኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች .....................................72

አባሪ ሦስት ፦ የአስረኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች.......................................82

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ሠንጠረዥ 1፡ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር የሚያሳይ ........................................ 33

ሠንጠረዥ 2፡ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነቶችን የሚያሳይ ........................................ 36

ሠንጠረዥ 3፡ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ስብጥር የሚያሳይ ........................................ 47

ሠንጠረዥ 4፡ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነት ........................................ 49

ሠንጠረዥ 5፡ በመጠይቁ ለሚገኙ ጥያቄ ቁጥር 1፣ 2፣ 3 እና 7 ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ ........................................ 52

# አጠቃሎ

*የዚህ ጥናት አላማ በ2004 ዓ.ም በታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍ ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄ አይነትና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ አጥኚዋ በዋና የመረጃ ምንጭነት የሰነድ ፍተሻን የተጠቀመች ሲሆን በአጋዥ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ስለሚገኙት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት ላይ የሚያጠነጥኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከሰነድ ፍተሻና ከተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች የጥያቄዎቹን አይነትና አደረጃጀት መሠረት በማድረግ ተተንትነዋል፡፡ ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመለክቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አይነትና አደረጃጀት ጠንካራም ደካማም ጎን ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በጥናቱ የታዩት ጠንካራ ጎኖች የዘጠነኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው መቅረባቸው፣ የጥያቄዎቹ አደረጃጀት ተገቢውን የአደረጃጀት መንገድ የተከተሉ መሆናቸው እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ቋንቋውን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ለሚደረገው ልምምድ የሚያግዙ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ በዚሁ ክፍል የታዩ ደካማ ጎኖች ከአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ውስጥ በአዛምድ መልክ የቀረቡ ጥያቄዎች አለመካተታቸው፣ በዝግና በክፍት መልክ የቀረቡ ጥያቄዎች ተመጣጣኝ አለመሆን፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ትዕዛዝ ግልፅ አለመሆን ችግሮች ታይተዋል፡፡ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የታዩ ጠንካራ ጎኖች የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ የጥያቄ ሰብጥራቸውን የጠበቁ መሆን፣ የመልመጃዎቹ አደረጃጀት ተገቢ የአደረጃጀት ስርአትን የተከተለ መሆንና ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው የቀረቡ መሆናቸውን ወዘተ… በጥናቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚሁ ክፍል የታየ ደካማ ጎን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ትዕዛዞች ግልፅ አለመሆንና የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚያግዙ ጥያቄዎች አለመካተታቸው ወዘተ… መሆኑን ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም የመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት ላይ የታዩ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ለንግግርና ለፅህፈት ክሒሎች የተሰጠው ትኩረት ለማዳመጥ ክሒልም ቢሰጥ ግልፅ ያልሆኑ ትዕዛዞች በግልፅ ቢሰፍሩ ለዘጠነኛ ክፍል የክፍትና የዝግ ጥያቄዎች ቁጥር የተመጣጠኑ ቢሆኑ ሁለቱመተ መማሪያ መፃህፍት ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆኑ አጥኚዋ ታምናለች፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## 1. የጥናቱ ዳራ

በሀገራችን በተወሰኑ አመታት ቆይታ የመማሪያ መፅሐፍቶች በአዲስ መልኩና የነበረውን በማሻሻል ይዘጋጃሉ፡፡ በዚህ ሂደት የተለያዩ የክፍል ደረጃዎችን መሠረት አድርገው ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ መማሪያ መጽሐፍት በትምህርት እና በቋንቋ ሳይንስ መርሆች ላይ ተመስርተው በተገቢው መንገድ ከተዘጋጁ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ቀላል እንዲሆንና ፍሬያማ ውጤት እንዲያስገኙ በማድረግ በኩል ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ Hutchinsion and Torres(1994) እንደሚገልፁት ተማሪዎቹ ትምህርቱን ሲያካሂዱ፣ ሲወያዩ መልመጃዎችን ሲሰሩ፣ ሲያጠኑ፣ የቋንቋ ተግባራትን ሲያከናውኑ፣ የቤት ስራ ሲሰሩና ለፈተና ሲዘጋጁ ወዘተ. መማሪያ መፅሐፍትን ይጠቀማሉ፡፡ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ትምህርታቸውን በማደራጀት በኩል እገዛ ስለሚያደርጉላቸው ተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍቱን እንደ መመሪያ አድርገው ይመለከቷቸዋል፡፡ ለመምህራኑም ከተማሪዎቻቸው ፍላጎት ጋር የተስማሙ የትምህርት ይዘቶችን ስለሚያቀርቡ ተማሪዎቻቸው ተምረው ያለፉትን አሁን እየተማሩት ያለውን እና ወደፊት የሚማሩትን ስለሚጠቁሙ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተቀላጠፈ እንዲሆን ስለሚያግዙ ከጊዜና ከገንዘብ አንጻርም ወጪ ቆጣቢ ስለሆኑ በመማሪያ መጽሐፍ በመገልገልትምህርቱንይሰጣሉ፡፡

እንደ Dubin and Olishtain (1992) ገለፃም ለቋንቋ ማስተማሪያነት ተብለው የሚዘጋጁ መማሪያ መፅሐፍት የታላሚውን ቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶችን አቀናብረው የያዙና የቋንቋውን ስነ ልሳናዊና ስነ ትምህርታዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ ንባብ ነው፡፡ ንባብ ከተቀባይ ክሂሎች ውስጥ የሚካተት ሲሆን ከምናነበው ጽሁፍ ውስጥ ቁም ነገር ነቅሶ ማውጣትን፣ የምንባቡን ዝርዝር ሀሳብ መረዳትን መቀበልና ማስተላለፍ፣ የቃላትን አውዳዊፍቺ መረዳት ወዘተ. አጠቃሎ የያዘ መሆኑን ያመለክታሉ (Harmer 1991፣ Sheng 2000)፡፡

በተጨማሪ የንባብ ተግባር ረቂቅና አእምሮአዊ ሂደት በመሆኑ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክዋኔና ምንባብን የተረዱበት አተያይ በርካታ ሊሆን ይችላል፡፡ Williams (1984) እና Davis (1995) ንባብ ግላዊ ተግባር መሆኑን ገልፀው በዚህም እያንዳንዱ ተማሪ አንድን ምንባብ

አንብቦ ለመረዳት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ማለትም የመረዳት፣ የመተርጎም፣ የማገናዘብና ምንባቡን በራስ ሀሳብ የመግለፅ ሁኔታ ከግላዊ ችሎታውና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከነበረው ዳራዊ እውቀት አኳያ የተለያየ ሊሆን እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ በዚህም መሰረት አንብቦ መረዳትን ለማስተማር በሚቀርቡ መልመጃዎች ስር የሚካተቱ ጥያቄዎች የተማሪዎችን የተለያየ የግንዛቤ ደረጃ የሚፈትሹ መሆን እንደሚኖርባቸው ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ውጤታማ ትምህርት ለማስተማር የሚረዱ መሆን አለባቸው፡፡ ስለሆነም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ሲቀርቡ የትምህርቱን አላማ መሰረት አድርገው ተማሪው አላማውን በተሟላ መንገድ ለማከናወን እስከቻለ ድረስ በ "አዎ" ወይንም "አይደለም"፣ በ"እውነት" ወይም "ሐሰት" "ባዶ ቦታን በመሙላት"፣ በ "ምርጫ" ወዘተ መልክ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በአንድ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኝን የአንብቦ መረዳት መልመጃ አዘጋጅ ተማሪውንና ተግባራቱን በማገናኘት ተማሪው ውጫዊና ውስጣዊ ፍንጮች ተጠቅሞ በቀረበው ይዘት አማካኝነት የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆን መርዳት ነው (አለም 1995፣ Harmer 2001፣ David 2005)፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ በርካታ ነጥቦች መካከል በመሰረታዊነት የሚጠቀሱትን Grellet (1991፡6-9)አብራርተዋል፡፡ እነሱም ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመር፣ የጥያቄዎችን ስብጥር መጠበቅ፣ ከልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀትና በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ናቸው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በዘፈቀደ የሚፃፍ ድንገተኛ ስብስቦች ሳይሆኑ ከሚፈለገው አላማ ጋር በተያያዘ መንገድ በስልት ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማስተማር አመቺ የሆኑ ስራዎች በውስጣቸው የያዟቸውን ዋነኛና ደጋፊ የሆኑትን ሐሳቦች አንቀፆችንና ዓርፍተነገሮችን የፅሁፎቹ ባህሪያት ጋር ለማያያዝ የሚያስችሉ ቃላትን እንዲረዱ የሚያግዙ መልመጃዎችን ያቀርባሉ (Dubin and Olshtain 1986:164)፡፡ እንዲሁም ምንባብን አንብቦ ለመረዳት የሚያግዙ ጥያቄዎች የተለያዩ አይነቶች ሲሆኑ፣ ከሁሉም ውስጥ ተማሪው አንብቦ የመረዳት ክሂሉን እንዲጠቀም የሚያደርጉ አነባብን የሚመለከቱ ጥያቄዎችም ይገኙበታል፡፡ በምንባቡ ውስጥ ወዳሉ የተወሰኑ አርፍተ ነገሮች ስሜታቸውን በመምራትና

ከጥያቄው አርፍተ ነገር አስፈላጊነት ጋር በማያያዝ ትክክለኛውን መልስ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል (Widowson 1978፡110)፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አንባቢ የአንድን ጽሁፍ ሁለንተናዊ መልእክት ከተለያዩ አተያዮች አንፃር ለመገንዘብና ለመመርመር የሚዘጋጁ ሲሆኑ ክሂልን ለማዳበርም አበረታች መንገድ የሚቀይሱ ናቸው፡፡ ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን አይነታቸውንና አደረጃጀታቸውን በመፈተሽ ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ነጥቦች መጠቆምና ሊበረታቱ የሚገባቸውን ማበረታታት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም፡፡ በዚህም መሠረት በ2004 በአዲስ መልክ የታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀትን መፈተሽ የዚህ ጥናት ትኩረት ነው፡፡

## 2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሀገር አቀፍ ደረጃ በ2004 ዓ.ም የታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ. በ2004 ዓ.ም የታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነታቸውን መፈተሽ፡፡

ለ. በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች እንዴት አደረጃጀታቸውን መፈተሽ፡፡

ሐ. በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር (የክፍትና የዝግ) ጥያቄዎች ተመጣጣኝነት መመርመር

መ. በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅት መመርመር ነው፡፡

## 3. የጥናቱ አስፈላጊነት

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጥሀፍ ለቋንቋው ትምህርት ተግባር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ በመሆኑም የመማሪያ መፃህፍት በአገልግሎት ላይ እያሉ የሚታይባቸውን የዝግጅት

ጉድለት ለመሙላት የተለያዩ የግምገማ ስልቶችን በመጠቀም መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በ2004 ዓ.ም በአዲስ መልክ የታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን አይነትና አደረጃጀት ላይ ፍተሻ ስለሚያደረግ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

ሀ. ለስርአተ ትምህርት ጥናትና ዝግጅት ክፍል መረጃ ይሰጣል

ለ. ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች በቀጣይ ለሚያከናውኑት የማሻሻል ስራ ያግዛል

ሐ. በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀታቸው ተገቢ መሆን አለመሆኑን በመመርመር ለቋንቋ መምህራን መረጃ ይሰጣል፡፡

## 4. የጥናቱ ወሰን

በሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ለማስተማር መማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በሀገር አቀፍ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ጥናት በ2004 በአዲስ መልክ የታተሙትን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ በሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ ሁለተኛ ደረጃ የሚባለው ዘጠነኛና አስረኛ ክፍልን ነው፡፡ ጥናቱም በእነዚህ ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ብቻ ይዳስሳል፡፡ በዚህ ጥናት ሌሎች ክሂሎች ማለትም ማዳመጥ፣ መናገርና መፃፍ እንዲሁም የሰዋስውና የስነፅሁፍ መልመጀዎች በጥናቱ አይካተቱም፡፡ ነገር ግን ከምንባብ የወጡ የክሂል፣ የሰዋስውና የስነፅሁፍ ጥያቄዎች የጥናቱ አካል ናቸው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ወሰን ለጥናቱ በተመረጡት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነታቸው፣ አደረጃጀታቸው፣ የንባብ ጥያቄዎቹ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅት ምን እንደሚመስል ሰነዶቹን ይፈትሻል፡፡ ጥናቱ ከ2004 በፊት የታተሙ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍትን አያካትትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ ጥናቱ ይዞት ያተነሳውን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ የተለያዩ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝቶች ተካተዋል፡፡ በቅኝቱ መሰረት ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጉዳዮች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ምንነት፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አስፈላጊነት፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አይነቶች እና ባህሪያት፣ የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ ምንነት፣ የመልመጃዎቹ አደረጃጀት፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንነትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄ አይነቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 2.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ምንነት

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን ዋና ግብ በማድረግ የመማር ማስተማሩ ሂደት ግቡን እንዲመታ የክፍል ደረጃ ተወስኖለት መርሀ ትምህርቱን መሠረት ያደረጉ ይዘቶችን የያዘ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም በመማር ማስተማሩ እንቅስቃሴ ትምህርቱን በቅድና በተገቢ ሁኔታ እንዲተላለፍ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ ነው፡፡

Ur (2006፡183) እንደገለፁት የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አንድን የትምህርት አይነት ጥቅል ይዘቶችን የያዘ ጥራዙ ነው፡፡ ይህም ጥራዝ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች ቅጂው የሚደርሳቸው ሲሆን መምህሩና ተማሪው ተገቢውን መርሀ እንዲከተሉ የሚያደርግና ለቋንቋ ትምህርት መሠረት የሆነ የማስተማሪያና የመማሪያ መሣሪያ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ Allwright (1981) እንደገለፁት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተማሪዎች ለትምህርት የቀረበውን ቋንቋ በራሳቸው እንዲማሩ የሚያስችሉ መምሪያዎች ከመሆናቸውም በላይ መፃህፍቱ ተማሪዎቹ መማር ያለባቸውን የትምህርት ይዘቶች፣ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ጭምር ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የትምህርቱ ሂደት የተስተካከለ እንዲሆን ታስበው የተዘጋጁ ሲሆን በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ክንውን የመወሰን አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ በተጨማሪም እንደ Sheldon (1987፡ 1-3) አገላለፅ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ከአንድ የትምህርት ተቋም እስከ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ድረስ ላለው የቋንቋ ትምህርት ሂደትና ፍላጎት በተገቢው ምላሽ ለመስጠት በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲና በመርሀ ትምህርቱ መሠረት የትምህርት ይዘቶቹ በሙያው በተካኑ ባለሙያዎች አማካኝነት ተዘጋጅተው ለቋንቋ ትምህርት

አላማ ግብ መምታት የሚቀርቡ ሰነዶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የመማር ማስተማሩን ሂደት በተሟላ ሁኔታ እንዲከናወን ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

ተስፋዬ (1981፣ 89) "የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚባሉት ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ወይም የተመደቡ ብቻ ናቸው፡፡ ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ለአንድ የተወሰነ ክፍል እንዲያገለግሉ ስርአተ ትምህርቱን ወይም የክፍሉ ተማሪዎች ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ችሎታ መሠረት በማድረግ ለማስተማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ ናቸው"፣ በማለት ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አገላለፅ የምንረዳው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት መርሀ ትምህርቱንና የተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት አድርገው ከሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል በዋናነት የሚመደቡ መሆናቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለተማሪዎች ቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁ መሆናቸውን እና እንዲሁም ከሌሎች መፃህፍት በተሻለ ሁኔታ መልመጃዎችን፣ ጥያቄዎችንና ምሳሌዎችን አካተው በመያዝ ለተማሪዎች ስለቀረበው የቋንቋ ትምህርት የተለያዩ ተግባራትን በመስጠት እንዲለማመዷቸው በማድረግ የሚያደርጉት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ለመምህሩም ምን እንደሚያስተምር እና እንዴት እንደሚያስተምር አቅጣጫ የሚጠቁሙ በመሆናቸው ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ወሳኝ መማሪያና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

### 2.1.1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚኖሩ ክንውኖችን፣ ይዘቶችንና የማስተማር ዘዴዎችን ለመምረጥና ለመተግበር የመነሻ መሰረቶች ናቸው፡፡ Behar (1994፡13) እንደገለፁት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አንድን ይዘት በተቀናጀ፣ ቅደም ተከተሉን በጠበቀና በተጠየቀው መንገድ በማቅረብ መምህራን ይህን የአካሄድ ቅፅ ተከትለው እንዲያስተምሩ ያግዛሉ፡፡ ለመምህራንና ተማሪዎችም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

- በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ተመሳሳይ ይዘት እንዲቀርብላቸው ያግዛሉ፣
- አንድን የተነደፈ አላማ ለማስፈፀም ስልታዊ በሆነ መንገድና በተደራጀ ቅፅ ለማዘጋጀት ያስችላሉ፣
- ለመምህራን አጠቃላይ ትምህርቱን የማስተማር እቅድ ለመንደፍ እንደ ቢጋር ሆነው ያገለግላሉ፣

- ለመምህራን፣ እንደተዘጋጀ ቅፅ በማገልገል ለትምህርቱ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን እንዲያዘጋጁ ይረዷቸዋል፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለቋንቋ ትምህርት አላማ ግብ መምታት ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደ Richards and Rodgers (1986: 24-26) Sheldon (1987:7-8) አገላለፅ የአንድን ህብረተሰብ እድገት የኑሮ ሁኔታ፣ ባህል ፍላጎትና እምነት ወዘተ. ባገናዘበ መልኩ የሚዘጋጁ የቋንቋ ማስተማሪያ መፃህፍት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይሰጣሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በትምህርቱ ሂደት ለሚታየው እንቅስቃሴና ለሚጠበቀው ውጤት የጎላ ሚና አላቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ፣ በተማሪው፣ በባለሙያውና በህብረተሰቡ ዘንድ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ተፈላጊነታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ተስፋዬ (1981፣93) የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አስፈላጊነት በሚከተለው መልኩ ይገልፁታል፤

1. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለመምህሩ የትምህርቱን ቅደም ተከተል በመወሰንና በማቅረብ፣ መነሻውንና መድረሻውን በመጠቀምና ምን ማድረግ እንዳለበት በማመላከት ትምህርቱን ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲያስተምር እገዛ ያደርጋሉ፤
2. የተለያዩ ጉዳዮችን በማቅረብ፣ የሚያስደስቱ መልመጃዎችን የሚፈፀሙ ስራዎችን በመወሰን፣ ተማሪው የተማረውን በተግባር እንዲገልፅ እድል በመስጠት፣ አስተማሪውም ሆነ ተማሪው ሊገነዘቡት የሚችሉትን ይዘት በማቅረብና ለንባብ የሚቀርቡትን ምንባቦች በቃላት ብቻ ሳይሆን በልዩ ልዩ ስዕሎች፣ ቻርቶች፣ ግራፎች፣ ፎቶ ግራፎች፣ ወዘተ. አጅቦ በማቅረብ ትምህርቱ አስደሳች እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡
3. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ትክክለኛና ተገቢ የቋንቋ አጠቃቀም ስልትን የሚይዙ በመሆናቸው በቋንቋ ትምህርት ሂደት ከስህተት የራቀ የቋንቋ ትምህርት ይዘትን በማቅረብ የመማር-ማስተማር ሂደቱን ያግዛሉ፤
4. የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በቋንቋ ትምህርት ዘርፎች መካከል ያለውን ቅንጅት አጥጋቢ በሆነ ስልት ለማጣመር ያግዛሉ፤ ይህም የቋንቋውን ክሂሎች በተመጣጠነ ደረጃ ለማስተማር ከማገዛቸው በላይ የቃላት አመራረጥን፣ የአገባብ ስርአትን የስርአተ ነጥብ አጠቃቀምን፣ የአፃፃፍ ውበትን ወዘተ. የሚያጠቃልሉ በመሆናቸው ጉልህ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

5. ተማሪውንም ሆነ መምህሩን የሚያነቃቁ መሆናቸው፣ በየደረጃው የተፈፀመ ተግባር መኖሩን ማመልከታቸው፣ የመምህሩን የማስተማር ዘዴ ማገዛቸው፣ ወዘተ. ዋና ዋናዎቹ የአገልግሎታቸው መገለጫዎች ናቸው፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ባገናዘበ መልኩ በአግባቡ የተመረጡና የተደራጁ ይዘቶችን በማካተት፣ በተለያየ ሁኔታና ቦታ ለሚማሩ ተማሪዎች በጋራ እንዲገለገሉባቸው ታስበው የተዘጋጁ በመሆናቸው ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

## 2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አይነቶች

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት አይነቶች እንደ ዘመኑ ፍልስፍና እንደየ ስርአተ ትምህርቱና የመማር ማስተማሩ አላማ የተለያዩ ናቸው፡፡ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በሀገራችንም ሆነ በሌላው አለም ብዙ ዘመናትን አስቆጥሯል፡፡ ለዚህም ከውጭው አለም የላቲንና የግሪክ ቋንቋ እንዲሁም ከሀገራችን የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት መጥቀስ ይቻላል (አለም 1995)፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ተብለው ቢዘጋጁም በይዘታቸው ግን የተለያዩ እንደሚሆኑ ከተለያዩ ምሁራን ገለፃ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍቱ ከሚከተሉት ስነ ዘዴ የትምህርት ይዘት ከተማሪዎች አንፃር ልዩነት ይኖራቸዋል፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍቱ በቅርፅ በአደረጃጀት፣ በይዘት፣ በፀሐፊና በአሳታሚ ድርጅቶች የተነሳ የተለያዩ ናቸው (Dighton 1971፡ 97-98)፡፡ እንደ Sheldon (1987:1-2) አመለካከት የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለአጭር፣ ለረጅም ጊዜና ለጥልቅ ጥናት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ምሁራን የተለያዩ የመማሪያ መፃህፍት አይነቶች መኖራቸውን ይገልፃሉ፡፡ ከእነዚህ ምሁራን መካከል Grant (1987:12) የቋንቋ መማሪያ መፃህፍትን በሁለት ይመድባሉ፡፡ እነርሱም ልማዳዊ የቋንቋ የመማሪያ መፃህፍት (Traditional textbooks) እና ተግባቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት (Communicative textbooks) በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡ የሁለቱን መማሪያ መፃህፍት ዝርዝር ባህሪ ቀጥለን እንመልከት

### 2.1.2.1 ልማዳዊ የመማሪያ መፅሐፍ

ልማዳዊ የመማሪያ መፃህፍት የሚባሉት ተማሪዎቹ ሲማሩ ቀላል ሆነው ትምህርቱ ሲጠናቀቅ ግን ተማሪዎቹ ስለቋንቋ አጠቃቀም በቂ የሆነ እውቀት ሳይዙ ትምህርቱን

እንዲያጠናቅቁ የሚያደርጉ መፃህፍት ናቸው። በእነዚህ መፃህፍት የሚማሩ ተማሪዎች የቋንቋውን የሰዋስው ስርአት ሊያውቁ ቢችሉም በቋንቋው ግን የሚፈለገውን ደረጃ ያህል መግባባት ይሳናቸዋል (Grant 1987:13)።

እንደ ምሁሩ ገለፃ ልማዳዊ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ዋና ትኩረታቸው ተማሪዎች ከሁሉም ቅድሚያ የቋንቋውን ስርአት እንዲማሩት ማድረግ ሲሆን ስርአቱን ከተማሩ በኋላ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያስችላቸው ችሎታ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታመንበት ነው።

በተጨማሪም ልማዳዊ የመማሪያ መፃህፍት የሚከተሉትን ባህሪያት በከፊል ወይም በሙሉ ሊያሟሉ እንደሚችሉ አክለው ይገልፃሉ። እነርሱም ከቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባራት ይልቅ በቅርፅ፣ በስርአት፣ በሰዋስው ወዘተ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፤ ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች በበለጠ ለንባብና ለፅህፈት ክሂሎች አፅንኦት ይሰጣሉ። ቋንቋውን ከማመንጨት ይልቅ ለአጠቃቀም ትክክለኛነት ቅድሚያ ይሰጣሉ። በፈተናዎች ላይ ያተኩራሉ። ለአጠቃቀምና ለፈተና ዝግጅት አመቺ ስለሆኑ በቋንቋ መምህራ ይወደዳሉ።

በአጠቃላይ በዚህ ገለፃ መሠረት ልማዳዊ የመማሪያ መፃህፍት በተማሪዎች የቋንቋ ልምምድ ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ የቋንቋውን ስርአት ማሳወቅ ላይ ያነጣጠሩ ናቸው። በዚህም የተነሳ ተማሪዎች በቋንቋው በበቂ ሁኔታ ለመገልገል ከመሞከር ይልቅ ስርአቱን ለማወቅ ብቻ ጥረት ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ ለቋንቋ ትምህርት አላማ ከግብ መድረስ የራሱ አሉታዊ ተፅኖ የሚያሳድር ነው።

### 2.1.2.2 ተግባቦታዊ የመማሪያ መፅሐፍ

ተግባቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ የመማር አጋጣሚዎችን በመፍጠር በቋንቋው መግባባት የሚችሉበትን ሁኔታ የሚፈጥሩ ናቸው። አብይ ትኩረታቸውም ቀደም ሲል በተጠቀሱት ልማዳዊ የመማሪያ መፃህፍት ላይ የታዩትን ድክመቶች መቅረፍ ሲሆን ተማሪዎች በእለት ተዕለት ህይወታቸው ቋንቋውን ሊጠቀሙበት በሚያስችላቸው መልኩ እንዲለማመዱ ያበረታታል። ተግባቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ሁነቶች ታሳቢ በማድረግ በክፍል ውስጥ የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር ለተማሪዎቹ የቋንቋ ብቃት ማደግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው (Grant 1987:13-14)።

እንደ ምሁሩ አገላለፅ ተግባቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት ከልማዳዊ መማሪያ መጽሐፍት በበርካታ ጉዳዮች ይለያሉ፡፡ ከእነዚህም የመጀመሪያው ተግባቦታዊ የመማሪያ መፃህፍት አብይ ትኩረቱ በተግባቦታዊ ተግባራት ላይ ነው፡፡ ይህ መፅሐፍ ከቋንቋው ህግጋት ይልቅ ተማሪዎች ቋንቋውን እየተጠቀሙበት ስራቸውን እንዲሰሩ ያደርጋል፤ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማንፀባረቅ ጥረት ያደርጋሉ፤ ከቋንቋው ሰዋስው ይልቅ ለክሂሎች አፅንኦት በመስጠት በአገልግሎት ላይ በሚውሉበት ሁኔታ ላይ ያተኩራል፤ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ሚዛናዊ ተግባራት ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆኑ ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የተለየ ቦታ ይሰጣሉ፡፡ የቋንቋ ይዘቶቹም ሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎቹ በቋንቋው የእለት ተዕለት አገልግሎት ላይ ያተኩራሉ፡፡ በመምህራን የክፍል ውስጥ አደረጃጀት ብቃት ላይ ተመስርተው ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን በመሆን ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እያከናወኑ እንዲማሩ ያበረታታሉ፡፡ ከቋንቋ አጠቃቀም ትክክለኛነት ይልቅ ለሀሳብ አፍልቆትና ፍሰት ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡

በአጠቃላይ ተግባቦታዊ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ አዘገጃጀቱ ወደ ተግባር የሚያተኩር ሆኖ ከፍተኛ ትኩረቱ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ መግባባት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ከቅርብ አመታት ወዲህ ከፍተኛ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ሲሆን በከፍተኛ ደረጃም ስራ ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡

### 2.1.3 የመማሪያ መፃህፍት ባህሪያት

ከቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የመማሪያ መፃህፍት ነው፡፡ ለተወሰኑ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ እንዲሆኑ ታስበውና ሆን ተብለው የሚዘጋጁ መፃህፍት በሚዘጋጁበት ወቅት የሚከተሉትን ባህሪያት አሟልተው እንዲይዙ ይጠበቅባቸዋል (ተስፋዬ 1981፣ 94-95)፡፡

**እውነተኛነት** ለትምህርት የቀረበው የቋንቋ አካል እውነት የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ የሚለው መሆን አለመሆኑን የሚዳኝበት ነው፡፡ ተማሪው እንዲማር የሚቀርብለት፣ እንዲለማመደው የሚያደርገው የቋንቋ አካል ቋንቋውን ይበልጥ የሚያሳውቅ በቋንቋው ይበልጥ የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድር መሆን አለበት፡፡

**ግልፅነት** የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ የያዟቸው የትምህርት ጉዳዮች መምህሩ እንዲያስተምር ተማሪው እንዲማር ለማገዝ በግልፅ መስፈር አለመስፈራቸው የሚመዘንበት

ነው። ግንዛቤ እንዲገኝባቸው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ጉዳዮች ምንነታቸው በማያሻማ ስልት እንዲቀርብ ያስፈልጋል።

**ተለጣጣቂነት** በአንድ መፅሐፍ ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከልም ሆነ ለተለያዩ ክፍሎች በተዘጋጁ መፃህፍት መካከል ተለጣጣቂነት የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው። ተማሪው ቀጥሎ የሚደርስበት ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ያለፈውን የሚደግም ከሆነ ግን እድገት ወይም አዲስነት የለበትምና መሰልቸት ይከተላል።

**ተግባራዊነት** ተግባራዊነት መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪው እንዲማር የሚያግዝ መሳሪያ የመሆኑ ጉዳይ ነው። የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሳሪያ የያዘው የትምህርት ይዘት በተማሪው ተግባራዊ የሚደረግ መሆን ይኖርበታል።

**ተገቢነት** የተገቢነት ጉዳይ የማስተማሪያ መሳሪያው በይዘቱ ለተማሪዎች ደረጃ ለተማሪዎች እድሜ ለተማሪዎች ችሎታና ለተማሪዎች ፍላጎት የሚመጥን መሆን እንዳለበት የሚያመላክት ነው። ለትምህርቱ ሂደትም ቢሆን የማስተማሪያ መሳሪያው ብቃት የሚታየው በዚሁ ዘርፍ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው በየትኛውም የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚዘጋጁ የመማሪያ መፃህፍት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ባህሪያት መኖራቸውን ነው። ይህን ከቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከት በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚቀርቡ የቋንቋ አካላት በተናጋሪው ህብረተሰብ ዘንድ እውነትነታቸው የተረጋገጠ መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ይዘቶቹ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ መሆናቸውን በግልፅ ቋንቋ መቅረባቸው ጭምር አብሮ ይታያል። ሌላው በመፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች በስፋትና በጥልቀት ከፍ እያሉ መሄድና ይዘቶቹም በመምህሩና በተማሪዎቹ መተግበር መቻል ይኖርባቸዋል።

## 2.1.4 የንባብ ምንነት

ንባብ ምንድነው?ስንል የተለያዩ ምላሾች ይሰጣሉ። እንደ Goodman (1970: 260) ገለፃ ንባብ በፅሁፍ ከቀረበ መልዕክት ውስጥ አንባቢው የሚፈልገውን ብቻ እየመረጠ ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ተግባር ነው። ንባብ በአንድ ፅሁፍ አማካኝነት የሰፈረውን መልዕክት መረዳት እና ማገናዘብን ይመለከታል። እንዲህ ስለተባለ ግን መልዕክቱ በፅሁፍ አማካኝነት

በቀላሉ ሰፍሮ የሚገኝ አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡ የሰፈረውን መልዕክትም ለመረዳት የአንባቢን ንቁ የአዕምሮ ተሳትፎ ይጠይቃል በማለት የገለፁት አለም (1997፣2) ናቸው፡፡

እንደ May (1990፡10) አገላለፅ የንባብ ምንነት ከተለያዩ ነጥቦች አንፃር ሊገለፅ ይችላል ይኸውም፡-

- ንባብ በፅሁፍ የቀረበውን ሀሳብ የመረዳት ሂደት ነው፡፡
- ንባብ የመተርጎም፣ ፍቺ የማፈላለግና በፅሁፍና በስዕል የቀረቡ መልእክቶችን ወደ ግል ግንዛቤ የመተርጎም ሂደት ነው፡፡
- ንባብ አንባቢው በፅሁፍ ከቀረቡ ቃላት ጋር የሚያደርገው ጭውውትም ሊሆን ይችላል፡፡ ማለትም አንድን ጽሁፍ ለመረዳት በሚደረግ ሂደት አንባቢ ከቃላት ጋር በመነጋገር በመጫዋወት የፀሐፊው ሀሳብ ይህ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡

በተጨማሪም Harmer (1991)፣ Sheng (2000) ንባብ ከተቀባይ ክሂሎች ውስጥ የሚካተት ሲሆን ከምናነበው ፅሁፍ ውስጥ ቁም ነገሩን ነቅሶ ማውጣትን፣ የምንባቡን ዝርዝር ሀሳብ መረዳትን መቀበልና ማስተላለፍ፣ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ መረዳትን ወዘተ አጠቃሎ የያዘ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ይህም ንባብ በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የቀረበን ፍሬ ነገር አንብቦ ለመረዳት የሚደረግ ጥረት መሆኑን ያመለክታል፡፡

እንዲሁም Grellet (1981፡8) "ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከር፣ ራስን ጥያቄ መጠየቅንና ንቁ ተሳትፎ ማድረግን የሚፈልግ ሂደት ነው"፡፡ በሂደቱም አንባቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላት ፍቺዎችን የሚገምትበት ገና ከመነሻው ባገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ ያነበበውን ፅሁፍ መረዳት አለመረዳቱን ራሱን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለን፡፡ በሌላ በኩል የተለያዩ ምንባቦችን ሲያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን፡፡

በተጨማሪም ንባብን በሶስት የተለያዩ ደረጃዎች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል Nuttal (1996)ን በመጥቀስ አለም (1997፣ 3) የሚከተሉትን ነጥቦች አስፍረዋል፡፡

ሀ. መነጠል፣ መለየት፣ መቁጠር (ለፊደል ወይም ለምልክት)

ለ. ከአንደበት ማፍለቅ፣ ንበት፣ የድምጽ አፈላለቅ፣ መናገር ወዘተ.

ሐ. መረዳት፣ መገንዘብ፣ ትርጉም መጨበጥ፣ ስሜት መከተል ወዘተ.።

ከነዚህ ደረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው ንባብ የመለየትን፣ ከአንደበት የማፍለቅን፣ የመገንዘብን የመተርጎምንና ሌሎች ሂደቶችን አጠቃሎ የሚይዝ ተግባር እንደሆነ ነው።

በአጠቃላይ ስለ ንባብ ምሁራን ወጥ የሆነ ብያኔ ያልሰጡበት ምክንያት ከንባብ ባህሪ የመነጨ እንደሆነ Alderson (1984፡1) ይገልፃሉ። ይኸውም የንባብ ተግባር ግላዊና ረቂቅ መሆን ነው። ይህ እንዲሆን ያደረገው የተለያዩ አንባቢዎች አንዱን ፅሁፍ የሚረዱበት መንገድ፣ የሚያነቡበት አላማና የአነባበብ ዘዴያቸው የተለያየ መሆን ነው። ንባብ ማለት ለአንዱ የሚፈልገውን መረጃ ብቻ ነቅሶ ማውጣት ሲሆን ለሌላው ደግሞ መልዕክቱን በዝርዝር መገንዘብ ይሆናል። እንዲሁም ንባብ ፀሀፊው ላስተላለፈው መልዕክት አንባቢ ምላሽ የሚሰጥበት ተግባር የሚሆንበት ሂደትም አለ።

## 2.1.5 ለምን እናነባለን?

ለምን እናነባለን? የሚለውን ጥያቄ ተከትሎ የሚመጣው ነጥብ የምናነብበት አላማ ምንድነው? የሚለው ይሆናል። እያንዳንዱ አንባቢ በፅሁፍ የቀረቡ መልዕክቶችን የሚያነብበት የራሱ የሆነ አላማ ይኖረዋል። ንባብ ከሚከናወንባቸው አላማዎች ውስጥ የተወሰኑትን ለመግለፅ ያህል ትምህርት ነክ ጉዳዮችን አንብቦ ፈተና ለማለፍ፣ ለጠቅላላ እውቀት፣ አስተያየት ለመሰንዘር፣ ስለአለማችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣ የአስተሳሰብ አድማስን ለማስፋት፣ ለመዝናናት፣ መፍትሔ ለማግኘት፣ ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል። Harmer (1995፡18) የንባብ አላማ እንደሚነበበው የፅሁፍ አይነትና እንደ አንባቢው ፍላጎት የተለያየ ነው ይላሉ።

ሌላው አንድን ፅሰሁፍ ለማንበብ የምንፈልግባቸው የተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ። ጥቂቶቹን ለመግለፅ ራሳችንን ከአደጋ ለመከላከል ስንል የማስጠንቀቂያ መልዕክቶችን እናነባለን። ከነዚህም ውስጥ የተከለከሉ ቦታዎችን የሚገልፁ መግባትና መውጣት ወይም ማለፍ ክልክል መሆኑን የሚያመለክቱ የነገሮችን መርዛማነትና አደገኛነት የሚገልፁና የተለያዩ ቅጣቶችን ሊያስከትሉ የሚችሉ የማስጠንቀቂያ ፅሁፎችን መጥቀስ ይቻላል (አለም 1997፣6-7) ፀሐፊው ጨምረው እንዳብራሩት ለምን እናነባለን የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ ምሁራን የጠቀሷቸው የንባብ አይነተኛ አላማዎች መረጃ ለማግኘት፣ ለመግባባት፣ ጥሩ ተናገሪና ፀሐፊ ለመሆን ለትርጉም ስራና ስነጽሁፋዊ ሂስ ለማቅረብ የሚሉት ናቸው።

## 2.1.6 ምን እናነባለን?

ምን እናነባለን? ስንል የምናነብበት አላማም ተያይዞ ሊነሳ ይችላል። ለምሳሌ ተማሪ ምን ያነባል ስንል ፈተናውን በሚገባ ሰርቶ ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚያስችለውን ማስታወሻ የያዘበትን ደብተሩን፣ መማሪያ መፅሐፉንና የሚያነበውን የትምህርት አይነት የሚመለከቱ አጋዥ መጽሐፍት እንደሚሆን ይገመታል።

እንደ Gunning (2006) ገለፃ የምናነበው ነገር እንደምናነብበት አላማና እንደ ፅሁፍ አይነት የተለያየ ነው። ከነዚህም ጥቂቶቹ ጋዜጦች፣ መጽሄቶች፣ ልብወለዶች፣ ግጥሞች የምርምር ስራዎች፣ ማስታወቂያዎችና የፍልስፍና ፅሁፎችን መጥቀስ ይቻላል። እያንዳንዱ አንባቢ እነዚህን የተዘረዘሩትን የተለያዩ መረጃ ሰጪ ፅሁፎች ሲያነብ የሚነሳው የሚፈልገውን መረጃ ለማግኘት አለበለዚያም ለማግኘት የፈለገውን እውቀት መሠረት አድርጎ ነው።

## 2.1.7 እንዴት እናነባለን?

ለምን አላማ እንደምናነብ ከለየንና ምን እንደምናነብ ካወቅን በኋላ የምንፈልገውን መረጃ ለማግኘት የምናነበውን ፅሁፍ እንዴት እናነባለን? የሚለው ጥያቄ በቀጣይ የሚነሳ ይሆናል። ይህ ጥያቄ ሲነሳ ፅሁፉን በፍጥነት ነው? በዝግታ ነው? የምንፈልገው መረጃስ ነጠላ መረጃ ነው? ዝርዝር ነጥቦችን ለማግኘት ነው? የሚሉ ተያያዥነት ያላቸው ነጥቦች ይነሳሉ። ለዚህም አብዛኛውን ጊዜ ስራ ላይ የሚውሉና የሚታወቁ አራት መሠረታዊ የንባብ ስልቶች አሉ። እነርሱም የገረፍታ ንባብ፣ የአሰሳ ንባብ፣ ሰፊ ንባብና ጥልቅ ንባብ ናቸው (Nuttal 1982፣ Cushenbery 1985፣ Aebersold and Field 1997)። ፀሐፍቱ ያሰፈሯቸውን ነጥቦች አንድ በአንድ በዝርዝር እንመልከት።

### 1. የገረፍታ ንባብ (Skimming)

የገረፍታ ንባብ ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ሲባል በቅኝት መልክ ገረፍ ገረፍ አድርጎ በመመልከት የሚከናወን የንባብ አይነት ነው። በገረፍታ ንባብ በፅሁፍ ውስጥ ያሉ ዝርዝር መረጃዎችን ለማወቅ ጥረት አይደረግም። የንባቡ ዋና አላማ የአጠቃላይ ፅሁፉን ፍሬ ነገር መጨበጥ ስለሆነ ፈጠን ባለ መልክ የሚከናወን ነው። ለምሳሌ :- የማስታወቂያን አጠቃላይ መልእክት ወይም በራሪ ወረቀቶች ላይ የሰፈረን ሀሳብ አብዛኛውን ጊዜ በገረፍታ ንባብ ይቃኛል። ይህም የሚሆንበት የመረጃው ጠቃሚ መሆን አለመሆኑን

ለመለየት የሚከናወን ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ የጽሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ ካገኘን በኋላ ወደ ሌላ የንባብ አይነት ልንሸጋገር እንችላለን ወይም ንባባችንን ልናቋርጥ እንችላለን፡፡

### 2. የአሰሳ ንባብ (Scanning)

የአሰሳ ንባብ እንደ ገረፍታ ንባብ በፍጥነት የሚከናወን ቢሆንም አላማው ግን የተለየ ነው፡፡ የአሰሳ ንባብ ዋና አላማ የፅሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ መገንዘብ ሳይሆን ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚፈለግ ቁንፅል መረጃ ነጥሎ ለማውጣት የሚከናወን የንባብ ተግባር ነው፡፡ በአሰሳ ንባብ የፅሁፍን እያንዳንዱን ቃል ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ማንበብ አይጠበቅብንም፡፡ ነገር ግን አይንን በፍጥነት በማንቀሳቀስ የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት ጥረት ይደረጋል፡፡ መረጃው ከተገኘ በኋላም ቀሪውን ጽሁፍ ላናነብ እንችላለን፡፡ በዚህ ንባብ ከቁጥር ጋር የተያያዘ የቦታና የሰው ስሞችን ወዘተ. ከአንድ ምንባብ ውስጥ አስሶ በፍጥነት ለማግኘት ሲባል የሚተገበር የንባብ አይነት ነው፡፡

### 3. ሰፊ ንባብ (Extensive Reading)

ሰፊ ንባብ ሰፋ ያለ ጊዜን የሚጠይቅ ሲሆን አላማውም በሚነበበው ጽሁፍ እየተዝናኑ ቁም ነገርን ለመቅሰም ነው፡፡ ይህ ንባብ እንደ ገረፍታና አሰሳ ንባብ በፍጥነት የሚከናወን ሳይሆን እርጋታን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ንባብ አብዛኛውን ጊዜ ተግባር ላይ የሚውለው ረጅም ልብ ወለዶችንና የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን በምናነብበት ጊዜ ነው፡፡

### 4. ጥልቅ ንባብ (Intensive Reading)

ጥልቅ ንባብ በተለምዶአዊ የንባብ ፍጥነት የሚከናወን ነው፡፡ የጥልቅ ንባብ አላማ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ የተወሰኑ ሀሳቦችን በጥልቀት መረዳት ነው፡፡ በዚህ የንባብ አይነት አንባቢው የፀሐፊውን እምነት፣ የጽሁፉን አንድምታና አጠቃላይ የጽሁፉን አላማ በጥልቀት መመርመር ነው፡፡ ይህ የንባብ ስልት የምርምር ፅሁፎችንና አዳዲስ ግኝቶችን በጥልቀት ለማወቅ ስንፈልግ ተግባር ላይ የሚውል የንባብ ስልት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የንባብ ስልቶች እርስ በርሳቸው ተደጋጋፊነት እንዳላቸው ፀሐፍቱ ይገልፃሉ፡፡ አንድ አንባቢ አንድን ጽሁፍ ሲያነብ የገረፍታን፣ የአሰሳን፣ ጥልቅና ሰፊ ንባብን ብቻ ነጥሎ ሊያነብ ይችላል፡፡ ነገር ግን በጥልቅ ንባብ ውስጥ የገረፍታን ወይም የአሰሳ ንባብን

ሊጠቀም ይችላል። በሌሎቹ ውስጥም በተመሳሳይ አንዱን ከሌላው ቀይጦ የሚጠቀምበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

በአጠቃላይ ስለ አንብቦ መረዳት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ቢሰጡም የአብዛኞቹ ግን አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ያለን ሀሳብ መገንዘብ መቻል መሆኑን ይስማማሉ። ምናልባት የእያንዳንዱ አንባቢ የአረዳድ ሁኔታ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰው የሚፈልገውን መረጃ አንብቦ መገንዘብ ከቻለ አንብቦ መረዳት ማለት ከዚህ የተለየ አይደለም።

## 2.1.8 የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ፈልቅቆ ማውጣትን የሚይዝና ጽሁፍን የመገንዘብ ሂደት ነው። አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈልገውን መረጃ የሚወስድበት የማይፈልገውን የሚለይበት እና ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤ የሚያመላክት ነው (Smith 1985፡ 14፣ አለም 1995፡ 11፣ Williams 1990፡ 3)። እንደ Green Wood (1981፡ 89) አገላለፅ አንብቦ መረዳት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መገንዘብ ነው። በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ያለን መልዕክት ለመረዳት የእያንዳንዱን ቃል ፍቺ ማወቅ የግድ አይሆንም። በጽሁፉ ውስጥ በግልፅ የተቀመጠውን መልዕክትና መልዕክቱን ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ጉዳዮች መረዳት ግን ወሳኝ ነው። ይህም ሲባል አንባቢ በግልጽ የተቀመጠው መልዕክት ላይ ብቻ ተወስኖ መቅረት አለበት ማለት ሳይሆን በግልጽ የተቀመጠውን መልዕክት መነሻ በማድረግ በመመርመር የሚደረስበትን ስውር መልዕክትም መረዳት ይጠበቅበታል። በዚህን ጊዜ ከጽሁፉ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ አገልግሎት እና ፍቺ መረዳት የግድ ነው፡፡ በተጨማሪም የምንባቡን ቅደም ተከትላዊ የሀሳብ አገላለጽ በፅሁፉ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አንቀጾች ያላቸውን የእርስ በርስ ቁርኝት መረዳት ተገቢ ነው፡፡

አንብቦ መረዳት አንድን ጽሁፍ ቅደም ተከተላዊ የሀሳብ አገላለጽ፣ የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር ከቀጣዩ ጋር ያለውን የሀሳብ ግንኙነት እና ግጥምጥምነት የሚከውኑ አያያዦች የፀሐፊው ሀሳብ የሚንፀባረቅባቸው በመሆናቸው ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው (Nuttal 2000 :28)፡፡ አንብቦ መረዳት ማለት በአንድ በቀረበ ጽሁፍ ወይንም ምንባብ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ መረጃዎችን መገንዘብ ማለት ነው፡፡ በእርግጥ የአንብቦ መረዳት ደረጃ ሊለያይ ይችላል፡፡ ይህም ከሚነበበው ነገር፣ ከሚነብብለት ዓላማ፣ ከአነባብ ዘዴው መለየት ሊከሰት ይችላል ለምሳሌ አንድ ማስታወቂያና አንድ ሳይንሳዊ ጥናት በተመሳሳይ መንገድ

አይነበቡም፡፡ የማስታወቂያው መልዕክት በገረፍታ ሊደረስበት ሲቻል የሳይንሳዊው መልዕክት ለመረዳት ግን ጥልቅ ንባብ ያስፈልገዋል፡፡

በአጠቃላይ ስለ አንብቦ መረዳት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ ቢሰጡም የአብዛኞቹ ግን አንብቦ መረዳት በአንድ ፅሁፍ ውስጥ ያለን ሀሳብ መገንዘብ መቻል መሆኑን ይስማማሉ፡፡ ምን አልባት የእያንዳንዱ አንባቢ የአረዳዱ ሁኔታ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው የሚፈልገውን መረጃ አንብቦ መገንዘብ ከቻለ አንብቦ መረዳት ማለት ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

## 2.1.9 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከቀደምት ጊዜያት እስካሁን በስፋት ሲሰራባቸው የቆዩ አብዛኛውን ጊዜ ከምንባብ ቀጥሎ የሚመጡና የሚነበበውን ፅሁፍ መሠረት አድርገው የሚዘጋጁ ጥያቄዎች እንደሆኑ Nuttal (1988፡125) ያስረዳሉ፡፡

እንደ Shin (1992፡ 290) ገለፃ ቋንቋን ለማስተማር አላማ ያደረገ የንባብ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መመለስ እንዲያስችላቸው መምህራን በቅድመ ንባብ ተግባራት ዳራዊ እውቀታቸውን እንዲፈትሹ መንገዶችን ያመቻቻሉ፡፡ ለደረጃው የሚዘጋጁ የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍትም ይህንኑ መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም በቅድመ ንባብ ደረጃ የተማሪውን ዳራዊ እውቀት የሚፈትሹ፣ በንባብ ጊዜ አጫጭር ማስታወሻዎችን እንዲያዝ የሚያዙ በድህረ ንባብ ጊዜ ውይይቶችን የጽሁፍ ተግባራትን ሌሎች ክሂሎችን አጠቃለው የሚይዙ ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች መሠረታዊ የሆኑ በይዘት ላይ ያተኮሩ መልመጃዎችን በምን መልኩ እንደሚሰጥ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል፡፡

ሌላው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የአንድን ፅሁፍ አጠቃላይ መልእክት ለመገንዘብ ከተለያዩ አተያዮች አንጻር ለመመርመር የሚዘጋጁና የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር መንገድ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡ እንደ Grellet (1991፡6-9) አገላለፅ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ ትኩረት ሊደረግባቸው ከሚገቡ በርካታ ነጥቦች መካከል በመሰረታዊነት የሚጠቀሱት ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመር፣ የጥያቄ ስብጥር መጠበቅ፣ ከልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀትና በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ናቸው በማለት ይገልፃሉ፡፡ እነዚህን ነጥቦች ቀጥሎ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

**ከአጠቃላይ ጭብጥ መጀመርን** በተመለከተ የአንብቦ መረዳት ጥያቄ በሚዘጋጁበት ጊዜ ሁልጊዜም ከምንባቡ አጠቃላይ ጭብጥና አላማ በመነሳት ወደ ዝርዝር ሀሳቦች ቢያመሩ ተመራጭነት ይኖረዋል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የአንድ ምንባብ አላማና ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት በመጀመሪያ በሚገባ ከተረዱ በተከታይ የሚመጡት ዝርዝር የቃላት የአገላለፅና ሌሎች ጥቃቅን ነጥቦችን ጥያቄ ለመመለስ ብዙ እንዳይደክሙ ስለሚረዳ ነው (Grellet 1991፡6)፡፡

**የጥያቄዎችን ስብጥር መጠበቅ** ሲባል ደግሞ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል ሌላው ነጥብ የጥያቄዎችን ስብጥር ተመጣጣኝ ማድረግ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ጥያቄዎቹ ምንባቡን ተከትለው የሚመጡ በመሆናቸው ለጥያቄዎቹ ምላሽ መስጠትና የንባብ ተግባርን ማከናወን ጎን ለጎን የሚሄዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚወጡት ጥያቄዎች የተለያዩ የንባብ አይነቶችን ለማዳበር የሚረዱ ስብጥር ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡ Grellet (1991፤9) እንደገለፁት የተለመዱና ምን ጊዜም ተደጋግመው የሚመጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አወንታዊም አሉታዊም ጎን አላቸው፡፡ ነገር ግን ጥያቄዎቹ ምን ጊዜም ተለዋዋጭነት (Flexibility) ያላቸውና ከጥያቄ አይነቶች የተውጣጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ከምንባብ የሚወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የምንባቡን አላማ የፀሐፊውን አመለካከት የአንባቢውን አረዳድና ሌሎችንም ነጥቦች የሚዳስሱ በመሆናቸው በተለያየ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በክፍት ጥያቄ (Open Ended) ምርጫ ሰጪ፣ በእውነት ሀሰት፣ በአዛምድና ሌሎች አይነት እየተሰባጠሩ ቢቀርቡ የተሻለ ይሆናል፡፡ ሌላው ጥያቄዎቹ እነዚህን የግድ ያካተቱ ማለት ሳይሆን ጥያቄዎቹ እንደ ምንባቡ ባህሪ ተለዋዋጭነት ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡

**ከልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር ማቀናጀትን** በተመለከተ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ከተለያዩ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማውጣት እንደሚቻል Grellet (1991፡ 4-5) ሲገልፁ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ መንገዶችን በማመቻቸት የተለያዩ ጥያቄዎችን ማውጣት ይቻላል፡፡ ጥያቄዎቹም ከምንባቡ አጠቃላይ አደረጃጀት ጀምሮ እስከ ዝርዝርና ግልፅ የተቀመጡ ይዘቶች ላይ ያተኩሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የጥያቄዎቹ አይነትና ተግባርም የተወሰኑ ክሂሎችን ከማዳበር ጋር የተቆራኘ መሆን ይኖርበታል፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የንባብ ክሂልን ብቻ ሳይሆን ሌሎችን የቋንቋ ክሂሎችንም ማዳበር አለባቸው፡፡ እንደ Grellet (1991) አገላለፅ አንብቦ መረዳት ከሌሎች ክሂሎች ተነጥሎ

ሊታይ አይችልም። ስለዚህ በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነት የሚከተሉትን ክሂሎች በማቀናጀት ማዳበር ይቻላል።

- **ንባብና ፅሁፍ፡-** በንባብ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች እግረ መንገዳቸውን ሊያዳብሩት ከሚጠበቅባቸው ክሂሎች አንዱ ጽሁፍ ነው። ይህንን ክሂል እንዲያዳብሩ በጥያቄዎቹ አማካኝነት ለተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን መስጠት የጽሁፍ ክሂልን እንዲያዳብሩ ይረዳል። ከተግባራቱ ጥቂቶቹ ማስታወሻ እንዲይዙ በማድረግ፣ አጭር ሀሳብን አስፍተው እንዲፅፍ፣ ምንባቡ የያዘውን ሀሳብ ባጭሩ እንዲፅፉ የሚያደርጉ መልመጃዎች የጽሁፍን ክሂል ከንባብ ክሂል ጋር አቀናጅተው እንዲያዳብሩ የሚያግዙ ናቸው።
- **ንባብና ማዳመጥ፡-** የማዳመጥ ክሂልን ከንባብ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር ተማሪዎች ዜናዎችን፣ ድራማዎችን፣ የተቀረፁ ንግግሮችን፣ እንዲያዳምጡ በማድረግና ከምንባቡ ጋር ተያያዥነት ያለውንና የሌለውን እንዲለዩ በማድረግ ንባብን ከማዳመጥ ጋር አያይዘው እንዲያዳብሩት ይረዳል።
- **ንባብና ንግግር፡-** ንግግርን ከንባብ ጋር በማቀናጀት የሚዘጋጁ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎች በነጠላም ሆነ በቡድን ሆነው ሊሰሯቸው የሚችሉ ናቸው። ይህንን ለማድረግ የሚከናወኑ ተግባራት፣ ለክርክር፣ ለውይይትና ለንግግር የሚጋብዙ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ በቡድንም ሆነ በነጠላ አንብበው እንዲዘጋጁ በማድረግ እንዲያቀርቡ ማድረግ ነው።

**በመልመጃ ጥያቄዎችና በፈተና ጥያቄዎች መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ** ሲባል አብዛኛውን ጊዜ የፈተና ጥያቄዎች በባህሪያቸው ትክክለኛ ምላሽን የሚሹና መልሳቸውም የተወሰነ ሲሆን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ግን ሊዳብር የተፈለገውን የቋንቋ ክሂል መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ የችሎታ ማዳበሪያ ጥያቄዎች በመሆናቸው የሚከተሉት ባህሪያት እንዳሏቸው ያብራራሉ (Grellet 1995፡9)።

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን በተደጋጋሚ እንዲያዩና ያገኙትን ቁምነገር በተለያየ መንገድ እንዲያንፀባርቁ የሚረዱ ናቸው እንጂ ትክክል ወይም አይደለም ብለው ለመገምገም የሚዘጋጁ አይደሉም።

- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሁልጊዜ አንድ ወጥ ምላሽ ላይኖረው ይችላል። ከዚያ ይልቅ ተማሪዎች በተለያየ መንገድ መልስ የሚሰጡበትን ሁኔታ እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ናቸው።
- ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀጥተኛ ምላሽ ከምንባቡ ላይገኝ ይችላል። የተማሪዎቹን አጠቃላይ ዳራዊ እውቀት መሰረት አድርገው በራሳቸው አተያይና አረዳድ አስተያየት መስጠት የሚችሉባቸው ጥያቄዎች ናቸው።
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስ የቃላት ክብደት እንደ ችግር ሊቆጠር አይገባም። በምንባቡ ውስጥ የሚገኙ አዳዲስ ወይም ከዚህ በፊት ባነበቧቸው ምንባቦች ውስጥ ያጋጠሟቸው ሆነው ከተገኙ የሚያነቡትን አዲስ ምንባብ ተመርኩዘው ምሁራዊ ግምት መስጠት ይችላሉ። ግምታቸው እንደ ስህተት ላይቆጠር ይችላል። ምክንያቱም አንብቦ መረዳት ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ የምንባቡን ሀሳብ በተቻላቸው መጠን ለመገንዘብ ጥረት የሚያደርጉበት በመሆኑ ነው (Cornish 1992፡ 26-27)።

ከላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ባህሪያትን አይተናል። ከዚህ በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የታለመውን ግብ እንዲመቱ ቀጥሎ በቀረቡት መሠረት መዘጋጀት እንዳለባቸው አለም (1995፣13) ያስረዳሉ፡-

1. ጥያቄዎቹ ምንባቡን ባላነበበ ሰው ሊመለሱ የሚችሉ ሊሆኑ አይገባም።
2. ጥያቄዎቹ ባንድ በተወሰነ የምንባብ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ ሁሉንም የምንባብ (የፅሁፍን) ክፍል በሚዳስሱበት መንገድ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል።
3. የጥያቄዎቹ ቁጥር እጅግም ሳይበዛ እጅግም ሳያንስ በቂ የሆነ መጠን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
4. የተለያዩ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ማቅረቢያ መንገዶች አሉ። ስለዚህም ጥያቄዎቹን በተለያየ አቀራረብ መንገድ ለማቅረብ መሞከር አስፈላጊ ይሆናል።
5. ጥያቄዎች አንድ አካባቢ ሊኖረው ከሚገባ የንባብ ስትራቴጂ ጋር የማስተዋወቅ ሐይል ሊኖራቸው ይገባል።
6. ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል።
7. ጥያቄዎቹ የተገለፁበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ ወይም የከበደ መሆን አይኖርበትም።

8. የጥያቄዎቹ መልሶች ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠየቅ የለባቸውም፡፡
9. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የተማሪውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉበት መንገድ እንጂ የተማሪውን ችሎታ የሚፈትኑ አይነት ሆነው መቅረብ አይኖርባቸውም፡፡
10. አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎቹ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበት መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከላይ በተገለፀው መልኩ በጥንቃቄ ከተዘጋጁ የተማሪው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍ እንዲልና የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹንም ለመስራት መነቃቃትን ይፈጥራሉ፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ማንበብ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክሂሎችንም ማዳበር እንዲችሉ ያግዟቸዋል፡፡

## 2.1.10 የአንብቦ መረዳት ጥያቄ አይነቶች

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በአይነት በአይነታቸው ለመከፋፈል በርካታ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል (Nuttal 1988:132)፡፡ ክፍፍሎቹ ግን ወጥ የሆኑ አልነበሩም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ክፍፍሉ የጥያቄዎቹን ይዘት መሰረት ያደረጉ ስለነበሩና በወቅቱ ደግሞ አዳዲስ ይዘቶች መቀያየራቸው ነው፡፡

እንደ Nuttal (1988፡133) አገላለፅ በስፋት የሚሰራባቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄ አይነቶችን የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1. ቀጥተኛ ጥያቄዎች

ቀጥተኛ ጥያቄዎች ከምንባቡ በቀጥታ ተወስደው ቃል በቃል ምላሽ የሚሰጥባቸውን ጥያቄዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ምላሾቹም የፅሁፍን ግልፅ መልእክት የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥያቄዎች አማካኝነት መላሹ በቀጥታ የፀሐፊውን ሀሳብ ያንፀባርቃል፡፡ አብዛኛውን ጊዜም ምንባቡ እንዳለቀ የሚመጡ ተከታታይ ጥያቄዎች የዚህ አይነት ባህሪ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ይህ ግን ሁል ጊዜ የሚከሰት ላይሆን ይችላል፡፡

2. ማገናዘብንና ማቀናበርን የሚጠይቁ ጥያቄዎች

እነዚህ የጥያቄ አይነቶች የምንባቡን ሀሳብ በቀጥታ ከመመለስ ባለፈ መልእክቱን የማገናዘብና የማቀናበርን ችሎታ ለማዳበር እንዲረዱ ታስበው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ ከበድ የማለት መንፈስ ቢኖራቸውም አንድ ወጥ ምላሽ የሚሰጥባቸው ሳይሆኑ የተለያዩ ተማሪዎችን የተለያየ የግንዛቤ ደረጃ የሚፈትሹ በመሆናቸው ነፃ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የምንባቡን ዋና መልእክት ፈልቅቆ በማውጣት የመገንዘብ፣ ሀሳብን ጨምቆ የማቀናበርና የመሳሰሉ ችሎታዎችን በዚህ የጥያቄ አይነት ሊዳብሩ የሚችሉ ናቸው፡፡

3. መመራመርን የሚጠይቁ ጥያቄዎች

የአንብቦ መረዳት ጥያቄ ከቀላል ወደ ከባድ እያደጉና እየተወሳሰቡ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ይህ የጥያቄ አይነትም ጥልቅ ንባብን የሚጠይቅ ሲሆን ተማሪዎቹ አጠቃላይና ዝርዝር ሀሳቦችን ለይተው በሚገባ እንዲመራመሩባቸው የሚያግዙ ናቸው፡፡ አብዛኛውን ጊዜም የምንባቡን ስውር መልእክት አብጠርጥረው ሊያወጡ የሚችሉ የጥያቄ አይነቶች በዚህ ስር ይመደባሉ፡፡ ከነዚያም ጥቂቶቹ የአንቀፆችን ፍሬ ነገር መለየት፣ አውዳዊ ፍቺን መፈለግ፣ የምንባቡን ዋና መልእክትና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲቻል ፅሁፉን የግድ መስመር በመስመር እያነበቡ በጥልቅ እንዲመራመሩ ይጋብዛል፡፡

4. የግምገማ ጥያቄዎች

የግምገማ ጥያቄ የምንባቡን አጠቃላይ ፍሬ ሀሳብ፣ መልእክቱን የፀሐፊውን አቀራረብና መሰል ነጥቦችን ለመገምገም የሚረዱ ሲሆኑ አንባቢውም ምንባቡን ተመርኩዞ የቀደመ እውቀቱን ተጠቅሞ በፀሐፊው ሀሳብ ላይ ግምገማውን፣ አስተያየቱንና የተሰማውን ስሜት ይገልፃል፡፡

5. የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች

እነዚህ ጥያቄዎች የአንባቢን ሀሳብ የመስጠት ችሎታ ለማዳበር የሚረዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንባቢው ፅሁፉን መሰረት በማድረግ ሊሆን ይችላል ብሎ ባሰበውና በገባው መንገድ የግል አስተያየቱን መግለፅ ይችላል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ከግምገማ ጥያቄዎች የሚለዩበት ዋናው ነጥብም የግል አስተያየትን የሚፈልጉ ጥያቄዎች ከፅሁፍ ውጪ የአንባቢን አስተያየት በማንፀባረቅ ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ነው፡፡

### 2.1.11 የቋንቋ ክሂል መልመጃ ምንነት

የቋንቋ ክሂል መልመጃ የምንለው ለተማሪዎቹ ትምህርታዊ ልምምድ የሚሆኑ የቋንቋ ክሂል ጥያቄዎችን የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ በዋናነት ለቋንቋ ትምህርት የተነደፈለትን አላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችሉ ሆነ ተብለው የሚቀረፁትን ክንውኖች የሚመለከት ነው። መልመጃ የሚባለው የቋንቋ ክሂሎች ይዘት ለክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ልምምድ ወደ ተማሪዎች የሚቀርቡበትን ስልት ነው። መልመጃ ልዩ ልዩ ቅርፅና አቀራረብ ኖሮት ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው እንዲተገብሩት የሚጠበቀውን የቋንቋ ተግባራት እንዲያከናውኑ የሚያግዙ ጥያቄዎችን የሚያካትት ነው።

ለተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎች ልምምድ የሚቀረፁ መልመጃዎች ከክፍል ውስጥ ልምምድ ባሻገር ቋንቋውን በገሀዱ አለም በአግባቡ እንዲገለገሉበት የሚያበቁ ሊሆኑ ይገባል። ይህን በማስመልከት Grant (1987፡ 800) ሲገልፁ "ለየትኛውም የክፍል ደረጃ መልመጃዎች ሲቀረፁ ተማሪዎች ቋንቋውን በገሀዱ አለም እንዲጠቀሙ በሚያስችል መልኩ መሆን ይኖርባቸዋል" በማለት አስረድተዋል።

### 2.1.12 የቋንቋ መልመጃ አደረጃጀት

የቋንቋ ትምህርት አላማን እንዲያሳኩ የሚዘጋጁ የክሂል መልመጃዎች በተገቢው ሁኔታ መደራጀት ይኖርባቸዋል። መልመጃዎቹ በሚፈለገው መልኩ ካልተደራጁ የሚጠበቀውን ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም ለትምህርት የሚዘጋጁ ይዘቶችና መልመጃዎች ሲደራጁ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሦስት መስፈርቶች አሉ። እነሱም ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት እና ውህደት ናቸው (ተስፋዬ 1981፣ 40)።

**ተከታታይነት፡-** ተከታታይነት ለተገቢው ቀጥተኛ አወቃቀር ወይም አደረጃጀት ዋና ጉዳይ ነው። ተከታታይነተ ሲባልም በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ እያደገ በተደጋጋሚ የሚመጣ ነው። እንደ Tyler (1949) ገለፃ ተከታታይነት በአንድ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በሚቀጥሉት ምዕራፎች እየተከታተሉ መምጣቱን የሚመለከት ነው። በትምህርት ይዘቶቹ መካከል ያለው ድግግሞሽ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ይበልጥ እንዲረዱ ያግዛቸዋል። ትምህርት ረጅም ጊዜና የማያቋርጥ ክትትል የሚያስፈልገው ጉዳይ በመሆኑ በውስን የትምህርት ይዘት የተፈለገው የትምህርት አላማ ግቡን ይመታል ተብሎ ስለማይታሰብ

ተማሪዎች የተፈለገውን ለውጥ እንዲያመጡ ተደጋጋሚነት ያላቸው የትምህርት ልምዶች እየተደጋገሙ ደረጃ በደረጃ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

**ተለጣጣቂነት:-** ከተከታታይነት ጋር የሚዛመድ ቢሆንም የሚለይበት ባህሪ አለው፡፡ ለትምህርት የሚቀርብ ጉዳይ በየደረጃው ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ የሚመራ ነው፡፡ ተለጣጣቂነት ጉዳዮን መደጋገም ብቻ ሳይሆን የጉዳዩን እንደገና እየሰፋ መሄድንም የሚመለከት ነው፡፡ የትምህርቱ ክብደት እየጨመረ መሄዱን ከግለፅ ወደ መሰብሰብ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ መደራጀትን ጭምር ያሳያል፡፡

እንደ Larson (1991)፣Tyler (1949) ገለፃ ተለጣጣቂነት ተዋረዳዊ የትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን የሚመለከት ነው፡፡ ለተከታታይ የክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ያላቸውን ተዋረዳዊ ዝምድናና ተደጋጋሚነት የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ይዘቶቹ እርስ በርስ ተሳስረው በመሄድ የተማሪው የቋንቋ ደረጃ እያደገ በሄደ ቁጥር በመማሪያ መፅሐፍት ውስጥ ያሉ ይዘቶችም ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲሄዱ የሚደረግበት አደረጃጀት ነው፡፡

ውህደት የሚባለው ደግሞ በማስተማሪያ መሳሪያው ውስጥ ያሉትን የትምህርት ልምዶች መስመራዊ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ የተዋሀደ የትምህርት ልምዶች ቅንብር የትምህርት ልምዶቹን የርስ በርሰ መደጋገፍ፣ የትምህርት ልምዶቹ አንዱ ሌላውን የማዳበርና የማበልፀግ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

በሌላ በኩል ውህደት ተማሪው እንዲማረው የሚቀርብለት ትምህርት ውስጥ ጉዳዮችን የሚያነሱ የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖራቸው ተደርገው መደራጀት አለባቸው፡፡ ይህም ሲባል ለተማሪው የቀረበው የትምህርት ይዘት ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ሊተሳሰር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ይዘቶቹ የሚኖራቸው የእርስ በርስ ግንኙነት ውህደት ይባላል፡፡

## 2.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠችው ርዕስ ላይ ጥናቷን ከመጀመሯ በፊት በርዕሱ ዙሪያ ተቀራራቢነት ያላቸውን የቀደምት ስራዎች ለመዳሰስ ሞክራለች፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት በ2004 የታተሙትን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት መፈተሽ ላይ በመሆኑ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ጥናቶች ማግኘት ባይቻልም በተዘዋዋሪ ተቀራራቢነት ያላቸው ስራዎች ተዳሰዋል፡፡

የሺጥላ ምንይልሸዋ (2000) በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ በሚል ርዕስ በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ የቀረበውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ገምግመዋል፡፡ የየሺጥላ ጥናት አላማ የምንባቦቹ ይዘት፣ አመራረጥና ግልፅነት ሲሆን በተጨማሪም የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር በሚያግዝ መልኩ መቅረብ አለመቅረባቸውንም ፈትሸዋል፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ጥናቶች በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ መሰራታቸውና የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ላይ ማተኮራቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ነገር ግን መማሪያ መፃህፍቱ የህትመት ዘመናቸው መለያየትና የሺጥላ የገመገሙት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ አሁን በስራ ላይ አለመኖሩ ጥናቶቹ እንዲለያዩ አድርጓቸዋል፡፡ ሌላው አብይ ጉዳይ የየሺጥላ ጥናት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ምን ያህል የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያዳብራሉ በሚል ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ደግሞ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹን አይነትና አደረጃጀታቸው ምን እንደሚመስል ይፈትሻል፡፡

ሁለተኛው ከዚህ ጥናት ጋር በከፊል የሚዛመደው በተሻለ ክፍሌ (2005) በ2004 ዓ.ም በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት በሚል ርዕስ የተሰራው ጥናት ነው፡፡ የተሻለ ጥናት አላማው የአራቱን ቋንቋ ክሂሎች ይዘትና መልመጃዎች አቀራረብ የክሂል መልመጃዎቹ የተደራጁበትን ስልት መገምገም ነው፡፡ ጥናቱ በ2004 በታተመው የዘጠነኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ መሰራቱና የአንብቦ መረዳት መልመጃዎችን በጥቂቱም ቢሆን መፈተሹ ከዚህኛው ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ የሁለቱ ጥናቶች ልዩነት የተሻለ ጥናት አራቱንም የቋንቋ ክሂል መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ሲዳስስ ይኸኛው ጥናት ግን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት መፈተሽ በመሆኑና የተሻለ ጥናት ለዘጠነኛ ክፍል የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ

ላይ ብቻ ሲሆን ይኸኛው የአስረኛ ክፍልን ጭምር ማካተቱና በአንድ የቋንቋ ክሂል ላይ ብቻ ማተኮሩ በሁለቱ ጥናቶች መካከል ልዩነትን ፈጥሯል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በተወሰነ ደረጃ ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰሉም የሁሉም ጥናት አላማ ግን የተለያየ ነው፡፡ ሁሉንም ጥናቶች አንድ የሚያደርጋቸው የሰነድ ፍተሻን በዋና የመረጃ ምንጭነት መጠቀማቸው ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመከተል የሚከናወን ሲሆን ከሰነድ ፍተሻ፣ ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በገላጭ (Descriptive) መንገድ እየተነተኑ ቀርበዋል፡፡ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎችና የመረጃዎቹ የአተናተን ዘዴ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 3.1 የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጮች የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሲሆኑ በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት ደግሞ በደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን፣ በደራሼ ወረዳ፣ በጊዶሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2007 ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

H

### 3.2 የናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1 የመማሪያ መፃህፍት ናሙና አመራረጥ

በሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከዘጠነኛ ክፍል ይጀምርና አስረኛ ክፍል ላይ ይጠናቀቃል፡፡ ለእነዚህ ለሁለተኛ ደረጃና ለመሰናዶ ትምህርት መማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በሀገር አቀፍ ደረጃ ነው፡፡ በቅርቡም ለእነዚህ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት በአዲስ መልክ ታትመው ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ከእነዚህ መማሪያ መጽሐፍት መካከል የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ይገኙበታል፡፡ መማሪያ መፃህፍቱ በቅርብ ጊዜ ስራ ላይ ከመዋላቸው የተነሳ በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ዙሪያ የግምገማ ስራ ባለመካሄዱና የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መጀመሪያም ማጠናቀቂያም በመሆናቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከአይነትና

ከአደረጃጀት አንፃር ለሁለተኛ ደረጃ የቋንቋ ትምህርት ምን ያህል ብቃት እንዳላቸው ለማየት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የጥናቱን ትኩረት ስበዋል፡፡

### 3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

የዚህን ጥናት አላማ ከዳር ለማድረስ አጥኚዋ በደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በሰገን አካባቢ ህዝቦች ዞን የደራሼ ወረዳን በአላማ ናሙና (purposive sampling) ስልት መርጣለች፡፡ ይህንን ወረዳ የመረጠችበት ዋነኛ ምክንያት አጥኚዋ በወረዳው ለአስራ አራት አመታት አማርኛ ቋንቋን ስታስተምር የቆየች በመሆኗ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አስፈላጊውን ትብብር አገኛለሁ ብላ በማሰብ ነው፡፡ በወረዳው ከሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አንድ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና (Convenience Sampling) ስልት ተመርጧል፡፡ ይህ የጊዶሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ የምታስተምርበት ስለሆነ አስፈላጊውን መረጃ በተፈለገ ጊዜ ለማግኘት፣ ጊዜንና ወጪንም ለመቀነስ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት በ2004 በታተሙት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በመገልገል ላይ የሚገኙና በ2007 ዓ.ም በትምህርት ገበታቸው ላይ ያሉ የጊዶሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ካለው የጊዜና የገንዘብ እጥረት አኳያ ተራ እጣ ናሙናን በመጠቀም በአስር ምድብ ከተከፈሉ 420 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ አምስቱን ምድብ በመምረጥ ከእያንዳንዱ ምድብ አስር አስር ተማሪ በመውሰድ በድምሩ 50 ተማሪዎች ተመርጠዋል፡፡ በዚሁ ትምህርት ቤት በአስር ምድብ የተከፈሉ 472 የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ሲኖሩ ከምድቡ አምስቱን ምድብ በመምረጥ ከእያንዳንዱ ምድብ አስር ተማሪዎችን በመውሰድ በድምሩ 50 ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ ተገቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አጥኚዋ ሁለት አይነት የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎችን ጥቅም ላይ አውላለች፡፡ እነዚህም የሰነድ ፍተሻና የጽሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ ከመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ውስጥ ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለገለው የሰነድ ፍተሻ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁ በአጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለ ነው፡፡ እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በመገልገል የመረጃዎቹ አሰባሰብ ከዚህ በታች ባለው ሁኔታ ተከናውኗል፡፡

### 3.3.1 የሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ ለዚህ ጥናት አላማ ከግብ መድረስ ትልቁን ድርሻ የያዘ ነው፡፡ በዚህም የጥናቱ ተተኳሪ መፃህፍት በ2004 ዓ.ም የታተሙት አሁን በስራ ላይ ያሉትን የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት በምዕራፍ ሁለት ምሁራን ካቀረቧቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንነት አንፃር የጥያቄዎቹ አይነትና አደረጃጀት ተፈትሸዋል፡፡

### 3.3.2 በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በጥናቱ ለታቀፉ ተማሪዎች የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ሁለት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን አጠቃላይ ዳራ የሚጠይቅ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ለጥናቱ በተመረጡት መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት አስመልክቶ በምዕራፍ ሁለት ምሁራን ያቀረቧቸውን ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ተንተርሰው የተቀረፁ 10 ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ ዝግ ጥያቄዎቹ የ "Likert Scale"ን የአጠያየቅ ስልት መሠረት ያደረጉ ሆነው 1 "በጣም አልስማማም"፣ 2 "አልስማማም"፣ 3 "ለመወሰን ያስቸግረኛል"፣ 4 "እስማማለሁ"፣ 5 "በጣም እስማማለሁ" የሚሉ አማራጭ መልሶችን የያዙ ናቸው፡፡ መጠይቆቹ አጥኚዋ በጥናቱ አላማ ይዛ ለተነሳችው ጥያቄዎች መልስ የሚያስገኙ መሆናቸው ታስቦ በአጥኚዋ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ በመጠይቆቹ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተገቢነታቸው እንዲረጋገጥ በአማካሪ ተገምግመውና እርማት ተሰጥቶባቸው ለጥናቱ በተመረጡ ተማሪዎች ተሞልተው ተመልሰዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ከሰነድ ፍተሻና ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት ስለ አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት የተሰበሰቡ መረጃዎች በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ እነዚህ መረጃዎች የተደራጁት የጥናቱ አብይ የመረጃ ምንጭ በሆነው የሰነድ ፍተሻ አጥኚዋ በምዕራፍ ሁለት ምሁራን ካቀረቧቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንነት አንጻር ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ደጋፊ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች ከሰነድ ፍተሻ የተገኘውን መረጃ ተከትለው በመቅረብ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ለጥናቱ የተመረጡት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍትም ባላቸው ተዋረዳዊ ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያ የዘጠነኛ ክፍል በመቀጠል የአስረኛ ክፍል ደረጃ በደረጃ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከአይነትና ከአደረጃጀታቸው አንፃር ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያ ላይም በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችን በማሳወቅ በ2004 ታትመው በስራ ላይ ባሉት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት በመማር ማስተማሩ ላይ ያላቸው አውንታዊና አሉታዊ ተፅኖ በመግለጽ ጠንካራ ጎናቸው የሚቀጥሉበት ደካማ ጎናቸው የሚቀረፍበትን አቅጣጫ በመጠቆም ጥናቱ ተቋጭቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የመረጃ ትንተና

ይህ ጥናት ትኩረቱ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀትን በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንነት አንጻር ይተነተናሉ። የትንተናው ዋነኛ ትኩረት ከሰነድ ፍተሻ በተገኙ መረጃዎች ላይ ሆኖ ከተማሪዎች በፅሁፍ መጠየቅ የተገኙ መረጃዎችንም ከሰነድ ፍተሻው ጋር በማያያዝ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም ይተነተናሉ። በመፃህፍቱ ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀታቸውን አስመልክቶ የተገኙ መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት ስለ መማሪያ መጽሐፍቱ ጥቂት መረጃዎችን እንመልከት።

### 4.1 የተተኳሪ መፅሐፍቱ አጭር ቅኝት

የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በአዲስ መልክ ታትሞ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ እየተሰራበት ይገኛል። የእነዚህ መፃህፍት አዘጋጆችም የዘጠነኛ ክፍል ደመላሽ አለሙ፣ ሳህሉ አክሊሉና የሺጥላ መንግስቴ ሲሆኑ የአስረኛ ክፍል አዘጋጆች ማርታ እሸቱና ነፃነት ጌትነት ናቸው። እነዚህ በአዲስ መልክ የተዘጋጁት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ሽፋናቸው ጠንካራና በስስ ላስቲክ የተሸፈነ ነው።

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መልኩ ሙሉ አርንጓዴ ሆኖ በሽፋኑ ፊት ለፊት የኢትዮጵያ ባንዲራና አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የሚያመላክቱ ስዕሎች አሉበት። ከሽፋኑ ግርጌ በብርቱካናማ፣ በቢጫ፣ በነጭና በአረንጓዴ ቀለም ወደ ጎን የተሰመረ ሲሆን በብርቱካናማው ቀለም ላይ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተርን አርማ ይዟል። የዚህ መፅሐፍ ቁመቱ 21 ሴ.ሜ ወርዱ 15 ሴ.ሜ የመጽሐፍ ዋጋ አሰራ አምስት ብር ሲሆን የገፁ ብዛት አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ነው። ይህ መጽሐፍ በአስር ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን መልመጃዎቹም በተለያየ ህብረ ቀለም ያሸበረቀ ነው። መጽሐፉ በመጨረሻ ተጨማሪ የንባብ መፃህፍትን፣ ማጣቀሻ መፃህፍትን፣ የተለያዩ ቃላትን ከነፍቻቸውና፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ከነፍቻቸው ይዟል።

የአስረኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ መልኩ ሙሉ ቢጫ ሲሆን በሽፋኑ ፊት ለፊት የኢትዮጵያ ባንዲራና አራቱን የቋንቋ ክሂሎች የሚያመላክቱ ስዕሎች ይዟል፡፡ የሽፋኑ ግርጌ በብርቱካናማ፣ በአርንጓዴ፣ በነጭና በቢጫ፣ ቀለም ወደ ጎን የተሰመረ ሲሆን በብርቱካናማው ቀለም ላይ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር አርማ አርፎበታል፡፡ ይህ መፅሐፍ ቁመቱ፣ ወርዱ ዋጋውና የምዕራፍ ብዛት ከዘጠነኛ ክፍል ጋር እኩል ሲሆን የገፁ ብዛት ግን 142 ነው፡፡ በመፅሐፉ በመጨረሻዎቹ ገፆች ላይ ሙዳዬ ቃላት፣ ፊሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸውና ዋቢ መፅሐፍትን የያዘ ነው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የሽፋን መልካቸው የተለያየ ቢሆንም በሽፋናቸው ላይ የያዙት መረጃ ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለቱም መፅሀፍት በሽፋናቸው የውስጥ ገጽ ላይ ስለ መፃህፍቱ አያያዝ አስር መመሪያዎች ተቀምጠዋል፡፡ ሁለቱም መፃህፍት ለአያያዥ ምቹና የውስጥም ሆነ የላይ ቀለማቸው ተማሪዎችን እንዲመስጡ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

## 4.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የምንባቡን አላማ የፀሀፊውን አመለካከት የአንባቢውን አረዳድና ሌሎችንም ነጥቦች የሚዳስሱ በመሆናቸው በተለያየ መንገድ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በክፍት ጥያቄ፣ ምርጫ ሰጪ፣ በእውነት ሀሰት፣ በአዛምድና ሌሎች አይነት እየተሰበጣጠሩ ቢቀርቡ የተሻለ ይሆናል፡፡ ሌላው ጥያቄዎቹ የግድ ሁሉንም አይነት ያካተቱ ማለት ሳይሆን እንደ ምንባቡ ባህሪ ጥያቄዎቹ ተለዋዋጭነት ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡ የጥያቄዎቹን ስብጥር አስመልክቶ በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡- የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር ሲታዩ

| ምዕራፍ እና ርዕስ | የመልመጃ ጥያቄ አይነቶች | | | | በየምዕራፉ ያሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍት ጥያቄዎች | ዝግ ጥያቄዎች | | | |
| | | ምርጫ | አዛምድ | እውነት/ሐሰት | |
| ምዕራፍ አንድ፡ የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት | 25 | - | - | 7 | 32 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ ስነ ቃል | 13 | 5 | - | - | 18 |
| ምዕራፍ ሶስት፡ ስነ ጽሁፍ | 27 | 5 | - | 5 | 37 |
| ምዕራፍ አራት፡ ወንድማማቾቹ | 26 | - | - | 10 | 36 |
| ምዕራፍ አምስት፡ ቃል ኪዳን | 30 | 6 | - | 5 | 41 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ የተውኔት አላባዊያን | 12 | 9 | - | - | 21 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ ቆሻሻና አወጋገዱ | 16 | 5 | - | 5 | 26 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ" | 22 | - | - | - | 22 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ዴሞስቴን፣ የምርጥ ንግግር አባት | 20 | - | - | - | 20 |
| ምዕራፍ አስር፡ ሙግት | 29 | - | - | 10 | 39 |
| **ድምር** | 220 | 30 | 0 | 42 | 292 |
| **በመቶኛ ስሌት** | 75% | 10% | 0% | 15% | 100% |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደተመለከትነው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አስር ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ በእነዚህ አስር ምንባቦች ውስጥ ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችም በሁለት መልኩ የቀረቡ ሲሆን ክፍት ጥያቄዎች 220 (75%) ዝግ ጥያቄዎች 72 (25%) ናቸው፡፡ ዝግ ጥያቄዎቹ በምርጫና በእውነት ሐሰት የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ደረጃ በአስሩም ምንባብ ውስጥ በአዛምድ መልክ የቀረበ የአንብቦ መረዳት ጥያቄ የለም፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ ከፍተኛው የአንብቦ መረዳት ጥያቄ ቁጥር በክፍት መልክ መቅረቡን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡ እንደ Madson (1983)፣ Wier (1990) አስተያየት ክፍት ጥያቄዎች መላሹ ነፃ ሆኖ ያለ ገደብ የራሱን ሀሳብ በተረዳው መንገድ የሚገልፅባቸው የጥያቄ አይነቶች በመሆናቸው የአንባቢውን የመተንበይ፣ የማብራራት፣ የማነፃፀር፣ የመገመትና ሌሎች ችሎታዎችን በማዳበር ረገድ ከዝግ ጥያቄዎች የተሻሉ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ አንጻር በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን በነፃ ለመግለፅ፣ አመቺነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡

እንደ Grellet (1991) ገለፃ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የተለያዩ የጥያቄ አይነቶችን ያካትቱና ተለዋዋጭነት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸውና የጥያቄ አይነቶቹም በክፍት ወይም በዝግ መልክ የቀረቡ ቢሆኑና አልፎ አልፎ ስዕላዊ መግለጫዎችን በመመርኮዝ ማብራሪያ የሚሰጥባቸው አይነት ሆነው ቢቀርቡ ተመራጭ ነው፡፡ ይህም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር እገዛው የጎላ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍት ውስጥ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከአዛምድ ጥያቄዎች በስተቀር ሁሉንም የጥያቄ አይነቶች አካተው የያዙ ናቸው፡፡ የተካተቱት የጥያቄ አይነቶችን አስመልክቶ የሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርበዋል፡፡

**ለክፍት ጥያቄ፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 6) ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቃላት ቀርበዋል ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 7)፡፡

**ለዝግ ጥያቄ፡-** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መካከል በምንባቡ መሰረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 19)፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለፁ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 37)፡፡

**ስዕላዊ መግለጫን በመመርኮዝ የቀረበ፡-** ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ምንባቡን መሠረት አድርጉና ስዕላዊ መግለጫውን ወደ ፅሁፍ በመቀየር የጥንቱን ሙግትና የዛሬውን ክርክር የየግልና የጋራ ባህሪ ዘርዝራችሁ በመፃፍ አቅርቡ፡፡ እያንዳንዱ ክብም አንዱ ባንዱ ውስጥ ወይም አንዱ ካንዱ ውጪ ለምን እንደዋለ አስረዱ፡፡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 72)

ከዚህ አንጻር የጥያቄዎቹ ስብጥር በዝግ፣ በክፍትና በስዕላዊ መግለጫዎች የቀረበ ቢሆንም ከዝግ ጥያቄዎች መካከል በአዛምድ መልክ የቀረበ ምንም የአንብቦ መረዳት ጥያቄ የለም፡፡ በስዕላዊ መግለጫ መልክም የቀረበው ጥያቄ አንድ ብቻ መሆኑ በሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

የጥያቄዎቹን ስብጥር ተመጣጣኝነት በተመለከተ ቀደም ሲል በሰንጠረዥ አንድ እንደተመለከተው ከ292 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መካከል 220 ክፍት ጥያቄዎች ሲሆኑ 72 ዝግ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በፐርሰንት 75% ክፍት እና 25% ዝግ ከዚህ አንጻር ስብጥሩ የተመጣጣኝነት ችግር ይታይበታል፡፡

በአጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተካተቱ አስር ምዕራፎች ስር ከቀረቡ ምንባባት የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስንመለከት ከፍተኛውን የጥያቄ ቁጥር የያዘው ምዕራፍ አምስት ሲሆን 41(14%) ጥያቄዎችን አካቷል፡፡ ዝቅተኛውን የጥያቄ ቁጥር የያዘው ምዕራፍ ደግሞ ምዕራፍ ሁለት ሲሆን 15(5%) የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ በቀሪዎቹ ምዕራፎች የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተመጣጣኝ ቁጥር ያላቸው መሆናቸውን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡

ሌላው በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚካተቱ መልመጃዎች የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተለ መሆን አለበት፡፡ እንደ Nuttall (1992:132) አገላለፅ መልመጃዎቹ ቀጥተኛ ማገናዘብንና ማቀናበርን የሚሹ፣ የመመራመር፣ የግምገማና የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ወዘተ. ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በ9ኛ ክፍል ያሉት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በሚከተለው ሠንጠረዥ እንይ፡፡

ሠንጠረዥ 2፡ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነቶችን የሚያሳይ

| ምዕራፍ እና ርዕስ | የጥያቄ አይነቶች ዝርዝርና ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀጥተኛ ጥያቄዎች | የማገናዘብና የማቀናበር ጥያቄዎች | የመመራመር ጥያቄዎች | የግምገማ ጥያቄዎች | የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች | ድምር |
| ምዕራፍ አንድ፡ የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት | 12 | 13 | 7 | - | - | 32 |
| ምዕራፍ ሁለት፡ ስነ ቃል | 5 | 4 | 5 | 4 | - | 18 |
| ምዕራፍ ሶስት፡ ስነ ጽሁፍ | 15 | 10 | 10 | 1 | 1 | 37 |
| ምዕራፍ አራት፡ ወንድማማቾቹ | 10 | 6 | 16 | - | 4 | 36 |
| ምዕራፍ አምስት፡ ቃል ኪዳን | 9 | 5 | 23 | 1 | 3 | 41 |
| ምዕራፍ ስድስት፡ የተውኔት አላባዊያን | - | 12 | 8 | - | 1 | 21 |
| ምዕራፍ ሰባት፡ ቆሻሻና አወጋገዱ | 5 | 11 | 10 | - | - | 26 |
| ምዕራፍ ስምንት፡ "ለወሬ ሞትኩ ይበሉ" | 9 | 3 | 9 | - | 1 | 22 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡ ዴሞስቴን፣ የምርጥ ንግግር አባት | - | 8 | 11 | - | 1 | 20 |
| ምዕራፍ አስር፡ ሙግት | 12 | 12 | 14 | 1 | 1 | 39 |
| **ድምር** | **77** | **84** | **113** | **7** | **12** | **292** |
| **በፐርሰንት** | **26%** | **29%** | **39%** | **2%** | **4%** | **100%** |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደተገለፀው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተካተቱት የአንብቦ መረዳት የጥያቄ አይነቶች ከብዛት አንፃር ቅደም ተከተላቸው ሲታይ ከሁለት መቶ ዘጠና ሁለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የመመራመር ጥያቄ ሲሆን የጥያቄው ብዛት 113 (39%) ነው፡፡ እንደ Zintz (1972)፣ Grellet (1990) Nuttal (1988) አገላለፅ የመመራመር ጥያቄዎች ተማሪዎች ምንባቡን በጥልቀት እንዲያነቡ የሚጋብዙ በመሆናቸው የምንባቡን ዝርዝር ሀሳብ ነጣጥለው በሚገባ እንዲመራመሩ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ በዚህም በመማሪያ መፅሐፍ ለመመራመር ጥያቄዎች ትኩረት መሰጠቱን ያመለክታል፡፡

በመማሪያ መፅሐፍ ከመመራመር ጥያቄ ቀጥሎ የማገናዘብና የማቀናበር ጥያቄዎች ሲሆኑ በቁጥር 84 (29%) ናቸው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ ቀጥተኛ ሲሆን ይህ የጥያቄ አይነት በቁጥር 77 (26%) ነው፡፡ ቀጥተኛ ጥያቄዎች ከምንባቡ በቀጥታ ተወስደው ቃል በቃል ምላሽ የሚሰጥባቸው የጥያቄ አይነቶች ናቸው፡፡

በአንፃሩ በመፅሐፍ ውስጥ ዝቅተኛውን ቁጥር የያዙት የጥያቄ አይነቶች የግምገማና የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ሲሆኑ የግምገማ 7 (2%)፣ የግል አስተያየት 12 (4%) ድርሻ አላቸው፡፡

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ሁሉንም የጥያቄ አይነቶች የዳሰሱ ቢሆንም ለሁሉም የጥያቄ አይነቶች ተመጣጣኝ የሆነ ድርሻ አለመሰጠቱን የሰነድ ፍተሻው ያሳያል፡፡ በመሆኑም የግምገማና የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች የተሰጣቸው ትኩረት አናሳ መሆኑን ከላይ የቀረበው መረጃ ይጠቁማል፡፡

## 4.2.1 የክሂሎች ቅንጅት

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ በቋንቋ ክሂሎች አቀራረብ ወቅት አንዱ ክሂል ሲነሳ ሌላው ተከትሎ የሚነሳ በመሆኑ ተያያዥነት ያላቸውን የቋንቋ ክሂሎች በማቀናጀት ማስተማርን የሚመለከት ሲሆን የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማቅረብ የተማሪውን ተግባቦትና ግንዛቤ ማሳደግ ይቻላል፡፡ ቋንቋ በትምህርት መልክ የሚቀርበው ተማሪዎች+ እንዲናገሩና እንዲፅፉ ወይም በክሂሎች እንዲጠቀሙ ብቻ ሳይሆን ቋንቋውን እየተማሩ ስለ ቋንቋ እንዲመራመሩ፣ እንዲያስቡ፣ እንዲጠይቁና የማገናዘብ ችሎታቸው እንዲጨምር ነው፡፡ Atkins et al, (1996:26) የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው በሚቀርቡበት ሂደት ውስጥ ተማሪዎቹ ተግባቦታዊ ችሎታቸው ላቅ እንዲል የሚማሩትን ትምህርት በጥልቀት ተገንዝበው ሀሳባቸውን የመግለፅ ችሎታ ከማጎልበታቸውም በላይ አእምሮአቸውን በማሰራት የአስተሳሰብ ችሎታቸውን ለማበልፀግ እንደሚረዳቸው ይገልፃሉ፡፡

**ንባብና ፅህፈት፡-** ከቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ ፅህፈት ሲሆን ለንግግር ድምፆች በሚወክሉ ምልክቶች አማካይነት ሐሳብን በወረቀት ላይ ማስፈር ነው፡፡ እንደ ተስፋዬ (1981፡6) አገላለፅ "ጽህፈት ሲባል የእጅ ፅህፈት አጣጣልን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡

የሐሳብ አቀነባበርን የሐሳብ አደረጃጀትን፣ የቃላት አመራረጥንና አገላለፅንም ስልት የሚጠይቅ ነው፡፡" በማለት አስፍረዋል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች ፅህፈትን በተለያየ ዘዴ እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ በዚህም በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ 41 የንባብ ክሂልን ከፅሁፍ ክሂል ጋር አቀናጅተው ለማዳበር የሚያግዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹ የተለያዩ ይዘት ቢኖራቸውም መሠረታቸው የቀረበው ምንባብ ስለሆነ ምንባቡን አንብበው በተለያየ መልኩ እንዲፅፉ የሚያግዙ ናቸው፡፡ ቀጥለን ንባብና ጽህፈት ተቀናጅተው መቅረባቸውን አስመልክቶ ከመማሪያ መጽሐፉ ምሳሌዎችን እንመልከት፡፡

የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ አንብቡና "እሱ" የተባለው ሰው ምን አይነት ባህሪይ እንዳለው፣ እንዲህ አይነት ባህሪ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ ፅፋችሁ ለክፍል አቅርቡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 85)፡፡ ባነበባችሁት ፅሁፍ ውስጥ በዋናነት የተነሱ ጉዳዮችን በፅሁፍ አቅርቡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 124)፡፡ የሚከተሉትን ከምንባብ የወጡ አባባሎች በራሳችሁ አባባል እንደገና ፃፉ፡፡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 124)፡፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ አብራርታችሁ መልሱ፡፡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 136)

እነዚህንና ሌሎች መሰል ትዕዛዝን የያዙ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችም ከምንባብ የወጡ ሆነው ምላሻቸው በጽሁፍ እንዲሰጥ የሚያዙ ሲሆን ይህም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፅሁፍ ጋር አቀናጅቶ ለማዳበር ያግዛሉ፡፡

የንባብ ክሂል ከጽህፈት ክሂል ጋር ስላለው ቅንጅት ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘ መረጃ

ጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ "የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በፅሁፍ እንድትመልሱ የሚጋብዙ ናቸው" ተብሎ ለተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "በጣም አልስማማም" ያሉት 2(4%)፣ "አልስማማም" 6(12%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 4(8%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 23(46%) እና "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 15(30%) ናቸው፡፡ ይህ መረጃ የሚያመለክተው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በጽሁፍ ለመመለስ የሚጋብዙ ጥያቄዎች የያዙ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ አጥኚዋ ከሰነድ ፍተሻ ያገኘችው መረጃ እና በፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች ያገኘቻቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ከጽህፈት ክሂል ጋር ተቀናጅተው መቅረባቸውን ነው፡፡

**ንባብና ማዳመጥ፡-** የማዳመጥ ክሂልን ከንባብ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር ተማሪዎች ዜናዎችን፣ ድራማዎችን፣ የተቀረፁ ንግግሮችን፣ እንዲያደምጡ በማድረግ ከምንባቡ ጋር ተያያዥነት ያለውንና የሌለውን እንዲለዩ በማድረግ ንባብን ከማዳመጥ ጋር አያይዘው እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል (Grellet፡ 1991)፡፡ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ንባብን ከማዳመጥ ክሂል ጋር ያቀናጁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

ቡድን መስርታችሁ አንዱ የቡድን አባል የቀረቡትን ጽሁፎች ሲያነብ ሌሎቻችሁ በማዳመጥ በአነባበብ ስልቱ ላይ አስተያየት ስጡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 27)፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች አንብባችሁ በመያዝ ማብራሪያውን እያዳመጣችሁ መልሶቻችሁን ስጡ (9ኛ ክፍል፡ ገጽ 27)፡፡

ከላይ በተገለፁት በሁለት ምዕራፎች ብቻ የማዳመጥ ክሂልን ከንባብ ክሂል ጋር ለማቀናጀት ጥረት ተደርጓል፡፡ በአብዛኞቹ ምዕራፎች የሚገኙ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡ ጥያቄዎች ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ሲሆን ይኸውም መምህሩ በመምህሩ መምሪያ ላይ የተፃፈ አንድ ፅሁፍ እንዲያነቡላቸውና ተማሪዎች ያንን በማዳመጥ በመማሪያ መፅሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ የሚጋብዙ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ (9ኛ ክፍል ገጽ፣ 8፣ 9፣ 23፣ 43) በእነዚህ ገፆች ላይ የሚገኙ የማዳመጥ ጥያቄዎች በሙሉ ምንባቦቹ ያሉት በመምህሩ መምሪያ ላይ ብቻ በመሆኑ መምህሩ እንዲያነቡ ትዕዛዝ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ከቀረበው ምንባብ ጋር ተያያዥነት ያለውን ርዕሰ ጉዳይ አስመልክቶ የቀረቡ ውይይቶችን፣ በቴፕ የተቀረፁ ምልልሶችን እንዲያዳምጡ በማድረግ ከምንባቡ ጋር ተያያዥነት ያላቸውንና የሌላቸውን እንዲለዩ የሚያዝ የማዳመጥ ጥያቄ አንድ ብቻ መሆኑን የሰነድ ፍተሻው ያመለክታል፡፡

**ንባብና ንግግር፡-** የንባብ ክሂልን ከንግግር ክሂል ጋር በማቀናጀት ሊዘጋጅ የሚችል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን በተለያየ መልኩ ማቅረብ እንደሚቻል በምዕራፍ ሁለት ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ እንደ Grellet (1991) ገለፃ የንባብ ክሂልን ከንግግር ክሂል ጋር በማቀናጀት ለንግግር፣ ለክርክርና ለውይይት የሚጋብዙ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ ተማሪዎች

ተዘጋጅተውበት እንዲመጡ በማድረግ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ 38 ንባብና ንግግርን የሚያቀናጁ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ቀጥለን ጥቂት አስረጂዎችን እንመልከት፡፡

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 6)፡፡ ልብ ወለዱን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡ በልብወለዱ ባለታሪኮች ላይ የተከሰተው ችግር ከመነሻው እንዳይፈጠር ችግሩ ከተፈጠረም በኋላ በቀላሉ እንዲፈታ ምን መደረግ ነበረበት ብላችሁ ታስባላችሁ በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በየቡድን መሪያችሁ በክፍል አቅርቡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 61)፡፡ በምንባቡ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያትን ወክላችሁ ተሟገቱ፡፡

ከላይ የቀረቡትንና ሌሎች መሰል ትዕዛዞች የንግግር ክሂልን ከንባብ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር በሚያስችል መልኩ በመማሪያ መፅሐፍ ላይ በተለያዩ ምዕራፎች ቀርበዋል፡፡ ይህንኑ አስመልክቶ ለተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የቀረበውን እንመልከት፡፡

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከንግግር ክሂል ጋር ያላቸውን ቅንጅት አስመልክቶ ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘ መረጃ

በጥያቄ ቁጥር 4፣ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይዘዋል፡፡ ለሚለው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ "በጣም አልስማማም" 5(10%)፣ "አልስማማም" 13(26%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" 6(12%)፣ "እስማማለሁ" 15(30%)፣ "በጣም እስማማለሁ" 11(22%) ሲሆኑ ይህ መረጃ የሚያመለክተው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የንግግር ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ ጥያቄዎችን የያዙ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃም የንግግር ክሒልን ለማዳበር የተዘጋጁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መኖራቸውን ያገልፃል፡፡

**ንባብ፣ ንግግርና ፅህፈት፡** አብዛኛውን ጊዜ የቋንቋ ክሂሎች፣ አንድ ባንድ ውስጥ ተደጋግፈው የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ይኸውም ምንባቡን አንብበው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል ወይም በፅሁፍ እንዲመልሱ የሚያዙ በርካታ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በመፅሐፍ ተካትተዋል፡፡ ንባብን፣ ንግግርን ፅህፈትን ባንድ ትዕዛዝ አካተው የያዙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሁሉም ምዕራፎች ባይገኙም በተወሰኑ ምዕራፎች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ ቀጥለን የተወሰኑ አስረጂዎችን እንመልከት፡፡

የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ በጥሞና አንብቡና "እሱ" የተባለው ሰው ምን አይነት ባህርይ እንዳለው እንዲህ አይነት ባህሪ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ ፅፋችሁ ለክፍል አቅርቡ። ባቀረባችሁት ላይም ተወያዩ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 85)። በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ምንባቡን መሠረት አድርጉና ስዕላዊ መግለጫውን ወደ ጽሁፍ በመቀየር የጥንቱን ሙግትና የዛሬውን ክርክር የየግልና የጋራ ባህርይ ዘርዝራችሁ በመፃፍ አቅርቡ። እያንዳንዱ ክብም አንዱ ባንዱ ውስጥ ወይም አንዱ ካንዱ ውጪ ለምን እንደዋለ አስረዱ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 85)።

በአጠቃላይ በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ከተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅት ከላይ የተገለፀውን ይመስላል። ነገር ግን አብዛኞቹ መልመጃዎች የትዕዛዝ ግልፅነት የጎደላቸው በመሆናቸው በቃል ይሁን ወይም በፅሁፍ ይሁን የማይገልፁ በአስሩም ምዕራፎች ስር ይገኛሉ። ትዕዛዙ በግልጽ ቢቀመጥ ኖሮ የበለጠ የክሂሎች ቅንጅት ይፈጠር ነበር። ቀጥለን የትዕዛዝ ግልፅነት የጎደላቸውን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች እንመልከት፡-

ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቃላት ቀርበዋል ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 7)። ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አመራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 19)። የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለፁ።

ከላይ የቀረቡት እንደ ምሳሌ ተጠቀሱ እንጂ በአስሩም ምዕራፎች በተመሳሳይ መልኩ በግል ይሁን በቡድን በመፃፍ ይሁን በመናገር ግልፅ ያልሆነ ትዕዛዝ የያዙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ይህንን አስመልክቶ ለተማሪዎች የቀረበውን የፅሁፍ መጠይቅ ቀጥለን እንመልከት።

### የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ የትዕዛዝ ግልፅነት አስመልክቶ ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ

በጥያቄ ቁጥር 8፣ "የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የአሰራር መመሪያዎች ግልፅ ናቸው" ተብሎ ለተማሪዎቹ በቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣ "በጣም አልስማማም" 15(30%) "አልስማማም" 12(24%)፣ "ለመወሰን ያስቸግራል" 5(10%)፣ እስማማለሁ

10(20%)፣ "በጣም እስማማለሁ" 8(16%) በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህ መረጃ የሚያሳየው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ግልፅ ያልሆኑ መመሪያዎች እንዳላቸውና ተማሪውም ጥያቄዎቹን በምን መልኩ እንደሚሰራ የማይገልፁ መመሪያዎች መኖራቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከጽሁፍ መጠይቁ እና ከሰነድ የተገኘው መረጃ እንደሚገልፀው በርካታ ቁጥር ያላቸው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ቢኖሩም የአብዛኞቹ መልመጃዎች ትዕዛዝ በምን መልኩ እንደሚሰሩ ስለማይጠቁሙ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ በይበልጥ የትኛውን ክሂል እንደሚያዳብሩ ለመግለፅ አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም ግልፅ ባልሆኑ መመሪያዎች በንግግር ወይም በፅሁፍ ያሰራሉ ብሎ ለመደምደም አዳጋች ነው፡፡

በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ትልቁ አላማ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተማሩትን ከክፍል ውጭ ከዕለት ተዕለት ኑሯቸው ጋር በማያያዝ እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው፡፡ ቋንቋው በገሀዱ አለም በተገቢው ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ለትምህርትነት የቀረቡት የክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከዚህ አንፃር በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተማሪዎቹ በገሀዱ አለም ቋንቋውን እንዲጠቀሙ የሚያስችል መሆን አለመሆናቸውን ለማየት የተወሰኑ አስረጂዎችን እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ በታች አጥንታችሁ የምትተውኑት ጭውውት ቀርቧል፡፡ የፆታ ስብጥሩን የጠበቀ ባለ አራት አባላት ቡድን መስርታችሁ በጭውውቱ ሀሳብና የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተወያዩ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 21)፡፡ በልብ ወለዱ ባለ ታሪኮች ላይ የተከሰተው ችግር ከመነሻው እንዳይፈጠር ችግሩ ከተፈጠረም በኋላ በቀላሉ እንዲፈታ ምን መደረግ ነበረበት ብላችሁ ታስባላችሁ፡፡ በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ በክፍል አቅርቡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 61)፡፡ በአጭር ልብ ወለድ እንደታየው በሁለቱ ዋና ገፀ ባህርያት መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ለዚህ ተጠያቂው ማነው፧ ዘነበ? ወይስ በልዩ? አንደኛውን ደግፋችሁ ሌላውን በመቃወም ተከራከሩ፡፡ በክርክሩ ያልተሳተፋችሁ ደግሞ በተከራካሪዎች የሚሰነዘሩ ሀሳቦች የቱን ያህል ምክንያታዊ መሆን አለመሆናቸው ላይ አስተያየት በመስጠት ተሳተፉ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 63)፡፡ በምንባቡ ውስጥ ያሉ ገፀ ባህሪያትን ወክላችሁ ተሚገቱ፡፡

እነዚህንና መሰል ጥያቄዎችን በማንሳት ምንባቡ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሊያጋጥም ይችላል ተብሎ የሚታሰቡትን ጉዳዮች ተማሪዎች ምንባቡን በማንበብ በዚያ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ እንዲከራከሩ እንዲወያዩ የተለያየ ገፀ ባህሪያትን በመላበስ ጭውውት እንዲሰሩ የሚያደርጉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመቅረባቸው ይህም ተማሪዎች ከክፍል ወጭ ለሚያደርጉት መስተጋብር መነሻ ይሆናቸዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ ተማሪዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ቋንቋውን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ እንዲጠቀሙ ያላቸውን እገዛ በተመለከተ ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ

በጥያቄ ቁጥር ስድስት "የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ቋንቋውን በክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጪ እንድትጠቀሙ የሚያግዙ ናቸው፡፡ በሚል ለተማሪዎች የቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ "በጣም አልስማማም" 6(12%) "አልስማማም" 1(2%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" 3(6%) "እስማማለሁ" 17(34%)፣ "በጣም እስማማለሁ" 23(46%) ናቸው፡፡ ከተማሪዎቹ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያግዙ መሆናቸውን ነው፡፡ ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

## 4.2.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አደረጃጀት

የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ በተገቢው መንገድ ከተመረጡ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው አደረጃጀት ነው፡፡ Nunan (1988); Cunnings Worth (1984) እንደገለፁት አደረጃጀት በቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንደሚገባቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተፈትሸዋል፡፡

**ከተከታታይነት አንፃር፡-** ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ተደጋግመው ሲቀርቡ መሆኑን ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ላይ ተገልፆል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት የተካተተው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ

ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተከታታይነታቸው ምን እንደሚመስል ቀጥለን እንመልከት፡፡

በአስሩም ምዕራፎች ላይ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ወጥ በሆነ መልኩ በክፍል አንድ ንባብ በሚለው ስር የቀረቡ ሲሆን አልፎ አልፎ በአንዳንድ ምዕራፎች ላይ ጥያቄን መሠረት አድርገው የቀረቡ ምንባቦች ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ ሁለት ገጽ 27፣ 28 እና 29፣ በምዕራፍ ሶስት ገጽ 47፣ በምዕራፍ አምስት ገፅ 85 እና 87 ላይ የገቡ ምንባቦች በስተቀር በሁሉም ምዕራፍ የመጀመሪያውን ክፍል የያዙት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ በተመሳሳይ ሁኔታ በተከታታይ መቅረባቸውን ብቻ ሳይሆን የጥያቄዎች ጥልቀት በምን መልኩ እንደቀረበ ከሰነድ ምርመራው የተገኙ አስረጂዎችን እንመልከት፡፡

በምዕራፍ አንድ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በምንባቡ መሠረት በቃል የሚመለሱ እውነት ሀሰት ብሎ ምክንያት እንዲዘረዝር የሚያዙ፣ ቃላት በምንባቡ ባላቸው አገባብ መሠረት እንዲመለሱ የሚያዙ፣ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ምርጫ፣ የቀረበውን ጭውውት በማንበብ ገፀ ባህሪን ወክሎ መጫወት፣ አንድ ዝርውና አንድ ግጥምን በማንበብ የተሻለ አነባበብ የቱ እንደሆነ እንዲመርጡ በማድረግ የአንብቦ መረዳት ክንውኖቹ ጠለቅ እያሉ መጥተዋል፡፡ በምዕራፍ አራት በቀረበው ልብ ወለድ ምንባብ በሁለት ወንድማማቾች መካከል አለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ለዚህ ተጠያቂው ማን እንደሆነ አንዱን በመደገፍ አንዱን በመቃወም እንዲከራከሩ፣ በተከራካሪዎች ሀሳብ ላይ አድማጮች አስተያየት በመስጠት እንዲሳተፉ የሚያዙ በምዕራፍ አስር በተመሳሳይ በምንባቡ የቀረቡትን ገፀ ባህሪያት በመወከል እንዲሞግቱ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ይህ የሚያሳየን ተመሳሳይ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ በተለያየ ምዕራፍ እያደረጉ መሄዳቸውን ያሳየናል (9ኛ ክፍል፣ ገፅ 63፣175)፡፡

**ከተለጣጣቂነት አንፃር፡-** በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳናት ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ተለጣጣቂነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የትምህርት ይዘቶች ተደጋግመው የሚመጡበት ሁኔታ ነው፡፡ የትምህርት ይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ሊኖራቸው ይገባል ስንል በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች እያደገና እየሰፋ መሄድ አለባቸው፡፡ በዚህ ጥናት ተለጣጣቂነትን ከተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ሳይሆን በዚሁ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከምዕራፍ ምዕራፍ ያላቸውን ተለጣጣቂነት በሚከተሉት አስረጂዎች እንመልከት፡፡

በምዕራፍ አንድ ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በቃል መመለስ፣ በእውነት ሀሰት መልክ መመለስና ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት ሲሆን በምዕራፍ ሁለት በቃል የሚመለሱትን ጥያቄዎች እንዲያብራሩ፣ በምሳሌ አስደግፈው እንዲገልፁ፣ ከምንባቡ ማስረጃ ጠቅሰው እንዲናገሩ የሚያደርጉ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 6፣20)፡፡ በምዕራፍ ሶስት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ ዐረፍተ ነገር ስሩ፣ በምዕራፍ አራት ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በልብ ወለዱ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፣ በምዕራፍ አምስት በግጥሙ መሠረት ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቺ ፈልጉላቸው፣ በምዕራፍ ሰባት ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ስጡ፣ አገባባዊ ፍቺ ለመስጠት የተጠቀማችሁበትን ዘዴም ግለፁ፡፡ በምዕራፍ ዘጠኝ ጥንድ ሆናችሁ ከሚከተለው አንቀጽ ውስጥ እማሬያዊ ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸው አምስት ቃላት አውጡና እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ስጡ፡፡ (9ኛ ክፍል፣ ገጽ 39፣ 64፣ 89፣ 124፣ 156)፡፡

ከላይ ከቀረቡት አስረጂዎች እንደሚያመለክቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ በተለያዩ ምዕራፎችና በተለያዩ ምንባቦች የቃላት ትምህርት ከምንባቡ በማውጣት ተጠይቋል፡፡ በተከታታይ ባየኋቸው ምንባቦች ስር የወጡት ቃላት የአጠያየቅ ስልታቸውን በመቀየር ካንዱ ምዕራፍ ወደ ቀጣዩ ምዕራፍ ሲሄድ ለቃላቱ የሚሰጠው ፍቺ ሰፋ እንዲልና ማብራሪያም እንዲታከልበት የሚያዙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ከሰነድ ፍተሻው ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንፃር የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ተለጣጣቂነት ያላቸው መሆኑ ታይቷል፡፡

**ከውህደት አንጻር፡-** ውህደትን አስመልክቶ ተስፋዬ (1981፣40) ሲያብራሩ "ውህደት የትምህርት ልምዶች እርስ በርስ በመደጋገፍ የትምህርት ልምዶች አንዱ ሌላውን የማዳበርና የማበልፀግ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው" ይላሉ፡፡ በሌላ በኩል ውህደት ተማሪው የቀረበለትን የትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ሊያዛምድ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠርለት ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የዘጠነኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንመልከት፡፡

ስለ ቆሻሻ አወጋገድ (ገጽ 122)፡፡ ስለ ስኳር አመራረት ሂደት (ገጽ 139)፡፡ ስለ ጋዜጠኝነት ሙያ አጀማመር (ገጽ 136)፡፡ የጥንቱ ክርክር /ሙግት/ ምን እንደሚመስል (ገጽ 169)፡፡ ስለ ተውኔት (ገጽ 101)፡፡

ከላይ የቀረቡትንና መሰል ጥያቄዎችን በማንሳት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከአካባቢ ሳይንስ፣ ከህብረተሰብ ሳይንስ፣ ከህግና ከኪነጥበብ ጋር በማገናኘት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ይዘት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ለማዋሀድ የተደረገ ጥረት መኖሩን በሰነድ ፍተሻው የተገኙ መረጃዎች አመላካች ናቸው፡፡

## 4.3 በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር

እንደ Grellet (1991፡9) አገላለፅ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች አንዱ የጥያቄ ስብጥር ተመጣጣኝ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር ቀጥለን እንመልከት፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡** በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ስብጥር የሚያሳይ

| ምዕራፍ እና ርዕስ | የመልመጃ ጥያቄ አይነቶች | | | | በየምዕራፉ ያሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|
| | ክፍት ጥያቄዎች | ዝግ ጥያቄዎች | | | |
| | | ምርጫ | አዛምድ | እውነት/ሐሰት | |
| ምዕራፍ አንድ የቋንቋ አጀማመር | 6 | 5 | - | 5 | 16 |
| ምዕራፍ ሁለት የዘይቤ ባህላዊ ጋብቻ | 15 | 5 | - | - | 20 |
| ምዕራፍ ሶስት ረጅም ልብወለድ | - | 4 | 5 | 5 | 14 |
| ምዕሰራፍ አራት ወጣቱና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት | 5 | - | 10 | - | 15 |
| ምዕራፍ አምስት ምንም የማይቻል ነገር የለም | 14 | - | - | 5 | 19 |
| ምዕራፍ ስድስት ግጥም | | 5 | - | 5 | 10 |
| ምዕራፍ ሰባት መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን | 14 | - | - | - | 14 |
| ምዕራፍ ስምንት የሴቷ መንገድ | 14 | - | - | 5 | 19 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ የጉለሌው ሰካራም | 2 | 5 | 6 | 6 | 19 |
| ምዕራፍ አስር የሰራ ያገኛል | 11 | - | - | 5 | 16 |
| **ድምር** | 81 | 24 | 21 | 36 | 162 |
| **በመቶኛ ስሌት** | 50% | 50% | | | 100% |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደተገለፀው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አስር ምንባቦች ይገኛሉ፡፡ በአስሩ ምንባቦች ስር በአጠቃላይ 162 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተካትተዋል፡፡ የጥያቄዎቹ አብይ ክፍል ሁለት ሲሆን ይህም ክፍትና ዝግ ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ በዝግ ጥያቄዎች የቀረቡት ምርጫ፣ አዛምድና እውነት ወይም ሀሰት በሉ የሚል ጥያቄዎችን ያካተተ ነው፡፡

በአስሩም ምንባቦች ከሚገኙ 162 ጥያቄዎች መካከል 81 (50%) ክፍት ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዝግ መልክ የቀረቡ ደግሞ 81 (50%) ያህል ድርሻ አላቸው፡፡ ይህ መረጃ እንደሚያሳየን በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የዝግና የክፍት ጥያቄዎቹ ቁጥር እኩል መሆናቸውን ነው፡፡

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ስብጥር ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ በሚከተለው መልክ ቀርቧል፡፡

**ከምንባቡ የወጡ ክፍት ጥያቄዎች፡-** ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ (ገጽ 20)፡፡ ቀጥሎ ከምንባቡ በወጡ ዓ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍቺ ፈልጉላቸው (ገጽ 21)፡፡ የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ክፍል ውስጥ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩባቸው፤ በመቀጠልም በጋራ ተወያዩ (ገጽ 69)፡፡

**ከምንባብ የወጡ ዝግ ጥያቄዎች፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት መልስ ስጡ (ገጽ 5)፡፡ ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መለስ/ሽ (ገጸ 36)፡፡ ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባብ የወጡ ናቸው በ "ሀ" ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በ "ለ" ክፍል ከተዘረዘሩት በፍቺ የሚስማማውን መርጣችሁ አዛምዱ (ገጽ 53)፡፡ ቀጥሎ የሚቀርቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ በ "ሀ" ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒ የሆኑትን ከ "ለ" ክፍል በመምረጥ አዛምዱ (ገጽ 53)፡፡

ከላይ በአስረጂነት የቀረቡትና ሌሎች እነዚህን መሰል የአንብቦ መረዳት ጥያቄ ትዕዛዞች በአስሩም ምዕራፍ ስር ተካተዋል፡፡ እንደዚህ አይነት የጥያቄ ስብጥር መኖሩ ተማሪዎች ሳይሰላቹ ጥያቄዎቹን እንዲሰሩ መነሳሳትን ይፈጥራሉ፡፡ በሌላ በኩል የጥያቄዎች ስብጥር ተማሪዎች የተለያዩ የንባብ አይነቶችን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን እንደተገለፀው በቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎች ቀጥተኛ፣ ማገናዘብንና ማቀናበርን፣ የሚሹ የመመራመር፣ የግምገማና የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ወዘተ. ሊሆኑ ይገባል (Nuttall 1992:132)፡፡ ከዚህ አንጻር በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ 4፡ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነት

| ምዕራፍ እና ርዕሶቹ | የጥያቄ አይነቶች ዝርዝርና ብዛት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቀጥተኛ ጥያቄዎች | የማገናዘብና የማቀናበር ጥያቄዎች | መመራመርን የሚጠይቁ ጥያቄዎች | የግምገማ ጥያቄዎች | የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች | ብዛት |
| ምዕራፍ አንድ የቋንቋ አጀማመር | 5 | 5 | 5 | 1 | - | 16 |
| ምዕራፍ ሁለት የዘይሴ ባህላዊ ጋብቻ | 5 | 5 | 10 | - | - | 20 |
| ምዕራፍ ሶስት ረጅም ልብወለድ | 5 | 4 | 5 | - | - | 14 |
| ምዕራፍ አራት ወጣቱና የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት | 4 | - | 10 | - | 1 | 15 |
| ምዕራፍ አምስት ምንም የማይቻል ነገር የለም | 5 | 3 | 10 | 1 | - | 19 |
| ምዕራፍ ስድስት ግጥም | 5 | 5 | - | - | - | 10 |
| ምዕራፍ ሰባት መካሪ ሽማግሌ አታሳጣን | 3 | 3 | 6 | - | 2 | 14 |
| ምዕራፍ ስምንት የሴቷ መንገድ | 5 | 5 | 8 | 1 | - | 19 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ የጉለሌው ሰካራም | 6 | 4 | 7 | - | 2 | 19 |
| ምዕራፍ አስር የሰራ ያገኛል | 5 | 4 | 5 | - | 2 | 16 |
| **ድምር** | 48 | 38 | 66 | 3 | 7 | 162 |
| **ፐርሰንት** | 29.63% | 23.46% | 40.74% | 1.85% | 4.32% | 100% |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ለማሳየት እንደተሞከረው በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተካተቱ 162 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መካከል አብላጫውን የጥያቄ ቁጥር የያዙት መመራመርን የሚጠይቁ ጥያቄዎች 66(40.74%) ናቸው፡፡ በተቃራኒው የግምገማ ጥያቄዎች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሲሆን እነሱም በቁጥር ሶስት ብቻ ናቸው ይህም በመቶኛ ስሌት 1.85% ሲሆኑ ለእነዚህ ጥያቄዎች የተሰጣቸው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንደ ግምገማ ጥያቄዎች ሁሉ የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ከሌሎች አን ፃር ሲታይ አናሳ ነው ይህ የጥያቄ አይነት 7 (4.32%) ብቻ ነው፡፡ ቀሪዎቹ ቀጥተኛ፣ ማገናዘብንና ማቀናበርን የሚጠይቁት ደግሞ የጥያቄዎቹ

ቁጥር ብዙም ያልተራራቀ ሲሆን ቀጥተኛ ጥያቄ 48 (29.63%) ማገናዘብና ማቀናበርን የሚጠይቁት 38 (23.46%) በመሆን ቀርበዋል፡፡

በዚህ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ መመራመርን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ከፍ ያለ ቁጥር መያዛቸው እንደ Nuttal (1998)፣ Wright (1968)፣ Grellet (1991) ገለፃ የምንባብን አውዳዊ ፍቺ፣ የቃላትና የሀረጋትን ፍቺ የሚጠይቁ ጥያቄዎች መመራመርን በሚጠይቁ ጥያቄዎች ስር የሚፈረጁ ናቸው፡፡ በዚህ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ 46 ያህል ጥያቄዎች የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ መፈለግ፣ ለቃላቱ ተቃራኒ የሆኑትን መፈለግ፣ ለቃላትና ለሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መፈለግ በሚል መልኩ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ እንደነዚህ አይነት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መብዛት መመራመርን ለሚጠይቁ ጥያቄዎች በቁጥር በርከት ብሎ መገኘት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

ከሰነድ ፍተሻው በተገኘው መሠረት ለእያንዳንዱ የጥያቄ አይነት የተወሰነ አስረጂዎችን እንመልከት፡፡

1. ቀጥተኛ ጥያቄ፡- ቀጥተኛ ጥያቄዎች ከምንባቡ በቀጥታ ተወስደው ቃል በቃል ምላሽ የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡

**ለቀጥተኛ ጥያቄ ምሳሌዎች፡-** የዘይሴ ብሔረሰብ በየትኛው ክልልና ወረዳ ይገኛል? (ገጽ 20)፡፡ የስነ ተዋልዶን መረጃ የመስጠት ሀላፊነት ያለባቸው እነማን ናቸው? (ገጽ 52)፡፡ በከንባታ ሴት ልጅ ትገረዝ የነበረው ምን በሚል ምክንያት ነው? (ገጽ 110)፡፡

2. መመራመርን የሚጠይቁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በዚህ የጥያቄ አይነት የአንቀፆችን ፍሬ ነገር መለየት፣ አውዳዊ ፍቺ ማፈላለግ ዝርዝር ሀሳቦችን ነጥሎ ማውጣትና መሠል ችሎታዎች የሚዳብርበት ነው፡፡

**ለመመራመር ጥያቄዎች ምሳሌ፡-** ጠለፋ ልጃ ልጅቷን ይዟት ሲኮበልል የሚከሰት ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል ፍቺው፡፡ የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ ምንባቡ ውስጥ ባላቸው አውድ ፍቻቸውን ግለፁ፡፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ፍቻቸውን ፃፉ፡፡

3. ማገናዘብና ማቀናበርን የሚጠይቁ ጥያቄዎች፡- እነዚህ የጥያቄ አይነቶች የምንባቡን ዋና መልእክት የመገንዘብ፣ ሀሳብን ጨምቆ የማቀናበርና መሠል ችሎታዎች የሚዳብሩበት ነው፡፡

**ለማገናዘብ ጥያቄዎች ምሳሌ፡-** በምንባቡ ከቀረቡት አስተሳሰቦች መካከል በህይወታችን ልንከተለው የሚገባው አስተሳሰብ የትኛውን ነው? ለምን? አብራርታችሁ ተናገሩ (ገጽ 69)፡፡ የምንባቡ አጠቃላይ መልእክት (ጭብጥ) ምንድነው? (ገጽ 133)

4. የግምገማ ጥያቄዎች፡ ይህ የጥያቄ አይነት አንባቢው ምንባቡን ተመርኩዞ የቀደመ እውቀቱን ተጠቅሞ በፀሐፊው ሀሳብ ላይ የተሰማውን ስሜት የሚያንፀባርቅበት ነው፡፡

**የግምገማ ጥያቄዎች ምሳሌ፡-** ከምንባቡ ሀሳብ በመነሳት ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ አረጋዊያንና ያልተማሩ አረጋዊያን በማህበረሰቡ ያላቸው ተቀባይነት እንዴት አይነት ይመስላችኋል? በእኩል አይን ይመለከቷቸዋል? ወይስ ያበላልጧቸዋል? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፉ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 94)

5. የግል አስተያየትን የሚጠይቁ ጥያቄዎች እነዚህ የጥያቄ አይነቶች ከፅሁፍ ውጪ የአንባቢን አስተያየት በማንፀባረቅ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡

**ለግል አስተያየት ጥያቄዎች ምሳሌ፡-** ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ልጆች ለማፍራት የወላጆች ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገልፆል፡፡ ይህንን ሀሳብ ከራሳችሁ ልምድ በመነሳት አስተያየት ስጡ፡፡

የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ከዘጠነኛ ክፍል በተሻለ ሁሉንም የጥያቄ አይነት ያካተተ መሆኑን ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከጥያቄ አይነቶች መካከል ለየትኛው የጥያቄ አይነት ትኩረት እንደተሰጠ ለተማሪዎች የቀረበውን የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ በሚከተለው ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ 5፡ በመጠይቁ ለሚገኙ ጥያቄ ቁጥር 1፣ 2፣ 3 እና 10 ከአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የተማሪዎች ምላሽ በተለያየ ስምምነት ደረጃ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣም አልስማማም | አልስማማም | ለመወሰን እቸገራለሁ | እስማማለሁ | በጣም እስማማለሁ | ድምር |
| 1 | የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንባቡን አንድ ጊዜ ብቻ በማንበብ ሊሰሩ የሚችሉ ናቸው? | 5 | 18 | 4 | 22 | 1 | 50 |
| 2 | የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡን በድጋሚ ለማንበብ የሚጋብዙ ናቸው? | 4 | 1 | 1 | 20 | 24 | 50 |
| 3 | የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስዳል? | 3 | 13 | 3 | 18 | 13 | 50 |
| 7 | የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንባቡ ሳይነበብ ሊመለሱ ይችላሉ? | 23 | 17 | 2 | 6 | 2 | 50 |

ሠንጠረዥ 16 ላይ እንደተመለከተው ለተማሪዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡን አንድ ጊዜ ብቻ በማንበብ ሊሰሩ የሚችሉ ናቸው ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ “በጣም አልስማማም” 5(10%)፣ “አልስማማም” 23(46%)፣ “ለመወሰን እቸገራለሁ” ብለው የመለሱት 4(8%)፣ “እስማማለሁ” ያሉት 17(34%)፣ “በጣም እስማማለሁ” 1(2%) ናቸው፡፡ ይህ መረጃ የሚያመለክተን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡ አንድ ጊዜ ብቻ ተነቦ ጥያቄዎቹ ሊሰሩ አለመቻላቸውን ነው፡፡ ስለዚህ በተደጋጋሚ ማንበብ የሚጠይቁ ጥያቄዎች መኖራቸው ደግሞ የምንባቡን ሀሳብ ተረድቶ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት የግድ ምንባቡን መስመር በመስመር ማንበብ ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ የመመራመር ጥያቄ ባህሪ መሆኑ በምዕራፍ ሁለት ተገልፃል፡፡

በጥያቄ ቁጥር ሁለት ላይ የቀረበው ጥያቄ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ምንባቡን በድጋሚ ለማንበብ የሚጋብዙ ናቸው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ "በጣም አልስማማም" ያሉት 4(8%)፣ "አልስማማም" በማለት የመለሱት 1(2%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 1(2%)፣ "እስማማለሁ" ብለው የመለሱት 20(40%) "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 24(48%) ናቸው፡፡ ከዚህ አሀዝ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡን በድጋሚ እንዲያነቡ የሚያደርጉ ጥያቄዎች መያዛቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምንባቡን አንድ ጊዜ በማንበብ ጥያቄዎቹን ለመስራት አዳጋች መሆኑ ያንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ጥልቅ ሀሳብ መያዛቸው እና ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘት ምንባቡን በድጋሚ በጥልቀት ማንበብ ይጠበቃል፡፡

በመጠይቁ ጥያቄ ቁጥር 3፣ ላይ የቀረበው ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስዳል? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የተማሪዎቹ ምላሽ "በጣም አልስማማም" በማለት የመለሱት 3(6%)፣ "አልስማማም" 13(26%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት ደግሞ 3(6%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 18(36%)፣ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 13(26%) ናቸው፡፡ የተማሪዎቹ ምላሽ ከግማሽ በላይ (62%) ያህሉ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ለመስራት ብዙ ጊዜ እንደሚፈጅባቸው ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ለመስራት የሚወስደው ጊዜ ሰፋ ማለቱ ጥያቄዎቹን ለመስራት ምንባቡን መልሶ መላልሶ ማንበብ ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ የምንባቡን ሀሳብ በመመራመር ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለማግኘት ያስችላል፡፡

በመጠይቁ ጥያቄ ቁጥር 7 ላይ የቀረበው ጥያቄ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡ ሳይነበብ ሊመለሱ ይችላሉ ለሚለው የተሰጠው ምላሽ "በጣም አልስማማም" ያሉት 23(46%)፣ "አልስማማም" በማለት የመለሱት 17(34%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 2(4%)፣ "እስማማለሁ" ብለው የመለሱት 6(12%)፣ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(4%) ናቸው፡፡ ከዚህ አሀዝ መገንዘብ የሚቻለው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በግምት የሚመለሱ ሳይሆኑ ምንባቡን በሚገባ መነበብ እንዳለበት የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ለመስራት ምንባቡን በሚገባ በማንበብ የምንባቡን ሀሳብ ፈልቅቆ ማውጣት እና ማቀናበርን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ አንፃር ጥያቄዎቹ ምንባቡን ባላነበበ ሰው የሚመለሱ አይደሉም፡፡

በአጠቃላይ ከተማሪዎቹ የተገኘው ምላሽና ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተን በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች የአመራማሪነት ባህሪ ያላቸው የተማሪዎችን የማስተዋል አቅም የሚያዳብሩና ተማሪዎች ምላሾቻቸውን አገናዝበው እንዲመልሱ የማድረግ አቅም ያላቸው ጥያቄዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 4.3.1 ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያለው ቅንጅት

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የተለያዩ ክሂሎችን ሊያዳብሩ በሚችል መንገድ አመቻችቶ የተለያዩ ጥያቄዎችን ማውጣት ይቻላል Grellet (1991:4-5)::

**ንባብና ጽሁፍ፡-** በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ከተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መካከል አንብቦ መረዳትን ከፅሁፍ ክሂል ጋር አቀናጅቶ ለማስተማር የሚያግዙ 24 ጥያቄዎች አሉ፡፡ ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው የምንባቡን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ሀሳባቸውን በፅሁፍ እንዲያሰፍሩ፣ ለቃላት ተመሳሳይ ትርጉም እንዲሰጡ፣ በመፅሐፍ በተለያየ ቦታ ተገልፆል፡፡ ይህንን አስመልክቶ ቀጥሎ የቀረቡትን አስረጂዎች እንመልከት፡፡

በምንባቡ መሠረት ዑደቶቹን በቅደም ተከተል በስተቀኝ በኩል በቁጥሩ ትይዩ በመሙላጽ ግለፁ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 21)፡፡ የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ላይ በመፈለግ ፃፉ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 69)፡፡ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት ፍቻቸውን ፃፉ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 133)፡፡

ከላይ የቀረቡትንና መሰል ጥያቄዎችን በማቅረብ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የፅሁፍ ክሂልን እንዲያዳብሩ ሆነው ተቀርፀዋል፡፡ ይህንን የሰነድ ፍተሻ አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘውን የፅሁፍ መጠይቅ ቀጥለን እንመልከት፡፡

## የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹን በፅሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች መያዛቸውን አስመልክቶ ለአሰረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ

በጥያቄ ቁጥር 9 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በፅሁፍ እንድትመልሱ የሚጋብዙ ናቸው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የተማሪዎቹ ምላሽ "በጣም አልስማማም" 2(4%)፣ "አልስማማም" ያሉት 6(12%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት ምላሽ የሰጡት 3(6%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 24(48%)፣ "በጣም እስማማለሁ" 15(30%) ናቸው፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በፅሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዙ መሆናቸውን ነው፡፡ ከሰነድ ፍተሻው እና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በጽሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች የያዙ መሆናቸውን ነው፡፡

**ንባብና ማዳመጥ፡-** በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ 16 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎቹም መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ እንዲያነብና ተማሪዎች አዳምጠው ማስታወሻ እንዲይዙ የሚያደርጉና በያዙት ማስታወሻ ላይ እንዲወያዩና በመማሪያ መፅሀፋቸው ላይ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጡ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ቀጥሎ ከመመሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

ቀጥሎ መምህሩ የሚያነቡላችሁን አጭር ምንባብ እያዳመጣችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ማስታወሻ ያዙ፡፡ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 13-14)፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ ላይ የሚያነቡላችሁን ፅሁፍ እያዳመጣችሁ የምትመልሷቸው ናቸው፡፡ ማዳመጥ ከመጀመራችሁ በፊት ጥያቄዎቹን በሚገባ ለመረዳት እንድትችሉ ደጋግማችሁ ከነአማራጮቻቸው አንብቧቸው፡፡ ጽሁፉን ሁለት ጊዜ ስለምታዳምጡ በመጀመሪያው ዙር ለጥያቄዎቹ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፣ ያመለጧችሁ መልሶች ካሉም በሁለተኛው ዙር አሟልታችሁ መልሱ፡፡ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 25-26)፡፡ ቀጥሎ መምህራችሁ ከመምህሩ መምሪያ ላይ "ኤድስ" በሚል ርዕስ አንድ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ያዙ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በያዛችሁት ማስታወሻ ዙሪያ ተወያዩ፡፡ (10ኛ ክፍል፣ ገጽ 59)

በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ንባብን ከማዳመጥ ክሂል ጋር ብቻ ሳይሆን ማዳመጥን ከመፃፍ፣ ማዳመጥን ከንግግር ክሂል ጋርም ለማቀናጀት የተደረገው ጥረት ቢኖርም ማዳመጥን ለማስተማር ከቀረበው ምንባብ ጋር የሚጣጣም ጥያቄዎች በመማሪያ መፅሐፍ አልተካተቱም፡፡ ሁሉም የማዳመጥ ጥያቄዎች መምህሩ ከመምህሩ መምሪያ እንዲያነብ የሚጋብዙ በመሆናቸው በመማሪያ መጽሐፉ ከቀረበው ምንባብ ጋር የተቆራኙ አይደሉም፡፡ ይህም የማዳመጥ ጥያቄዎቹ ከአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ጋር አለመቀናጀታቸውን ያሳያል፡፡

**ንባብና ንግግር፡-** የንባብና የንግግር ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር ተማሪዎች በጥንድ ወይም በነጠላ ሆነው በተመረጡ ወይም በቀረበላቸው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ንግግር እንዲያደርጉ፣ እንዲወያዩና ማብራሪያ እንዲሰጡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት የሚቻል መሆኑን Grellet (1991) and Ellis (1980) ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ንባብና ንግግርን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚረዱ 46 ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በምን መልክ እንደቀረቡ ቀጥለን የተወሰኑ ጥያቄዎችን እንመልከት፡፡

ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ (ገጽ 20)፡፡ በቡድን ሆናችሁ በአካባቢያችሁ ባለ አንድ ባህላዊ ጋብቻ ላይ ጭውውት አድርጉ፡፡ (ገጽ 22)፡፡ የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት ያደረጉ ናቸው በክፍል ውስጥ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩባቸው፤ በመቀጠል በጋራ ተወያዩ (ገጽ 69)፡፡ የሚከተሉት አባባሎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው የሚያስተላልፉትን መልእክት አብራርታችሁ ተናገሩ ወዘተ. (ገጽ 94)፡፡

መማሪያ መፅሐፍ በአስሩም ምዕራፎች ባይሆንም በተወሰኑት ምዕራፎች የንግግር ክሂልን ከንባብ ክሂል ጋር በማቀናጀት ለማቅረብ የተደረገ ጥረት መኖሩን ከሰነድ ፍተሻው በተገኙ አስረጇዎች ተገልፆል፡፡ ይህን አስመልክቶ ለተማሪዎች የቀረበውን የፅሁፍ መጠይቅ ቀጥለን እንመልከት፡፡

## የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎች መያዛቸውን አስመልክቶ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ

በጥያቄ ቁጥር 4 ላይ በቀረበው ጥያቄ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ "በጣም አልስማማም" በማለት የመለሱት 5(10%)፣ "አልስማማም" ያሉት 11(22%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 6(12%) "እስማማለሁ" ያሉት 16(32%)፣ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት ደግሞ 12(24%) ናቸው፡፡ ከተማሪዎቹ ምላሽ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዙ መሆናቸውን ነው፡፡

በሰነድ ፍተሻውና ለተማሪዎች በቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ በተወሰነ ደረጃ ከተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው መቅረባቸውን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን በርካታ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ መኖራቸውን በሠንጠረዥ አንድ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ ጥቂት ቁጥር ያላቸው ብቻ ማለትም ንባብና ፅሁፍ 24 ጥያቄዎች፣ ንባብና ማዳመጥ 16 ጥያቄዎችና ንባብና ንግግር 40 ጥያቄዎች ብቻ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ 80 ጥያቄዎች ከልዩ ልዩ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተዋል፡ ቀሪዎቹ 82 ጥያቄዎችስ ለሚለው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ግልፅ መመሪያ የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይኸውም በፅሁፍ ወይስ በቃል፣ በጥንድ ወይስ በግል በምን መልኩ እንደሚሰሩ የማይገልፁ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ ይህን በሚከተሉት አስረጂዎች እንመልከት፡፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት መልስ ስጡ (ገጽ 5)፡፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ (ገጽ 5)፡፡ ቀጥሎ ከምንባቡ በወጡ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ፈልጉላቸው (ገጽ 21)፡፡ የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ በ "ሀ" ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ (አቻ) የሆኑትን በ "ለ" ክፍል ከቀረቡት በመምረጥ አዛምዱ (ገጽ 36)፡፡

ከላይ የቀረቡት በምሳሌነት ቀረቡ እንጂ እንደነዚህ አይነት ትዕዛዞች በተለያዩ ምዕራፎች ላይ ተስተውለዋል፡ ይህ የሚያሳየን ግልፅ ያልሆኑ መመሪያዎች በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ መካተቱን ነው፡፡ ይህንን አስመልክቶ ከተማሪዎች የተገኘውን ምላሽ ቀጥለን እንመልከት፡፡

የአንብቦ መረዳት መልመጃዎቹ ትዕዛዝ ግልፅነትን አስመልክቶ ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎ የቀረበ ጥያቄ

በጥያቄ ቁጥር 8 የቀረበው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የአሰራር መመሪያዎች ግልፅ ናቸው? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ "በጣም አልስማማም" 5(10%)፣ "አልስማማም" 6(10%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" 8(16%)፣ "እስማማለሁ" 19(38%)፣ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የለመሱት 12(24%) ናቸው፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት የሚቻለው የአንብቦ ጥያቄዎቹ መመሪያዎች ግልፅ መሆናቸውን ነው፡፡ ነገር ግን አጥኚዋ ከሰነድ ፍተሻ ያገኘችው መረጃ ከ162 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች መካከል 82 ጥያቄዎች መመሪያቸው ግልፅ አለመሆኑን ያሳያል፡፡ የተማሪው ምላሽ ግን መመሪያዎቹ ግልፅ ናቸው የሚል ነው፡፡

### 4.3.2 የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አደረጃጀት

የቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ በተገቢው መንገድ ከተመረጡ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው አደረጃጀት ነው፡፡ Nunan (1988)፣ Cunnings Worth (1984) እንደገለፁት አደረጃጀት በቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንደሚገባቸው የትኛው መቅደም እንዳለበት የትኛው ደግሞ መከተል እንደሚገባው የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተፈትሸዋል፡፡

**ከተከታታይነት አንፃር፡-** ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረቡ የትምህርት ይዘቶች በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ተደጋግመው ሲቀርቡ መሆኑን ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ላይ ተስፋዬ (1981)፣ Larsen-Freman (1991)፣ Cummings Worth (1984) ገልፀዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በዚህ ጥናት የተካተተው የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከተከታታይነት አኳያ ምን ገፅታ እንዳለው ቀጥለን እንመልከት፡፡

በመማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከተለያዩ ምንባቦች የሚወጡ በመሆናቸው ይዘታቸው የተለያዩ ቢሆንም የጥያቄዎቹን ጥልቀት ከሰነድ ምርመራው የተገኙ አስረጂዎችን እንመልከት፡፡

በምዕራፍ አንድ ከምንባቡ የወጡትን ጥያቄዎች በእውነት ሐሰትና በምርጫ መልክ ቀርቧልል፡ በምዕራፍ ሁለት ግን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል የሚመለሱና ከምንባቡ ለወጡ ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ መፈለግ በሚል ትዕዛዝ ጥያቄዎቹ ጠለቅ እያሉ መጥተዋል (ገጽ 5፣21)፡፡ በምዕራፍ አምስት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ከመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን በመፈለግ እንዲፅፉ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ይህ የሚያሳየን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ሰፋ እያሉ መሄዳቸውን ያመለክታል (ገጽ 69)፡፡ የሚከተሉት አባባሎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው የሚያስተላልፉትን መልእክት አብራርታችሁ ተናገሩ (ገጽ 94)፡፡

ከላይ በቀረቡት አስረጂዎች እንዳየነው ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ቀርበው አጠያየቃቸው ግን ጠለቅ እያለ መሄዱን ያሳየናል፡፡ ከዚህ አንፃር የ10ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ተከታታይነትን የጠበቀ ነው፡፡

**ከተለጣጣቂነት አንፃር፡-** በምዕራፍ ሁለት በክለሳ ድርሳን ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ተለጣጣቂነት በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች የትምህርት ይዘቶች ተደጋግመው የሚመጡበት ሁኔታ ነው፡፡ የትምህርት ይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ሊኖራቸው ይገባል ስንል በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች እያደጉና እያሰፉ መሄድ አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ስንመለከት ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ፡

በዘጠነኛ ክፍል የቀረቡ የእውነት ሀሰት ጥያቄዎች እና የምርጫ ጥያቄዎች መልሱን ከመለሱ በኋላ መልስ የሆነበትን ምክንያት እንዲያብራሩ ይጠይቃል፡፡ መማሪያ መጽሐፍ ገጽ 37፣ 101፣ 122… እነዚህን መሰል ጥያቄዎች በአስረኛ ክፍል ላይ ቢኖሩም ለመልሶቻቸው ምክንያት እንዲያቀርቡ አይጠይቁም፡፡ ከዚህ አንፃር በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ተለጣጣቂነታቸውን የጠበቁ አይደሉም፡፡

**ከውህደት አንፃር**፡- ውህደትን አስመልክቶ ተስፋዬ (1981፡40) ሲያብራሩ "ውህደት የትምህርት ልምዶች እርስ በርስ መደጋገፍ የትምህርት ልምዶቹ አንዱ ሌላውን የማዳበርና የማበልፀግ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው" ይላሉ፡፡ በተጨማሪ ውህደት ተማሪው እንዲማረው የሚቀርብለት ትምህርት ውስጥ የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያነሱ የትምህርት ልምዶችና ይዘቶች ይኖራሉ፡፡ እነዚህ የትምህርት ልምጆችና ይዘቶች የእርስ በርስ ግንኙነት

እንዲኖራቸው ተደርገው መደራጀት አለባቸው፡፡ ተማሪው የቀረበለትን የትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር ሊያዛምድ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠርለት ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ይዘቶች የሚኖራቸው የእርስ በርስ ግንኙነት እና ዝምድና ውህደት ይባላል፡፡ ከዚህ አንፃር የአስረኛ ክፍል የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንመልከት፡፡

ስለ ዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ የሚጠይቁ ጥያቄዎች (ገጽ 20)፡፡ ስለ ወጣቱና ስነ ተዋልዶ (ገፅ 51)፡፡ ስኬታማ ህይወት ለመምራት ምን መደረግ እንዳለበት (ገፅ 69)፡፡ አረጋዊያን በማህበረሰቡ ውስጥ ስላላቸው ሚና (ገፅ 94)፡፡ የመጠጥ ሱስ የሚያስከትለው ችግር (ገፅ 122)፡፡ ወጣቶች የስራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የወላጆች ሀላፊነት ምን ይመስላል (ገፅ 132)፡፡ ወጣቶች በአገር ግንባታ ዘርፍ ያላቸው ሚና (ገፅ 133)፡፡

ከላይ የቀረቡትንና መሰል ጥያቄዎች በማንሳት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከሳይንስ፣ ከህብረተሰብ ሳይንስና ከባህል ጋር በማገናኘት የጥያቄዎቹን ይዘት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ለማዋሀድ ጥረት መደረጉን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አመላካች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ በ2004 ዓ.ም በታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር አላማዎች በውስጡ ማካተቱ ተጠቁማል እነሱም፡-

ሀ. በ2004 ዓ.ም የታተሙት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነታቸውን መፈተሽ፡፡

ለ. በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች እንዴት አደረጃጀታቸውን መፈተሽ፡፡

ሐ. በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ስብጥር (የክፍትና የዝግ) ጥያቄዎች ተመጣጣኝነት መመርመር

መ. በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅት መመርመር ነው፡፡

በዚህም አብይ አላማ ስር የቱነሱ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንዲያስችልና የጥናቱ አላማ ከፍፃሜ እንዲደርስ አስፈላጊ ናቸው ተብሎ የታመነባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተግባር ላይ ውለዋል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት ያገለገሉት በዋናነት የሰነድ ፍተሻ ሲሆን በአገዥነት የፅሁፍ መጠይቅም ስራ ላይ ውሏል፡፡ ከሰነድ ፍተሻውና ከፅሁፍ መጠይቁ የተሰበሰቡት መረጃዎች በስፋት ተተንትነው የቀረቡ ሲሆን መረጃውን መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ማጠቃለያ ሀሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡

- ከጥያቄ አይነቶች አንፃር የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ስብጥር በሁለቱም መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የሚገኙ ክፍትና ዝግ ጥያቄዎችን በየምዕራፉ በመቁጠር ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሠረት በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ክፍት ጥያቄዎች አብላጨውን ቁጥር የያዙ ሲሆን የዝግ ጥያቄዎች ቁጥር አነስተኛ መሆኑን

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንኑ በተመለከተ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍ ውስጥ የክፍትና የዝግ ጥያቄዎች ቁጥር እኩል መሆኑን ከሰነድ ፍተሻ በተገኘው መረጃ ተረጋግጧል፡፡

- ዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ በዝግ መልክ ከቀረቡ የመልመጃ አይነቶች በአዛምድ መልክ የቀረበ ጥያቄ አለመኖሩ በሰነድ ፍተሻ በተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአንፃሩ አስረኛ ክፍል ሁሉም የጥያቄ አይነቶች ተካተው ቀርበዋል፡፡
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አይነትን በተመለከተ ከፍተኛውን የጥያቄ ቁጥር የያዙት የመመራመር ጥያቄዎች ሲሆኑ ለግምገማ ጥያቄዎችና የግል አስተያየትን ለሚሹ ጥያቄዎች የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡
- በቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ቅንጅት አስመልክቶ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸውን ቅንጅት በሁለቱም ክፍል ንባብና ንግግር፣ ንባብና ፅህፈት፣ ንባብ፣ ፅህፈትና ንግግር ተቀናጅተው መቅረባቸው የተጠቀሰ ሲሆን ንባብና ማዳመጥ ግን ተቀናጅተው አለመቅረባቸው ለማየት ተችሏል፡፡
- ከአደረጃጀት አንጻር በሁለቱም መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አደረጃጀታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም ሲባል ከተከታታይነት አንፃር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች እያደጉና እየጠለቁ መሄዳቸው፣ በዘጠነኛ ክፍል ላይ የታዩ ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸውን ጠበቀው በአስረኛ ክፍል ላይ መታየታቸውና በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚገኙ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር መዛመዳቸው ውህደትን የጠበቁ መሆናቸው ለማየት ተችሏል፡፡
- በሁለቱም መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ግልፅነት የጎደላቸው ትዕዛዞች በመኖራቸው በምን መልኩ እንደሚሰሩ ግራ የሚያጋቡ ጥያቄዎች መኖራቸውን ለማየት ትችሏል፡፡
- በአጠቃላይ በሁለቱም ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ወቅት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አደረጃጀት፣ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅት ላይ ትኩረት የተሰጠው ቢሆንም ከጥያቄ አይነቶች አንፃር አለመመጣጠን ችግሮች መኖራቸውን ፤ ግልፅ ያልሆኑ ትዕዛዝ ያላቸው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

መካተታቸውና ለማዳመጥ ክሒል የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን በተደረገው የሰነድ ፍተሻ ማየት ትችሏል፡፡

## 5.2 አስተያየት

በዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ አጥኚዋ የሚከተሉትን አስተያየቶች አቅርባለች፡፡

- በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች የጥያቄ ስብጥርን በተመለከተ የማመጣጠን ስራ ቢሰራ በዝግና በክፍት ጥያቄዎች መካከል አሁን የታየውን ያህል ሰፊ ልዩነት እንዳይታይ እገዛ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- የጥያቄ አይነቶችን በተመለከተ ማለትም ቀጥተኛ፣ ማገናዘብና ማቀናበርን የሚጠይቁ፣ መመራመርን የሚጠይቁ የግምገማና የግል አስተያየት የሚጠይቁ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ እንደ ምንባቡ ይዘት የጥያቄ አይነቶችን ለማካተት ጥረት ተደርጎ ጥያቄዎቹ ቢዘጋጁ አንድ የጥያቄ አይነት ብቻ ሰፊ ቁጥር የመያዙን ሁኔታ እንዲስተካከል ማድረግ፡፡
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ከፅህፈትና ከንግግር ክሂል ጋር ለማቀናጀት የተደረገው ጥረት የማዳመጥ ክሂልንም ቢያካትት መማሪያ መፃህፍቱ በቋንቋ ክሂል ቅንጅት ሂደት የበለጠ ውጤታማነት ይኖራቸዋል፡፡
- በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ላይ የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ትዕዛዞች በግልፅ አለመቀመጣቸው ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን በምን መልኩ እንደሚሰሩ ግራ የሚያጋቡ ስለሚሆኑ ጥያቄዎቹ ግልፅ የሆነ ትዕዛዝ እንዲኖራቸው ማድረግ፡፡

በአጠቃላይ በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የታዩ ጠንካራ ጎኖች የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ከንግግርና ከፅህፈት ክሒል ጋር ተቀጅተው መቅረባቸው፣ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አደረጃጀት መርህን የተከተሉ መሆናቸው በአስረኛ ክፍል ላይ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በክፍትና በዝግ የአጠያየቅ ስልት በተመጣጣኝ መልኩ መቅረባቸው ተጠናክረው ይቀጥሉ፡፡ በሁለቱም መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የታዩ ክፍተቶች ለማዳመጥ ክሒል ትኩረት አለመሰጠቱ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ትዕዛዝ ግልፅ ሆኖ አለመቀመጡ፣ የግምገማ እና የግል

አስተያየትን ለሚጠይቁ ጥያቄዎች ትኩረትት አለመሰጠቱ ሲሆን በዘጠነኛ ክፍል ላይ የዝግና የክፍት ጥያቄዎች ቁጥር አለመመጣጠን ችግሮች ታያተዋል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ለጥያቄዎቹ ግልፅ የሆነ ትዕዛዝ ማስቀመጥ የማዳመጥ ክሒልን ለማዳበር እንደ ምንባቡ ያዘት ጥያቄዎች ተመቻችተው ቢወጡ እና የግምገማና የግል አስተያት ለሚጠይቁ ጥያቄዎች እንደ ምንባቡ ይዘት የሚካተቱበት መንገድ ቢመቻች የመማሪያ መፃህፍቱ ይበልጥ ተቀባይነት እንደሚኖራቸው አጥኚዋ ታምናለች ፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት


ተስፋዬ ሸዋዬ (1981)፡፡ "ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ተሻለ ክፍሌ (2005)፡፡ "በ2004 ዓ.ም በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለአማርኛ ማስተርስ (TeAm) ኤም.ኤ.ዲግሪ በክፍል ማሟያነት የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

አለም እሸቱ (1995)፡፡ "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሣሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር፡፡" ከጥቅምት 25-29/1995 ዓ.ም አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ (ከ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢንስቲትዩት) አዲስ አበባ፡፡

አለም እሸቱ (1997)፡፡ "ንባብ፣ አንብቦ የመረዳት እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ፡፡" አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)፡፡

የሺጥላ ምንይልሸዋ (2000)፡፡ "የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ፡፡" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለአማርኛ ማስተርስ (TeAm) ኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር (2004)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ 9ኛ ክፍል፣ 1ኛ እትም፣ በአል-ጉሬር አሳታሚ ድርጅት፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስተር (2004)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ 10ኛ ክፍል፣ 1ኛ እትም፣ በአል-ጉሬር አሳታሚ ድርጅት፡፡

Aebersold, J.A. and Field, M.L. (1997). *From Reader to Reading Teacher: Issues and Strategies for Second Language Classrooms.* Cambridge: Cambridge University Press.

Alderson, J. and Urguhart, A. (eds). (1984). *Reading in a Foreign Language.* New York: Longman.

All Wright, R.L. (1981). "What Do We Want Teaching Materials For?" *ELT Journal.* Vol. 36, No. 1, 5-18::

Atkins, J. Hailom Banteyerga and Nuru Mohammed (1996). *Skills Development Methodology.* Part 2, Addis Ababa University, Department of Foreign Language and Literature.

Behor, S. Linda (1994). *The Knowledge Base of Curriculum: An Imperial Analysis.* Lanham.Lanham University Press of America.

Cornish, F. (1992). "Foreign Language Reading Comprehension as Externally Guided Thinking Reading in a Foreign Language." Journal of the International Education Center. Vol. 8.No. 2. Pp. 12-38.

Cunnings Worth, A. (1984). *Evaluating and Selecting EFL Teaching Maerials.* London: Heinemann Educational Books. Ltd.

Cushenbery, D.C. (1985). *Improving Reading Skills.* New York: Macmillan Publishing.

David, A. (2005). *Reading Skills in English.*Delhi: Common Wealth Publishers.

Davis, F.B. (1995). "Fundamental Factors of Comprehensive in Reading", Reading Research Revised. Ohio: Charless, E. Merrill.

Dighton, L.C. (1971). *The Encyclopedia of Education.*Macmillan: Crowell, Collier Educational Corporation.

Dubin, F. and Olshtain (1986). *Course Design.* Cambridge: Cambridge University Press.

_____ (1992). *Course Design: Developing Programs and Materials for Language Learning* (6thed). Cambridge: Cambridge University Press.

Ellis, R. and Brain, T. (1980). *Taching Secondary English: A Guide to Teaching English as a Second Langauge.* lon: Longman.

Goodman, K. (1970). *Choosing Materials to Teach Reading Detroit*: Wayne State University Press.

Grant, N. (1987). *Making most out of Your Textbook.* New York. Longman.

Green Wood, J. (1981). "Comprehension and Reading" in the Teaching of English as an International Language: Pp. 81-110.

Grellet, F. (1981). *Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehensive Exercises* (1sted.) Cambridge: Cambridge University Press.

_____ (1991). *Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehension Exercises* (2nded.) Cambridge: Cambridge University Press.

_____ (1995). *Developing Reading Skills: A Practical Guide to Reading Comprehension Exercises* (3rded.) Cambridge: Cambridge University Press.

Gunning, T. (2006). "Reading Comprehension: Instructional Strategies." From: http://www.nsintel.moe,edu.sg/.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching* (1sted.) London: Longman Group (UK) Limited.

_____ (1995). *The Practice of English Langauge Teaching* (2nded.) London: Longman.

_____ (2001). *The Practice of English Language Teaching* (3rded.) Cambridge: Cambridge Pearson Educational.

Hutchinson, T. and Torres, E. (1994). The Textbook as Agent of Change. *ELT Jornal*, Volume 48. Issue 4.

Larsen Freeman, D. (1986). *Techniques and Principel in Langauge Teaching.* New York: Oxford Univeristy Press.

May, F.B. (1990). *Reading as Communicaiton in an Interacting Approach* (3rded.) New York: Merill Publishing Conmpany.

Nunan, D. (1988). *Syllabous Design.* Oxford: Oxford Univeristy Press.

Nuttal, C. (1982). *Teaching Readina Skills in a Foreign Language*(1sted.) London: Longman.

_____ (1988). *Teaching Reading Skills in a Foreign Language*(2nded.) London: Heinemann.

_____ (2000). *Teaching Reading Skills in a Foreign Language*(3rded.) London: Heinemann Educational Books.

Richards, J.C. T.S. Rodgers (1986). *Approach and Method in Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Prss.

Sheldon, L.E. (ed). (1987). *ELT Textbooks and Materials Problems in Evaluation and Development.* London: Oxford University Press.

Sheng H.J. (2000). "A Cognitive Model for Teaching Reading Comprehension. "In English Teaching Forum". Vol. 38, Num 4. Pp. 12-15.

Shin, M. (1992). "Beyond Comprehension Exercises in the ESL Academic Reading Class." TESOL Avarterly Vol. 26.No. 2. Pp. 289-318.

Smith, F. (1985). *Reading.* Cambridge: Cambridge University Press.

Tyler, R.W. (1949). *Basic Principles of Curriculum and Instruction.* Chicago: University of Chicago Press.

Ur, P. (2006). *A Course in Language Teaching: Practice and Theory* 13thed Printing, Cambridge University.

Weir, C.J. (1990). *Communicative Language Testing.* New York: Prentice Hail.

Widdowson, H.G. (1978). *Teaching Language as Communication.* Oxford: Oxford University Press.

Williams, E. (1984). *Reading in the Language Classroom.*London: Macmillan Publishing.

Wright, G.W. (1968). *Towrds Efficiency in Reading.* Cambridge: Cambridge University Press.

Zintz, M.U. (1972). *The Reading Process: The Teacher an the Learner.* Dubuque Brown Company Publisher.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ
## የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ
## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር
## በተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ በአዲስ አበባ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ተማሪ ነው፡፡

**ውድ ተማሪ፡-**

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በ2004 የታተመውን የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችአይነትና አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ግቡን እንዲመታ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና አንብባችሁ ተገቢውን ምላሽ እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ስለሚደረግልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡-

**አጠቃላይ መረጃ**

**ክፍል አንድ፡-** ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ መረጃ ሙሉ

1. ፆታ---------------------------
2. እድሜ----------------------
3. የክፍል ደረጃ----------------

**ክፍል ሁለት**፡- የመጠይቁ አሞላል፡፡

በመጠይቁ ውስጥ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ምርጫ ሰጪ ወይም ዝግ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በዝግ ለቀረቡት ጥያቄዎች አምስት አምስት አማራጮች የተቀመጡ ሲሆን ከአማራጮቹ አንዱን ብቻ የምትስማሙበትን በመክበብ መልሱ፡፡ አማራጮቹም በጣም አልስማማም፣ አልስማማም፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል፣ እስማማለሁ እና በጣም እስማማለሁ ናቸው፡፡

1. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡን አንድ ጊዜ ብቻ በማንበብ የሚሰሩ ናቸው?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

2. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡን በድጋሚ ለማንበብ የሚጋብዙ ናቸው?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

3. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹን ለመስራት ብዙ ጊዜ ይወስዳል?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

4. በመፅሀፍ ውስጥ የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ በቃል ለመመለስ የሚጋብዙ ናቸው?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

5. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ አቀማመጥ ከቀላል ወደ ከባድ ነው?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

6. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ቋንቋውን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ እንድትጠቀሙ የሚግዙ ናቸው?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

7. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ ምንባቡ ሳይነበብ ሊመለሱ ይችላሉ?

   1. በጣም እልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

   4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

8. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ የአሰራር መመሪያዎች ግልፅ ናቸው?

1. በጣም አልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

9. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በፅሁፍ እንድትመልሱ የሚጋብዙ ናቸው?

1. በጣም አልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

10. የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎቹ በተለያየ መንገድ ሊመለሱ ይቻላሉ?

1. በጣም አልስማማም 2.አልስማማም 3. ለመወሰን ያስቸግረኛል

4. እስማማለሁ 5. በጣም እስማማለሁ

# አማርኛ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፱ኛ ክፍል



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

**. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልስ ስጡ፡፡**

የሰው ልጅ የሚጠቀምበት መግባቢያ ከአንደበቱ በሚያፈልቀው ቋንቋ ብቻ ነው፡፡

የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ እውቀት በመላምት ደረጃ ያለና ትክክለኛው ገና ያልተደረሰበት ነው፡፡

ጥንታዊ ስእሎች፣ በድንጋይና በሸክላ ላይ ተጽፈው በቁፋሮ የተገኙ ጽሑፎች ስለ ቋንቋ ጥንተ አመጣጥ በቂ መረጃን አስገኝተዋል፡፡

በስነልሳን ተመራማሪዎች ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው የቁስአካላውያን የቋንቋ ጥንተ አመጣጥ መላምት ነው፡፡

ቁስአካላውያን ለቋንቋ መገኘት ምክንያቱ የሰው ልጅ ይሁነኝ ብሎ ሥራን መሥራቱ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

**. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ፡፡**

ከሚከተሉት አንዱ ከአንደበት የሚወጣ ድምጽ ሁሉ ቋንቋ እንደማይሆን ማሳያ ነው፡፡

ሀ. አንደበት ለንግግር ድምጾች የሰላ ከመሆኑ የተነሳ፣ ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ድምጾችን ማውጣት መቻሉ፤

ለ. የንግግር ድምጾች የተለዩና በቁጥርም የተወሰኑ ሆነው፣ ፍች ለማስገኘት የሚቀናጁበት ሥርዓት ያላቸው መሆኑ፤


ሐ. የሰው ልጅ ሲያዝን፣ ሲደሰትና ሲበሳጭ የሚያወጣቸው የለቅሶ፣ የጩኸትና የሳቅ ድምጾች በቋንቋነት መቆጠራቸው፤

መ. የሰው ልጅ በአንደበቱ ማፍለቅ የሚችለው የንግግር ድምጾችን በመሆኑና ለሌሎች ድምጾች የሰላ አለመሆኑ፡፡

፬. በዘይሴ ብሔረሰብ ውስጥ የዳሎ ጋብቻ ዓላማው ምንድን ነው?

፭. በዘይሴ ባህል በተመሳሳይ ጎሳ አባላት መካከል ጋብቻ መፈጸም የማይቻለው ለምንድን ነው?

፮. ከዚህ በታች የሰው ልጅ በተለያዩ ስነስርዓቶች የሚያልፍባቸውን የህይወት ዑደቶች የምታመለክቱበት ምስል ቀርቧል:: በምንባቡ መሰረት ዑደቶቹን በቅደም ተከተል በስተቀኝ በኩል በቁጥሮቹ ትይዩ በመሙላት ግለጹ::




አንድ ____________

ሁለት ____________

ሦስት ____________

አራት ____________

፯. ቀጥሎ ከምንባቡ በወጡ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍች ፈልጉላቸው::

ሀ. መደበኛ ባህላዊ ጋብቻ በብሔረሰቡ ወግ እና ደንብ ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም ነው::

ለ. ከቤተ-ዘመድና ከጎረቤት ጋር ተማክሬ መልሱን እነግራችኋለሁ በማለት ይሸኛቸዋል::

ሐ. ጠለፋ ልጁ ልጅቷን ይዟት ሲኮበልል የሚከሰት ነው::

መ. አንዲት ልጃገረድ በተለያዩ ባህላዊ ተጽዕኖዎች ምክንያት ሳታገባ ብዙ ጊዜ ልትቆይ ትችላለች::

ሠ. ወደ የመጣች ልጃገረድ እግረ እርጥብ ስለሆነች በረከት ይዛ ትመጣለች ተብሎ ይታመናል::

2. በልቦለድ ዓለም የሚባለ ገጸባሕርይት በሀገሪቱ ዓለም ላይ ሲኖሩ እንቅስቃሴ የነበሩ በዎች ሲሆኑ ይችላሉ::
3. ረጅም ልቦለድ በባህሪው መጠን ስለ በመሆኑ ደራሲው ከአንድ በላይ [illegible] ጭብጥ የማሳየት እድል ይኖረዋል::
4. የአንድ ልቦለድ ታሪክ በሀገሪቱ ዓለም ላይ በመሆኑ በማሰሪፍ ለ [illegible] ይችላል::
5. ልቦለድ ሰዎች ካነበቡት ታሪክ ማንነታቸውን እንዲፈትሹ እንዲ [illegible] የህይወትን ገጽታዎች ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱ ንቃተ ህሊናቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛል::

## ፪. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላ[illegible] ተመሳሳይ(አቻ) የሆኑትን በ"ለ" ክፍል ከቀረቡት በመምረጥ አዛምዱ::

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| | ሀ. ገበያ |
| 1. ምግብ | ለ. ዘርጋው |
| 2. አውን | ሐ. ቀና |
| 3. ነበሳ | መ. አንድ |
| 4. አበዜን | ሠ. በብብ |
| 5. ንብይ | ረ. [illegible] |

## ፫. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልስ/ሽ/::

1. ከሚከተሉት ውስጥ ስለልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ልቦለድ ድርሰት የመጻፍ ችሎታን የሰው ልጅ በ[illegible] የሚችለው ግጥም ነው::
   - ለ. የልቦለድ ታሪክ በመሪጃ የተደገፈ እንዲሆን ያስፈልጋል::
   - ሐ. ልቦለድ በሰው የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ገጠመኝን መሠ[illegible] አድርጎ የሚጻፍ የፈጠራ ድርሰት ነው::
   - መ. በልቦለድ የማስዋብ ወይም የማጋነን ሁኔታ አይፈቀድም::

[illegible]. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በ 'ሀ' ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በ 'ለ' ክፍል ከተዘረዘሩት በፍች የሚስማሟቸውን መርጣችሁ አዛምዱ::

| 'ሀ' | 'ለ' |
|---|---|
| 1. ፈታኝ | ሀ. እኩያ |
| 2. ዝንባሌ | ሊ. ክፍል |
| 3. ዘርፍ | ሐ. ፍላጎት |
| 4. ግፊት | መ. ህቡዕ |
| 5. አቻ | ሠ. ጫና |
| | ረ. አስቸጋሪ |

፫. ቀጥሎ የሚቀርቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: በ 'ሀ' ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በፍች ተቃራኒ የሆኑትን ከ 'ለ' ክፍል በመምረጥ አዛምዱ::

| 'ሀ' | 'ለ' |
|---|---|
| 1. መብት | ሀ. ቋሚ |
| 2. ብዙሀን | ለ. ደከመ |
| 3. በረታ | ሐ. ጥቂት |
| 4. ተለዋዋጭ | መ. ግዴታ |
| 5. ግልጽ | ሠ. ስውር |
| | ረ. ዳበረ |

## ክፍል ሁለት:- መጻፍ

፩. የሚከተሉትን መልመጃዎች በመመሪያው መሠረት ሥሩ::

ሀ. በጭውውት፣ በውይይት ወይም በትምህርታዊ ጉባኤዎች ላይ በመገኘት ማስታወሻ ይዛችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንባብ አሰሙ::

ለ. ተማሪዎች መምህራችሁ የሚያነብቡላችሁን መመሪያዎች አዳምጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ አስፉሩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ::



77

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**ሀ. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን 'እውነት' ስህተት የሆኑትን ደግሞ 'ሐሰት' በማለት መልሱ።**

1. ...ንታ ቢስ የሆኑ ሰዎች የ "ይቻላል!" መርህ ተከታዮች ናቸው።
2. የጽሑፉ አቅራቢ በዚህ ምድር ላይ የማይቻል ነገር የለም የሚል አቋም አላቸው።
3. የሚቻሉ ነገሮችን "አይቻልም!" ሲሉ የነበሩ ሁሉ ትንቢታቸው ሰምሮላቸዋል።
4. እስካለንበት ዘመን ድረስ የሰውን ልጅ ጨረቃ ላይ ማሳረፍ አልተቻለም።
5. የስኬታማ ህይወት ተቋዳሾች ዓለምን በብሩህ መልኩ የሚቀበሉ ናቸው።

**ለ. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ላይ በመፈለግ ጻፉ።**

1. ተቆራኘ
2. ተስፋ
3. ስኬት
4. ሰበከ
5. ተጨናገፈ
6. መፍትሔ
7. ስንቅ
8. ማነፅ
9. ቀና
10. ጥልቅ

**ሐ. የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ክፍል ውስጥ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩባቸው፤ በመቀጠልም በጋራ ተወያዩበት።**

1. በምንባቡ ከቀረቡት አስተሳሰቦች መካከል በህይወታችን ልንከተለው የሚገባው አስተሳሰብ የትኛውን ነው? ለምን? አብራርታችሁ ተናገሩ።
2. "አዲስ ታሪክ ለመሥራት ይነቃቃል" የተባለው ትውልድ የትኛውን አስተሳሰብ የሚከተለው ነው? ለምንስ ስኬታማ ይሆናል ተባለ?
3. ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ህይወታቸውን በምን ዓይነት መንገድ ማስተካከልና መምራት እንዳለባቸው ያላችሁን ሀሳብ ተናገሩ።

አይጥላህ፤ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ" የሚለው አባባል ከላ ካነሳነው የአረጋውያንን ምክርና ቃል ከማክበርና ከመፈጸም ጋር የተቆራ ነው:: ስለዚህ እነዚህ ዜጎች ማህበረሰቡን በመምራትና በመቆጣጠር በዘ ያላቸውን ሚና ትልቅ ግምት በመስጠት ልዩ እንክብካቤና ጥበ ሊደረግላቸው ይገባል::

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎ በቃል መልሱ::**

ሀ. አረጋውያን በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና ምንድነው?

ለ. ማህበረሰባችን ለአረጋውያኑ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? በማስረጃ በማስደገፍ አብራሩ::

ሐ. ስነ ቃሎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ፋይዳ ምንድን ነው?

መ. በወጣቶችና በአረጋውያን መካከል ያለውን ግንኙነት እንዴት ትገልጹታላችሁ?

ሠ. ከምንባቡ ሐሳብ በመነሳት በመናዊ ትምህርት የተማሩ አረጋውያንና ያልተማሩ አረጋውያን በማህበረሰቡ ያላቸው ተቀባይነት እንዴት ዓይነት ይመስላችኋል? በእኩል ዐይን ይመለከቷቸዋል? ወይስ ያበላልጧቸዋል? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፉ::

**፪. የሚከተሉት አባባሎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው:: የሚያስተላልፉትን መልዕክት አብራርታችሁ ተናገሩ::**

ሀ. ሚዛን የሚደፋ

ለ. የእድሜ ባለፀጋ

ሐ. የኑሮ ውጣ ውረድ

መ. አዕምሮአዊ ሀብት

ሠ. መሸምገል

ረ. ስናይ ተግባር

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ትክክል የሆኑትን 'እውነት' ስህተት የሆኑትን 'ሀሰት' በማለት መልሱ።**

1. ተበጀ የተባለው ሰው በአካባቢው የሚታወቀው ችፍግ ባለ ጢሙና በጎፈሬ ፀጉሩ ነው።
2. ተበጀ ምንም አንኳን በመጠጥ ሱስ የተጠመደ ቢሆንም በማህበራዊ ህይወቱ የተሳካለት ነበር።
3. ተበጀ ድምጹ የሚሰማውና ለአንቧጓሮ የሚነሳሳው መጠጥ ከጠጣ በኋላ ነው።
4. የመጠጥ ሱሰኛው ተበጀ ሱሱን ለማቆም ብዙ ጊዜ ሞክሮ ነበር።
5. ተበጀ ትዳር መስርቶ የሚኖር ሰው ነው።
6. ተበጀ የቀበሌው እድር አባል የሆነው መጠጥ ለመተው ቃል-ስለገባ ነው።

**፪. ምንባቡን መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልሱ።**

1. "የተበጀ የህይወት ታሪክ ፍጹም ገድል ነው" ሲል ____ ማለቱ ነው።
   - ሀ. አስቂኝ
   - ለ. አስገራሚ
   - ሐ. አስደንጋጭ
   - መ. አስፈሪ
2. የጉለሌ ባልቴቶች የቡና ማጣፈጫ ወሬ የተበጀ________ነው።
   - ሀ. አረመኔነት
   - ለ. ቅጥያጣ ድፍረት
   - ሐ. ሰካራምነት
   - መ. ዶሮ ነጋጼነት
3. ተበጀ በመጠጥ ሱሰኛነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ ________ ነበር።
   - ሀ. የተደነቀ
   - ለ. የተረሳ
   - ሐ. የተወደሰ
   - መ. የተገለለ
4. ተበጀ በመጠጥ ሱሰኛነቱ የተነሳ፣
   - ሀ. ሰው ደብድቦ ታስሮ ነበር፤
   - ለ. ስራ ለመቀጠር አስቦ አልተሳካለትም፤
   - ሐ. የዶሮ ንግድ ከስሮበታል፤
   - መ. ከእድርና ሰንበቴ ተባሯል፤

**ተማሪዎች! ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?**

የኢትዮጵያ ትልቁ ሀብት ወጣቱ ነው። ወጣቱ አስተሳሰቡ ብሩህ ነው፣ ትኩስ ጉልበት አለው፤ ከፍተኛ የመፍጠር ችሎታ አለው፤ ፈጣን ነው፣ አንድ ጊዜ የጀመረውን ነገር ደጋግሞ በመሥራት ለማሸነፍ ሰፊ የእድሜ ገፀ-በረከት ያለው የህብረተሰባችን ክፍል ነው። ከማንም የተሻለ መኖር የሚፈልገው ወጣቱ ነው። ይህንን ሁሉ ለማድረግ ብዙ መሥራት ያለበትም ወጣቱ ነው።

በጥቂቶች የኢኮኖሚ ነፃ መውጣት ብዙ ሰው ጥሩ ኑሮ መኖር አይችልም። የአስተሳሰብ ድህነትን የሚያወርሱት ልጅ ባለፀጋ አይሆንም፤ አትሆንም። ስለዚህ ሥራ ፈጣሪ ለመሆን የበለጠ እድል ላለው ለወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል የሥራ ፍላጎትና ተነሳሽነትን እናስተምረው።

*(ወሮታው በዛብህ፣ ኢንተርፕሬነርሽፕ፣1998፣109፣ ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ።)*

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ከምንባቡ የወጡ ዓረፍተነገሮች በመመርመር ትክክል የሆነውን "እውነት" ስህተት የሆነውን "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. ወጣቶች የሥራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የማድረግ ኃላፊነት ያለባቸው ወላጆች ብቻ ናቸው።
2. ሀገር የሚያድገው እያንዳንዱ ቤተሰብ በኢኮኖሚ ሲሻሻል ነው።
3. የሀገርን እድገት በተመለከተ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወተው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ነው።
4. ወላጆች ለልጆቻቸው ማውረስ የሚገባቸው ቀና አስተሳሰብንና ታታሪነትን ነው።
5. ወጣቶች በአገር ግንባታ ዘርፍ ሚና የላቸውም።

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**፩. በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ::**

1. ቀደም ባሉት ጊዜያት በከንባታ ሴት ልጅ ወደ ትምህርት ቤት በባህሉ ይፈቀድ ነበር::
2. ዶ/ር ቦጋለች በተወለዱበት ዘመን ሴቶች የቤት ውስጥ ሥራቸውን ከጨረሱ አደባባይ መዋላቸውን የሚቃወም አልነበረም::
3. የዛቶ አካባቢ ሰዎችን እጅግ ያስገረመው የቦጋለች አባት ቆርቆሮ ቤት የተሠራበት ውድ ገንዘብ ሳይሆን የቦጋለች ተግባር ነበር::
4. የቦጌ አካባቢ ሰዎች የቦጌን ሀሳብ ለመከተል ፍጹም ፈቃደኛ አልሆኑም::
5. በዶ/ር ቦጋለች ጥረት በከንባታ አካባቢ የሴት ልጅ ግርዛት በእጅጉ ቀንሷል::

**፪. የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፤ ምንባቡ ውስጥ ባላቸው ዐውድ ፍቻቸውን ግለጹ::**

1. ትጋት
2. ቢጤዎቿ
3. 'ቁም ነገር
4. አንግባ
5. ቁርጠኛነት
6. ስመ-መልካም
7. ግብረ ሰናይ
8. ሽንጣቸውን ገትረው

**፫. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ::**

1. በከንባታ ሴት ልጅ ትገረዝ የነበረው ምን በሚል ምክንያት ነው?
2. ትንሿ ቦጌ በአካባቢዋ ማህበረሰብ ዘንድ ሞገስ ያገኘችባቸውን ሁለቱን ዋና ዋና ተግባራት ግለጹ::
3. ዶ/ር ቦጋለች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ምን ተስፋ ሰንቀው ነው?
4. ሰላማዊ እኩልነትን የሚሻ ዜጋ ለማፍራት ዋና መሳሪያው ምንድን ነው?
5. ከዶ/ር ቦጋለች ህይወት ምን ተማራችሁ?

## ፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**ሀ. ቀጥለው የቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡**

የግጥምን ዕድሜ በትክክል ይህን ያህል ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡

ግጥም ለደስታ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ስሜቶችም መግለጫ ነው፡፡

ስድ /ዝርው/ ጽሑፍ እና ግጥም ስሜትን ለማስተላለፍ እኩል ናቸው፡፡

ቀለም ማለት ተናባቢ ድምጽ ብቻውን ሲመጣ የሚፈጥረው መዋቅር ማለት ነው፡፡

5. ምት ማለት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን መጥራት ማለት ነው፡፡

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

. የግጥም ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቁጥብ አይደለም ሐ. ዜማ አለው

ለ. ምት አለው መ. ምጣኔ አለው

2. ቁጥብነት ሲባል የ______ ቁጥብነት ማለት ነው፡፡

ሀ. የሐሳብ ሐ. የቃላት

ለ. የጽንሰ ሐሳብ መ. ሁሉም

3. የስንኝ መገን ግጥም በሐረግ ስንት ቀለም አለው?

ሀ. ፬ ለ. ፭ ሐ. ፮ መ. ፯

4. ግጥም ተለክቶ የሚያልቀው በ ____ውስጥ ነው

ሀ. ስንኝ ሐ. ሐረግ

ለ. ቀለም መ. ቤት

5. ለአዕምሮ የሚጥም ባለ ስልት የቋንቋ አደራደር ______ ይባላል፡፡

ሀ. ስነ ግጥም ሐ. ሐረግ

ለ. ስንኝ መ. ቀለም



83

# አማርኛ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ፯ኛ ክፍል



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፡- ንባብ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፡፡

1. ዘዬ ምንድን ነው?
2. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ የሚለየው በምንድን ነው?
3. ቋንቋ እንዴት እንደሚያድግ በምሳሌ አስረዱ፡፡
4. የቋንቋን ስነልሳናዊ አገልግሎት ግለጹ፡፡
5. ሰዎች ቋንቋ ባይኖራቸው ኖሮ፣ ማህበራዊ ህይወታቸው ምን ገጽታ ይይዛል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ለ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ፣ ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡

1. ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው፡፡ ማንኛውም ድምጽ ደግሞ እስካግባባ ድረስ ቋንቋ ነው፡፡
2. ቋንቋ በስርዓት የሚሰደሩ ድምጾች ስብስብ ነው፡፡
3. አንድ ቋንቋ "ሞተ" የሚባለው በተናጋሪዎቹ ላይ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስ ነው፡፡
4. የቋንቋ ስነልሳናዊ አገልግሎት የተናጋሪውን ማንነት ማሳወቅ ነው፡፡
5. ቋንቋ ሀሳብ ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን መቀበያም ነው፡፡
6. አንድ ሰው ስለራሱ "እንዲህ ነኝ" ብሎ ካልተናገረ በስተቀር፣ ከንግግሩ ተነስተን ስለማንነቱ መረጃ ማግኘት አንችልም፡፡
7. በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የዘዬ ልዩነት መኖር መግባባትን አያግድም፡፡



84

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

ፊ. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ::

1. ከሚከተሉት አንዱ ከስነ-ቃል ሊመደብ አይችልም::
   ሀ) ምሳሌያዊ ንግግር፣
   ለ) እንቆቅልሽ፣
   ሐ) የሥራ ላይ ግጥሞች
   መ) ልቦለድ መጻሕፍት::

2. ስለስነ-ቃል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ይሸጋገራል::
   ለ) በጽሑፍ ባለመስፈሩ በስነጽሑፍ ስር አይመደብም::
   ሐ) የልዩ ልዩ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያ ነው::
   መ) ራሱን የቻለ የጥናት መስክ ነው::

3. በክዋኔ ጊዜ የተደራሲያን ተግባር ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከዋኙን ማጀብ፣
   ለ) መልስ መስጠት፣
   ሐ) የስነ-ቃል ቅርጹን በመከወን መምራት፣
   መ) ማዳመጥ፣

4. ለስነ-ቃል ግለሰብ ደራሲ የማንጠቅስለት ለምንድን ነው?
   ሀ) የህዝብ አእምሮና የልማድ ውጤት በመሆኑ፣
   ለ) ምድቡ ከስነጽሑፍ ባለመሆኑ፣
   ሐ) በተለያዩ ጊዜያት የሚከወን በመሆኑ፣
   መ) ደራሲው በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ በመሆኑ፣



85

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለፁ::

1. ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ የሰው ልጅ ጽሕፈትን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የተገለገለባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎች ያመለክታል::
2. አንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊ ነው ለመባል በጽሑፍ መቅረቡ ብቻ በቂ አይደለም::
3. በጽሑፍ በሚገባ ተቀነባብሮ በቃላት የተገለጸ ሁሉ ከስነ-ጽሑፍ ይቆጠራል::
4. ስነ-ጽሑፍ በማህበረሰቡ ልዩ ቦታ እንዲይዝ ያደረገው መተላለፊያው በጽሑፍ መሆኑ ነው::
5. የሰው ልጅ ሁል ጊዜም ገጠመኙን ለማውጋት ያለው ፍላጎት ለስነ-ጽሑፍ መኖር እንደ አንድ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል::

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጡ::


1. ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ጽሑፍ ኪነጥበባዊ ብቃት መመዘኛ አይደለም::
   ሀ) በአገላለጹ የተባ መሆን፣
   ለ) በጽሑፍ አማካይነት መገለጽ፣
   ሐ) ሕይወትን ማሳየት፣
   መ) ማራኪና ሳቢ መሆን፣
2. ከሚከተሉት አንዱ "የተጻፈ ነገር ሁሉ ስነ-ጽሑፍ ነው" የሚሉ ወገኖችን ሀሳብ አያንጸባርቅም::
   ሀ) የዕለት ውሎ ማስታወሻና የሥራ ደብዳቤዎች ከስነ-ጽሑፍ ይቆጠራሉ::

. ልቦለዱን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ::

1. የውርስ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ዘነበ ከሳቀ በኋላ፣ "ሶስት ሺ ብርና የኔንም ወንድምነት ከዚሁ ጋር" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራሩ::
3. ለበልዩ ድሃ መሆን "ምክንያቶች ናቸው" የምትሏቸውን ዘርዝሩ::
4. የአካባቢው ባለስልጣኖች ዘነበን በቃጠሎው የጠረጠሩት ከምን ተነስተው ነው?

ፎ. በልቦለዱ ባለታሪኮች ላይ የተከሰተው ችግር ከመነሻው እንዳይፈጠር፣ ችግሩ ከተፈጠረም በኋላ በቀላሉ እንዲፈታ ምን መደረግ ነበረበት ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ድምዳሚ በየቡድን መሪያችሁ በክፍል አቅርቡ::

፬. ዋና ዋና የሆኑትን የልቦለዱን ድርጊቶች በቅደም ተከተል አስቀምጡ:: ይህንን ስታደርጉ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየትና የሚከተለውን ምስል ደብተራችሁ ላይ በመጠቀም ይሁን::






87

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

፩. ግጥሙን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ::

1. እንደ ግጥሙ ከሆነ ባለታሪኩ ቃል ሲገባ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም::
2. ባለ ብዙ ልሳን ሲል ንግግር ታበዣለሽ ማለቱ ነው::
3. "ያን ስምሽን ፍቶ" የሚለው ኋላ ቀርነትን ነው::
4. ባለ ታሪኩ ሀገሩን ለማልማት ሥራ ውስጥ ገብቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::
5. "መከዳዬ ነሽ" የሚለውን ሐረግ የተጠቀመው ሀገሩ መኖሪያው መሆኗን ለማመልከት ነው::

፪. በግጥሙ መሠረት ለተከታዮቹ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ኢትዮጵያን ለደፈራት ጠላት መነሻ ምክንያት የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ) ረሐብ
   - ለ) ጦርነት
   - ሐ) እርዛት
   - መ) አለመማር
2. ባለታሪኩ "ፊቴን ላልመልሰው" ሲል ምን ማለቱ ነው?
   - ሀ) ያለፈውን ላልመለከት
   - ለ) ላላፈገፍግ
   - ሐ) ከኋላዬ ያለውን ላልመለከት
   - መ) የልጅነት መልኬን ላልመለከት
3. "ያን ስምሽን ፍቶ" የሚለው የትኛውን ስሚን ነው?
   - ሀ) የጥንት ስልጣኔና ክብሯን
   - ለ) ለምለም ሀገር መሆኗን
   - ሐ) ኢትዮጵያ የሚለውን
   - መ) ኋላ ቀርነቷን
4. እንደ ተራኪው አገላለጽ ኢትዮጵያን የማይመለከተው የትኛው ነው?
   - ሀ) ተረጅነት
   - ለ) ቅኝ ተገዢነት
   - ሐ) የጥንት ገናናነት
   - መ) ኋላ ቀርነት



88

**ጽሑፍን አጥንቶ በቃል ለማቅረብ የማያግዙ ነጥቦች:-**

- በጽሑፍ የቀረበን ሐሳብ በቃል ለማጥናት በቅድሚያ ጽሑፉን ለመረዳት ማንበብ፣
- በጽሑፍ በተያዘው ሐሳብ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ነጥቦችና ዝርዝር ነጥቦችን መለየት፣
- ዋናና ዝርዝር ነጥቦች የተያያዙበትን ተጠየቅና ቅድም ተከተላቸውን መረዳት፣
- ወደ ትናንሽ ክፍሎች በመከፋፈል ለአጠናን ማመቻቸት፣
- የቀረበው ጽሑፍ ሀሳብ በቃል እስኪያዝ ድረስ ከፍላጎት ጋር ሀሳብን ሰብስቦ ደጋግሞ ማንበብ፣
- በቃል ለሚቀርብ ንግግር የሚጠና ሐሳብ የሚጠናው፣ ሐሳቡ ብቻ ሳይሆን በንግግር የሚቀርብበት ሁኔታ ጭምር እንደሆነ መረዳት፣

1. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የቀረቡ ገለጻዎችን፣ ማብራሪያዎችን ወይም ጥያቄና መልሶችን ተከታትላችሁ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

*(ማስታወሻ አያያዝ በተመለከተ በሌሉት ምዕራፎች የተነሱ ነጥቦችን አስታውሱ።)*

## ክፍል ሶስት፦ ጽሕፈት

፩. የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ በጥሞና አንብቡና «እሱ» የተባለው ሰው ምን ዓይነት ባህርይ እንዳለው፣ እንዲህ ዓይነት ባህርይ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ። ባቀረባችሁት ሳይም ተወያዩ።

እሱነው እሱ

እሱነው እሱ
ዐይን ባይኖረው
ለምን ብርሃን ኖረ የሚለው፤
እግር ባይኖረው
ለምን መንገድ ኖረ የሚለው ፤
እሱነው እሱ
ከቀናቴ
ፀሐይቱን የሰረቀ
በመንገዴ
አሜከላ ያፀደቀ።

*(ደበበ ሰይፉ፣ 1980፣55)*



89

8 በሁለተኛው ትዕይንት በተውኔቱ ውስጥ የተገለጸው መቼት በየትኛው ይገለጻል?

ሀ) ምሽት፣እመት ውድነሽ በጣሙ ቤት፣

ለ) ንጋት፣ እመት ውድነሽ በጣሙ ቤት

ሐ) ምሽት፣ ቄስ ታምሩ ቤት፣

መ) ንጋት፣ቄስ ታምሩ ቤት፣

9 በቀረበው ጽሑፈ-ተውኔት ውስጥ ምክንያትና ውጤት የተፈጠረው እንዴት ነው?

ሀ) እመት ውድነሽ በጣሙና አያ ቦጋለ መብራቱ ቢጋቡ ተረዳድተው መኖር መቻላቸው፣

ለ) እመት ውድነሽ በጣሙ አያ ቦጋለ መብራቱን ቢያገቡ አያ ቦጋለ መብራቱ የሚሞቱ መሆናቸው፣

ሐ) አያ ቦጋለ መብራቱ እመት ውድነሽ በጣሙን ቢያገቡ እመት ውድነሽ ሊሞቱ መቻላቸው፣

መ) አያ ቦጋለ መብራቱ እና እመት ውድነሽ በጣሙ ቢጋቡ ሁለቱም ሊሞቱ የሚችሉ መሆናቸው፣

፪. ጥንድ ሆናችሁ በመወያየት የሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የገቡበትን ፍች ስጡ።

1. ትዕይንት
2. ሙዳይ
3. መድረክ
4. ክዋኔ
5. ተውኔት
6. የገሀድ ዓለም
7. አሳረገ
8. ውሃ አጣጪ

፫. የተዉኔቱን ዋና ዋና ድርጊቶች ቅደም ተከተላቸዉን ጠብቃችሁ ግለጹ፣ አሠራራችሁ በድርጊት አንድ በተገለጸው ምሳሌ መሠረት ይሁን።

ድርጊት አንድ፣ <u>አያ ቦጋለ፣ እመት ዉድነሽ በጣሙን ለማግባት ስለሚችሉበት ሁኔታ ከቄስ ታምሩ ጋር ተመካከሩ።</u>

ድርጊት ሁለት፣-----------------------------------------

ድርጊት ሦስት፣ -----------------------------------------

ድርጊት አራት፣-----------------------------------------



90

5. አፈርን ወይም ውሃን በማይበክልበት ቦታና ሰዎችም በዚሁ ሳቢያ ለአደጋ በማይጋለጡበት ሁኔታ ማስወገድ አለብን፡፡

### የቃላት መጥበቅና መላላት

በአማርኛ ቋንቋ አንዳንድ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የተለያየ ፍች ይሰጣሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃላት በተናጠል ሲታዩ፣ የትኛውን ፍች እንደያዙ ወይም ጠብቀው ይሁን ላልተው እንደሚነበቡ ለመለየት ያስቸግራል፡፡ በዓረፍተነገር ውስጥ ሲገኙ ግን ይህንን ለመለየት ይቻላል፡፡ በአማርኛ ጠባቂ ድምፆች በአብዛኛው የሚገኙት በቃሉ መካከል ሲሆን አልፎ አልፎ በቃሉ መጨረሻ ላይም ይገኛሉ፡፡ በአማርኛ የቃል መጀመሪያ የሆነ ድምጽ አይጠብቅም፡፡

፩. የሚከተለውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ የቀረቡት ቃላት በመጀመሪያ ጠብቀው፣ ቀጥሎም ላልተው ሲነበቡ (ሲባሉ) የሚሰጡትን ፍች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በምትሠሯቸው ዓረፍተነገሮች አመልክቱ፡፡

*ምሳሌ፡-* <u>በራ</u> - መብራቱ በአስራ ሁለት ሰዓት <u>በራ</u>፡፡

- ሙባረክ ራሱ <u>በራ</u> ስለሆነ፣ ኮፍያ ማድረግ ያዘወትራል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | አጣና | 6 | አያት |
| 2 | ዋና | 7 | ጠላት |
| 3 | አካፋ | 8 | አለ |
| 4 | አባይ | 9 | አዳኝ |
| 5 | አላት | 10 | ሰባ |

4. በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ ዮናታን ዲምብልቢ እንዴት ሊጠቀስ ቻለ?
5. ዜና እና ጋዜጠኝነት ወይም ጋዜጠኝነትና ዜና ምን ግንኙነት እንዳላቸው ግለጹ፡፡
6. በኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ የተጀመረው በማን ዘመነ መንግሥት ነው?
7. የግል ጋዜጠኝነት ከመንግሥት ጋዜጠኝነት በምን ይለያል?
8. በኢትዮጵያ የግል ጋዜጠኝነት መቼ ተጀመረ?
9. በኢትዮጵያ፣ የግል ጋዜጠኝነት እንዲጀመር ምክንያት የሆነው ምን ይመስላችኋል?

፪. ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መስርቱና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ፡፡

ሀ) ዓለም አቀፍ
ለ) ሬዲዮ መጎርጎር
ሐ) "አንቱታ"
መ) ማውጋት
ሠ) እንደቅጠል ሲረግፍ
ረ) ይፋ ማውጣት
ሰ) መቀጣጠል
ሸ) እንደአሸን ፈሉ

## ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት

፩. በሚቀጥለው ታሪክ ውስጥ ቃልን ከቃል፣ ዓረፍተነገርን ከዓረፍተነገር፣አንቀጽን ከአንቀጽ ያያይዙ መሸጋገሪያና አያያዥ ቃላትን ጥንድ ሆናችሁ ለዩ፡፡

“በአሥራ ስምንተኛው ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ገደማ፣ የሱዳን ጦር ምዕራባዊውን የኢትዮጵያን ድንበር እያለፈ ዘረፋ በማካሄድ የአካባቢውን ሕዝብ በጣም ያስቸግር ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ፣ የወገን ጦር (የኢትዮጵያ ጦር) ከጎንደር በመንቀሳቀስ፣ በሀገሩ ላይ የተቃጣውን ሕገ ወጥ ድርጊት



92

2. በዚህ ዘመን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን እንደ ጥንታዊው ግሪካዊ ዴሞስቴን ከሰዎች ተገልሎ ለብቻ በመሆን ንግግር መለማመድ አስፈላጊ ይሆናል? እንዴት?
3. ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን መሰልጠን ወይም መገራት ያለባቸው የአካል ክፍሎች የትኞቹ ናቸው?
4. ዴሞስቴን ራሱን ወደጥሩ ተናጋሪነት ለማሸጋገር ያደረጋቸው ጥረቶች ምንድን ናቸው?

፪. በቀረበላችሁ ምንባብ አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገዉ ዋና መልእክት (ጭብጥ) ምንድነው? በአጭሩ ግለጹ::

፫. ለሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ የያዙትን ፍች በተብራራ መንገድ ስጡ::

1. የንግግር ጥበብ
2. የተገራ አንደበት
3. የታረመ አንደበት
4. አንደበተ - ርቱዕ
5. መንፈስ ማበልጸግ
6. ምላስ ማስላት

## ክፍል ሁለት:- ንግግር

፩. ዴሞስቴን ጥሩ ተናጋሪ ለመሆን ያደረጋቸው ጥረቶች ተገቢነት እንዳላቸዉና እንደሌላቸው የሚያስረዳ የጋራ ውይይት አካሂዱ::

፪. በምርጥ ንግግር አቀራረባቸው የምታደንቋቸው ሰዎች (መምህርቻችሁ፣ የክፍል ወይም የትምህርት ቤት ጓደኞቻችሁ ወይም ሌሎች) የንግግር አቀራረባቸው (በይዘትና በቅርጽ) እንዴት እንደሆነ በመዘርዘር ክፍል ውስጥ ተወያዩ፡

፫. ቡድን መሥርታችሁ፣ ንግግርን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ከማንበብና ንግግርን በጽሑፍ አዘጋጅቶ አጥንቶ በቃል ከመናገር የትኛው አድማጭን ማርካት እንደሚችል ተወያዩ::




93

ስለከተተው መውጫ አጥቶ ሲኳትን ይታያል፡፡ ___7___ ለሌለው ነገር እንኳን ትኩረት ሰጥቶ ሲጨነቅና ሰውነቱ እንደቂጠማ ___8___ ይታያል፡፡

፪. መዝገበ ቃላትን በመጠቀም ለሚከተሉት ቃላት ፍች ከፈለጋችሁላቸው በኋላ ፍቻቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች ከራሳችሁ አመንጭታችሁ ጻፉ፡፡

| | |
|---|---|
| 1. በሰና | 4. ቋፍ |
| 2. ተከነ | 5. ደብዛ |
| 3. አበሰ | |

፫. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ፣ ምንባቡን መሠረት አድርጉና ስዕላዊ መግለጫውን ወደ ጽሑፍ በመቀየር፣ የጥንቱን ሙግትና የዛሬውን ክርክር የየግልና የጋራ ባህርይ ዘርዝራችሁ በመፃፍ አቅርቡ፡፡ እያንዳንዱ ክብም አንዱ በአንዱ ውስጥ ወይም አንዱ ከአንዱ ውጪ ለምን እንደዋለ አስረዱ፡፡




*መግለጫ*

- የጥንቱ ሙግት ባህሪ = ሀ
- የዛሬው ክርክር ባህሪ = ለ
- የጋራ ባህሪ = ሐ



94

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ የራሴ መሆኑን እና በፅሑፍ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ፅሑፎችና መረጃዎች  በትክክል የጠቀስኩት መሆኔን በሚቀጥለው ስሜንና ፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ዘውዱ ታህሱ ታገኝ

ፊርማ ______

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የሂዩማኒቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል፤ ስነ ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ

ነሀሴ 2007 ዓ.ም